

# « ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ »



« ጾመ አርብዓ መዓልተ ወአርብዓ ሌሊተ ከመ ያድኅነነ »

ዓመታት ሙሉ አሀል ውኃ ያልቀመሱት ጻድቅ

የመንበር ማርያም አስደናቂ ተአምር

ፀድዋና ቅዱስ ጊዮርጊስ

ቅዱስ ሚካኤል ዕውር አበራ

ቁጥር ፲ ፲፱፻፹፮ ዓ/ም

አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ፣ ታሪክና ባሕል ፣ የመንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ዜና ለሕዝበ ክርስቲያን የሚያቀርብ» ስለሆነ «ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ» ተብሎ ተሠይሟል ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ኮሚቴ እየተዘጋጀ በየወሩ አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።


ዋና አዘጋጅ ሊቀ ልሳናት ንቅዐ ጥበብ ወንድም

ረዳት አዘጋጅ መ/ ኤፍሬም በየነ

ስልክ 11 26 63

የመልእክት ሣጥን ቍጥር 1283

አዲስ አበባ




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ ።

# በጾም የሚገኝ ፡ ምህረት ፤

በዘመነ ብሉይ የነበሩ አበው ያላቸውን ጽኑዕ እምነት እግዚአብሔር መሠረት በማድረግ ሱባኤ ገብተው አመድ ነስንሰው ማቅ ለብሰው ከእህል ከውሃ ተለይተው በጾም በጸሎት ተጠምደው እግዚአብሔር አምላካቸውን ሲለምኑት ቁጣው በትዕግስቱ መዓቱ በቸርነቱ ይለውጥላቸው እንደነበር ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል ።

ሊቀ ነቢያት ሙሴ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በሲና ተራራ በመጾሙ አሥሩ ሕጎች የተጻፈባትን ታቦት ከእግዚአብሔር እጅ ተቀብሏልና እግዚአብሔርንም ቃል በቃል አነጋግሯል ነቢዩ ሙሴ በሲና ተራራ ከእግዚአብሔር ጋር በቆየበት ጊዜ እሥራኤላውያን የወርቅ የጥጃ ምስል (ጣኦት) አቁመው ሲአመልኩ በመገኘታቸው እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው በተነሳ ጊዜ ሊቀ ነቢያት ሙሴ እነሱን ከምታጠፋ እኔን ከሕይወት መጽሐፍ ደምስሰኝ በማለት ፈጣሪውን በጾም በጸሎት በመጠየቁ ወገኖቹ እሥራኤልን ከታዘዘባቸው ቁጣ አድኗቸዋል ፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርባ ሌሊትና አርባ መዓልት በገዳመ ቆሮንቶስ በጾመ ጊዜ ሦስቱ አርእስተ ሐጣውእን ማለትም ትዕቢትን ስስትን አፍቅሮ ነዋይን ለምእመናን ድል ነስቶላቸዋል የሰው ልጅ የሕይወት መሰናክል የሆነውንም ዲያብሎስን (ሰይጣንን) ሑር እምድህሬየ ሰይጣን «አንተ ሰይጣን ከኋላየ፣ ሂድ በማለት ከተከታዮቹ ምእመናን ፊት በአምላካዊ ቃሉ ያስወገደው በዚሁ በመዋዕለ ጾሙ ጊዜ ነው ።

ስለዚህም ነበር አርባ ቀንና አርባ ሌሊት የጾመ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱ ሊፈውሱት ያልቻሉትን አንድ ጋኔን ያደረበት በሽተኛ ወደ እርሱ አምጥተውት ከፈወሰው በኋላ ደቀ መዛሙርቱ እኛ ልናወጣው ያልቻልነው ስለምንድነው ነው ብለው በጠየቁት ጊዜ «ዝንቱ ዘመድ ኢይወጽእ ዘእንበለ ጾም ወጸሎት» ይህ ሰይጣን ያለጾምና ያለጸሎት አይወጣም በማለት የተናገረው ።

በዚህ መሠረት ጾማችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ሀብተ ፈውስ ሀብተ ጸጋ ሀብተ ረድኤት ሊአሰጥ የሚችል ጾም እንዲሆንልን «ይጹም ዐይን ይጹም ልሣን እዝንኒ ይጹም እምሰሚአ ሕሡም በተፋቅሮ» ፍቅርን ገንዘብ በማድረግ ዐይን ይጹም ክፉ ከማየት እንደበትም ይጹም ክፉ ከመናገር ጆሮም ይጹም ክፉ ከመስማት በማለት የሀገራችን ሊቅ ቅ/ያሬድ እንደተናገረው ጾም ስንጾም እህል ከመብላት ውሃ ከመጠጣት ለተወሰኑ ሰዓታት ብቻ መቆየት ሳይሆን ዐይኖቻችን እያዩ ጆሮዎቻችን እየሰሙ ክፉ ነገሮችን ከማድረግ ሰውነታችን መከልከል አለብን ።

በአንደበታችንም ሰውን የሚአሳዝን ነገር መናገር የለብንም በዚህ የተቀደሰ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ራሳችንን አጽንተን በጸሎታችን በጾማችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ብንለምነው ለአባቶቻችን የሰጠውን ጸጋና ረድኤት ለእኛም ይሰጠናል የዝናሙ ጊዜ ሳያጥር የጸሐዩ ጊዜ ሳይበዛ ጠለ በረከት ለዘር እከለ በረከት ለመኸር ይሰጠናል ።

የጾምና የጸሎት መሠረቱም ሆነ ጉልላቱ የእርስ በርስ ፍቅር ነው ስለዚህ እርስ በእርሳችን ተዛዝነንና ተፋቅረን ሀብት ያለን ለሌለው አካፍለን ፍጹም በሆነ ክርስቲያናዊ የፍቅር መንገድ ተመላልሰን ፈጣሪያችን ብንፈልገው እናገኘዋለን ብንጠራው ይሰማናል ብንለምነው ሐሳባችን ይፈጽምልናል ። በዚህ ታላቅ መዋዕለ ጾም የተጣላ አስታርቀን እርስ በእርሳችን ተፋቅረን ከሸንገላ ነጻ በሆነ ሕሊና በቁጣው ፈንታ ትዕግሥቱ በመዓቱ ፈንታ ቸርነቱ እንዲሰጠን እግዚአብሔር አምላካችንን እንለምነው ።

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ

www.ethiopianorthodox.org

## ማውጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ርዕሰ አንቀጽ | ፫ |
| ፪ | ቃለ ምዕዳን | ፭ |
| ፫ | አስተርዕዮተ መስቀል | ፯ |
| ፬ | ልትድን ትወዳለህን | ፰ |
| ፭ | ጾመ ሕርቃል | ፱ |
| ፮ | ዐድዋና ቅ/ጊዮርጊስ | ፲፩ |
| ፯ | ጸድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ | ፲፫ |
| ፰ | ከነነዌ የምንማረው | ፲፯ |
| ፱ | ገዳማዊ ሕይወት | ፲፰ |
| ፲ | የቤተ ክርስቲያን ታሪክ | ፲፱ |
| ፲፩ | የጸሎት ኃይል | ፳፩ |
| ፲፪ | ሰማያዊ አባታችሁ | ፳፪ |
| ፲፫ | ሰንበትን አክብር | ፳፫ |
| ፲፬ | የደወሌው ቅዱስ ሚካኤል ዕውር አበራ | ፳፬ |
| ፲፭ | አስደናቂ ተአምር በወንበር ማርያም | ፳፮ |
| ፲፮ | የቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል | ፳፯ |
| ፲፯ | የደቡብ ወሎ ሀ/ስብከት | ፳፰ |
| ፲፰ | ለመምህር ክፍለ ዮሐንስ መርሻ አቀባበል ተደረገ | ፴ |
| ፲፱ | ለ፲፱፻፹፱ አብያተ ክርስቲያናት ልብሰ ተክህኖ የረዱት | ፴ |
| ፳ | በቅርጸ ቅርጽ ሙያቸው የታወቁት አባት | ፴፪ |


# ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ የ፲፱፻፹፯ ዓ/ም የዐቢይ ጾምን መግቢያ ምክንያት በማድረግ ለመላው ሕዝበ ክርቲስያን በረዲዮና በቴሌቪዥን ያስተላለፉት ቃለ ምዕዳን ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ

አምላክ አሜን ፤

በመላ ሀገራችን ኢትዮጵያ በየቦታውና በተለያየ ተግባር የምትኖሩ የመንፈስ ልጆቼ ምእመናን ፍል ውል እግዚአብሔር ሰላም ፀጋና ክብሩ ይድረሳችሁ ። ይደርባችሁ ።

የመንፈስ ልጆቼና ወገኖቼ ምእመናን ፤

ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር እንደተባለው የኑ ጊዜ ፍስና የሥጋ ተግባራት የምንፈጽምባቸው ጊዜያት አሉ ለመብልና ለደስታ ጊዜ እንዳለው ሁሉ ለጾምና ለጸሎትም የተወሰነ ጊዜ መስጠት ይኖርብናል ፤ የሚቀጥሉት ሳምንታት የንስሐ የጾምና የጸሎት ጊዜያት ናቸው ። ጊዜው ዐቢይ ጾም በመባል ይታወቃል ፤ ዐቢይ የተባለበትም ምክንያት የዓለም መድኃኒት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው ታላቅ ጾም ስለሆነ ነው ይህም ዐቢይ ጾም በዘመ ብሉይ የነበሩ አበው ነቢያት ጾመውታል ። ነቢዩ ሙሴ በሲና ተራራ ላይ ወጥቶ ከእህልና ከውሀ ተከልክሎ አርባ ቀንና ሌሊት ከፈጣሪው ጋር ቃል በቃል ተነጋግሯል የህይወታችን መመሪያ የሆኑ ዐሠርቱ ቃላት የተጻፈባቸው ጽላተ ኪዳን ከእግዚአብሔር እጅ ተቀብሎአል ። ኢሳይያስ ሕዝቅያስና ኤያሱም እንደዚሁ አርባ አርባ ቀንና ሌሊት እየጾሙ ብዙ የኃይልና የተአምራት ሥራ ሠርተዋል ። በዘመነ ሐዲስም ጌታችን መድኃኔታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ከኃጢአታችን ለማንጻት በፈለገ ዮርዳኖስ በዕደ ዮሐንስ ከተጠመቀ በኋላ ዕለቱን ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ በመሄድ የማዳን ሥራውን የጀመረው በጾምና በጸሎት ነው ። በጾመበትም ጊዜ ሰይጣን በትእቢት በስስትና በፍቅረ ንዋይ የአመጣበትን ፈተና ፤ በትህትና በትእግሥትና በጸሊአ ንዋይ ድል በመንሳት አስተምሮናል ። እኛም ስንጾምና ስንጸልይ እንዴት መዘጋጀት እንደሚኖርብን አሳይቶናል ። በጾማችንና በጸሎታችን የምናገኘውን መንፈሳዊ ኃይል በዓለም ያለውን ልዩ ልዩ ፈተና ተቋቁመን በጾም በጸሎት በፍቅርና በትህትና ፤ ድል ለማድረግ ስንበቃ ቅዱሳን መላእክት ሊረዱን ሊጠብቁንና ሊያገለግሉን እንደሚላኩ ገልጾ አመልክቶናል (መዝ ፤ ፺ ፤ ፲፩) ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ይኸንን አበው የተጠቀሙበትን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ቃሉን ለማስተማር ወደ ሕዝብ ከመውጣቱ በፊት የሥራው መጀመሪያ አድርጎ ፈታኙን ጠላት ሰይጣንን ድል የነሳበትን ጾም የተፈተነ የሕይወት መድኃኒት አድርጋ ትጠቀምበታለች ። ጾም የነፍስን ቁስል የሚያድን መድኃኒት መሆኑን ትገልጻለች ፤ የነቢያት የሐዋርያትና የጌታ ጾም እንዲጾም ለተከታዮቿ ምእመናን ታስተምራለች ።

ጾም ማለት ለተወሰነ ጊዜ ከምግበ ሥጋ መከልከል ቢሆንም ምስጢሩ የሥጋን ፈቃድ ለነፍስ ፈቃድ ማስገዛት ለሕይወት ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ ሕግና ሥርዓት መታዘዝ ማለት ነው ።

የጾም ጊዜ ማለት የንስሐ ጊዜ ማለት ነው ። ንስሐ ማለትም የሰሩትን በደል እያሰቡ በሐዘንና በዕንባ በጸሎት በምጽዋትና በስግደት ከእግዚአብሔር ይቅርታን መለመን ማለት ነው ። በጾም ወራት ክርስቲያኖች ሊፈጽሟቸው የሚገባቸው ዐበይት ተግባራት አሉ ፤ እነዚህም ፍቅር ፤ ትህትና ፤ ምጽዋት ፤ የመሳሰሉትም ናቸው በጾማችን ጊዜ ለተወሰነ ሰዓት ከእህል ከውሃ ተከልክለን የአጠራቀምነውን ምግብ ለችግረኞችና ለጾም አዳሪዎች በማካፈል ነዳያንን በርህራኄ ስጦታችን ማሰብ ይኖርብናል ።

በአጠቃላይ በዓለም ዙሪያና በአካባቢያችን አትኩረን የተመለከትን እንደሆነ በዘመናችን ብዙ ችግሮች አሉ ።

- ተደጋጋሚ የድርቅና የረኃብ ክስቶችን፣
- በሰው ልጆች መካከል የሚፈጠሩ የርስ በርስ ግጭቶች ፤ አለመግባባት ፤ አለመጣጣምና ጦርነትቶች ፤
- በተለይም በሀገራችን ከነበረው የአሠራር ኋላ ቀር የሆነ ልምድና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ደካማ የምርት ውጤት ፤
- የሰው ልጆች የርስ በርስ ሰላም ማጣትና አለመተማመን ፤
- የምድራችን ከዕፅዋትና ከልምላሜ ፀጋ መራቆት በዓለማችን የአሳደረው ተፅዕኖ በማኅበረ ሰብ ሕይወት ላይ ከፍተኛ የእልቂትን ፤ የመፈናቀልን የስደትንና የልምና አዳሪነትን ሁኔታ በአሳዛኝ መልኩ እያጠናከረው መምጣቱ ዘወትር በዐይናችን የምናየው በጆሮአችን የምንሰማው ነው

እያሌ የሰው ልጆች በዓለም ዙሪያና በየአካባቢያችን የኑሮ ፈተና ላይ ወድቀው በሞትና በሕይወት መካከል ሲታገሉ እንሰማለን እናያለን ።

በተለይ በሀገራችን ለሁሉ የሚተርፍ የተፈጥሮ ኃብት እያለን ፤ ሊሠራ የሚችል በቂ የሰው ኃይል ሞልቶ በድኅነት መታየት ረሀብተኛ መሆንና በበሽታ መንገላታት እጅግ የሚያሳፍር ከመሆንም አልፎ መንፈስን የሚያቃጥል የኅሊና እሳት ነው ። ሰብዓዊ ክብርንም ይነካል ። ስለሆነም መላው የሀገራችን ሕዝብ ለመልሶ መቋቋምና ለዘላቂ ልማት በሚነደፈው ዕቅድ በመተባበር ድኅነትን ፤ በሽታ



www.ethiopianorthodox.org

ንና ፣ ኋላቀርነትን ለማስወገድ ታጥቆ መነሳት ይና ርበታል ። በድካም ፍሬ ራሱን ቤተ ሰቡንና ሕብረ ተ.ነቡን ከመርዳትም አልፎ ምድር ለምለም አረሯ በጉርፍ እየተሸረሸረና እየተጠረገ ከመወሰድ ከዕፅ ዋትና የልምላሜ ፀጋ እየተራቆተች ለድርቅና ለቃ ጠሎ ከመጋለጥ እንድትድን መጣር ይኖርበታል ። ሁሉ ሰው በፍቅር ፣ በሰላምና በበጎ መንፈስ በመተ ያየት ሀገሩን ለማልማት ፣ ሕዝቡን ለማበልጸግና የጋራ እድገቱን ለማፋጠን ተግቶ መሥራት ያስፈ ልጋል ። እያንዳንዱ የሀገራችን ዜጋ በተቀናጀ ጉል በትና በጋራ ጥረት ራሱን መቻል በራስ መተማመንና ኢትዮጵያዊ ክብሩን ጠብቆ ማስጠበቅ ይኖርበ ታል ።

በአንድ ወቅት ከአቅም በላይ ችግር ያስጨነ ቀው ሕዝብ ጊዜያዊ ዕርዳታ ከሌላ መሻት ግድ ቢሆ ንበትም ሁልጊዜ የውጭ እርዳታና ድጋፍ ፈላጊ መሆን የለበትም ።

ወገኖችን ሁሉ ለልማት ሥራ በማሰለፍ በው ጤቱ ከአሳፋሪ የልምኖ አዳሪነት ልምድና ከተ መጽዋችነት ጥላ ሥር መውጣት ይኖርበታል ። በተፈጥሮ ሀብት የበለፀገች አገርና ጤናማ ሕይወት ይዞ ተረጅ ከመሆን የበለጠ አሳፋሪና ሰብአዊ ክብ ርን የሚነካ ነገር ባለመኖሩ ዕርዳታን ከልማት ጋር በማቀናጀት ችግሮችን በየመልኩ ከገጸ ምድር ለማ ጥፋት ለሚደረገው ጥረት ሕዝበ ክርስቲያን እን ዲተባበር የሥነ ልቡናና የመንፈስ ዝግጅት እንዲ ኖረው ማነቃቃት በሥራውም አብሮ መሰለፍ የቤተ ክርስቲያናችን የወቅቱ መልእክትና ተግባር ነው

- ችግር ፣ ረሀብ ድህነትና በሽታ እንዲወገድ፣
- የሕዝቡ የልማት እንቅስቃሴና ጥረት ሁሉ ፍሬማ እንዲሆን ፤
- በተለያዩ ምክንያት የተሰደዱ ወደ የሀገ ራቸው እንዲመለሱና በተሻለ ኑሮ እንዲ ቋቋሙ ፣ በቅንነትና በትጋት አገልግሎት እናት አገራቸውን እንዲያገለግሉ ፣
- እናት አባት ያጡ ሕፃናት አሳዳጊና ሰብ ሳቢ አግኝተው እንዲያድጉ ፣
- የታመሙ ሁሉ እንዲድኑ ፤
- በዓለም ዙሪያ ያሉ የሰው ልጆች ግጭትና ጦርነት እንዲወገድ በዓለም ላይ ፍጹም ሰላም እንዲሰፍን ፣ ፍቅር መተሳሰብና መተዛዘን በሁሉ ዘንድ እንዲኖር ቤተ ክርስቲያናችን በተለ ይም በጾሟ ወራት አጥብቃ ትጸልያለች ፣ ታስተም ራለች ።

የክርስትና ሃይማኖት የሥራን ክብርነት የሚ ያስተምር ነው ሰው ሁሉ በድካሙ ውጤት ራሱን የመርዳት ግዴታ እንዳለበት ተጽፎአል ሳይሠራ መኖር የሚሻ ቢኖር ሌሎች የደከሙበትን እንዳይ ካፈል ተከልክሎአል ። ጤናማ ሕይወትን ከሥራ ጋር ማለማመድ ጊዜን አክብሮ በሥራ ላይ ማዋል ከጾም የሚቆጠር ነው ሥራ ከኃሜት ከስንፍና ከድ ካም የሰው እጅ ከማየት ከመሳሰሉትም የጥፋት ሥራዎች ይጠበቃል ። የጾም ምሥጢር ከተግባራዊ ትርጉሙ አንጻር ሲነገር ዐይንን ክፉ ከማየት ፣ ጆሮን ክፉ ከመስማት ፣ መከልከል ፣ አንደበትን ከኃሜት መቆጠብ ልቡናን ከቂም ከበቀል ማንጻት መንፈስን ከክፉ ምኞትና ሐሳብ ማጥራት በአጠቃ ላይ ሕዋሳት ሁሉ ከክፉ ሥራ እንዲጠበቁ ማድረግ ነው ። በጾማችን ወራት ሰውን የሚያስደስት እግዚ አብሔር የሚወደው በጎ ሥራ ሰርተን ለመጠቀም እንድንበቃ የልዑል እግዚአብሔር ረድኤት ከሁ ላችን ጋር ይሁን ።

እናት ሀገራችን ኢትዮጵያን በአንድነትዋ በነ ፃነትዋ ይጠብቅ ይባርክ ይቀድስ ። አሜን


አባ ጳውሎስ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ/ም
አዲስ አበባ

# አስተርዕዮተ መስቀል

አስተርዕዮ ማለት መገለፅ ፣ መታየት ሲሆን አስተርአየ ታየ ፣ አሳየ ፣ ተገለፀ ፣ ተመለከተ ፣ አመለ ከተ ከሚለው ቋሚ ግስ የመጣ መስቀልን ከተቀበረ በት ከርሰ መቃብር የገለጸውን ዐቢይ ምስጢር የሚ ያካትት ንኡስ አንቀጽ ነው መገለጽ መታየት አንድ ሰው ከተሰወረበት ቦታ ወጥቶ በሜዳና በተራራ ላይ በቆመ ጊዜ ታየ ተገለጸ ይባላል እንደዚህም ሁሉ ከመታጣት ተፈልጎ መገኘት ካስ ፈልገው ያጡትን ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ሀብት ማግኘት የሚቻለው አጋጣሚ ጊዜ ሲገኝ ነው ይኸውም ምሳሌ በኃይለ መስቀሉ እምነው ለሚድኑ ሁሉ የመዳናቸውን ተስፋ የሚያገኙት እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ነው እንጂ እነሱ ባሰቡት ዕለትና ሰዓት አለመሆኑን ያስረዳል ። እንግዲህ ከዚህ ቀጥሎ ወደ ማዕከላዊ ትምህርቱ እንግዲህ ከዚህ ቀጥሎ ወደ ማዕከላዊ ትምህርቱ የሚያደርሰውን ቀኙን መንገድ ለመያዝ አመቺ እን ዲሆን የቅዱስ መስቀልን ታሪክ በሁለት ክፍሎ ማቅ ረብ ይጠቅማል ፩ኛ/ መስቀል የምእመናን ኃይል መሆ ኑንና ድል አድራጊነቱን ያሳወቀው በዓላዊ ንጉሥ በመክስምያኖስ ላይ በተቀዳጀው አክሊለ መዊዕ ነው መክስምያኖስ ከ፪፻፺፩ ዓ/ም ጀምሮ እስከ ፫፻፲፰ ዓ/ም በሮም የነገሠ እግዚአብሔርን አላውቅም ብሎ አብያተ ክርስቲያናትን ያፈረሰ የክርስቲያኖችን ደም በግፍ ያፈሰሰ ግፈኛ አመፀኛ ንጉሥ ነበረ በዚያን ጊዜ የተፈጸመውን በደልና ግፍ መጠኑ ይህን ያህላል መልኩ ይህን ይመስላል ብሎ ለመናገር የሚያስቸግ ርና ምሳሌ የታጣለት ስለሆነ ዓመተ ሰማዕታት ተብሎ አልፏል የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ፰ ከቁጥር ፩-፯ ብንመለከት የሁኔታውን አንጻር ያመለክተናል ። በሮም የነበሩ ክርስቲያኖችም ከስቃያቸው ጽናት የተ ነሣ መጥተህ እድነን ብለው ወደ ሃይማኖታዊው መስፍን ወደ ቆስጠንጢኖስ መልእክት ላኩ ቆስጠን ጢኖስም በቍስጥንጥንያ ክፍለ ግዛት የምትገኘው የብራንጥያ አውራጃ ገዡ ደጅ አዝማች ነበር መስፍኑ ቆስጠንጢኖስም በምእመናን እንባ የታተመውን ደብዳቤ ገልጾ አንብቦ እግዚአብሔር ሕዝቤን ጠብቅ ብሎ አደራ የሰጠው ሰው የተቀበለውን አደራ ዘን ግቶ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ይህን ያህል ስቃይ ያደርሳልን?ብሎ አዘነ አዝኖም አልቀረ ሌላ እረዳትና ልዩ መሳሪያ ሳይፈልግ የመስቀሉን ምልክት ብቻ መመሪያ አድርጉ ያለውን ሰራዊት አስከትሎ የክርስ ቲያኖችን ደም ለመበቀል ወደሮም ዘመተ ። መክሰ ምያኖስም የቆስጠንጢኖስን ወደ እርሱ መዝመቱን በሰማ ጊዜ በ፴፪ መሳፍንት የሚካተተውን ሠራዊት አስከትሎ ወደ ቆስጠንጢኖስ መጣ ባሕረ ኢዮጴ ላይ ሲደርስ ማይ ለማይ ተያዩ በዚያን ጊዜ በመክስምያ ኖስ ላይ አድረው ያንን ሁሉ ከንቱ ሥራ ሲያሠሩት የነበሩ አጋንንት በቆስጠንጢኖስ ሰራዊት ፊት ያለ ውን ትምዕርተ መስቀል አይተው መቋቋም ስላልተቻ ላቸው መክሰምያኖስን ትተውት እንደ ጢስ ተነው ጠፍተዋል መክሰምያኖስንም ከእነ ሠራዊቱ የባሕረ ኢዮቴ ድልድይ ተንዶ ከጥልቁ በታች ጥሎ አስጥ ሞታል የመስቀሉም ኃይል በዚህ ጊዜ ተገለጸ ከዚህ በኋላ ሀይማኖታዊው መስፍን ቆስጠንጢኖስ በድል አድራጊነት እሮም ከተማ ገባ ፡፡

ዘመክስምያኖስ እልው ድህረ ሀልቀ እድሜ ቆስጠንጢኖስ ቦአ ወነግሠ በሮሜ ይላል ስንክ ሳር ነሐሴ ፲፰ ትርጓሜውም አላዊ ንጉሥ የመክስም ያኖስ እድሜ ካለቀ መንግሥቱም ከተፈጸመ በኋላ ቆስጠንጢኖስ እሮም ገብቶ ነገሠ በግፍ የፈሰሰው የክርስቲያኖችም ደም ተመለሰ ማለት ነው በሮም የነበሩ ምእመናንም ቆስጠንጢኖስን በመንፈሳዊ ልዕ ልና ተቀብለው በሮምም ላይ ንጉሥ ነገሥት አድርገው አነገሡት እርሱም የፈረሱትን አብያተ ክርስቲያናት መልሶ አደሰ ከሞት የተረፉ ከስደት የተመለሱ ምእመ ናን መስቀል ኃይልነ መስቀል ቤዛነ እያሉ ደስታ ቸ ውን በአደባባይ ገለጹ ስለዚህ የቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት ዘመነ እረፍት ዘመነ ህድአት ተባለ ።

ትርጓሜውም ምእመናንን ከስደት የተመለሱ በት ከመከራ ያረፉበት የጸጥታ የሰላም የእረፍት ዘመን ማለት ነው ንጉሡ ቆስጠንጢኖስ ለክብረ መን ግሥቱ የሥራ መጀመሪያ ያደረገው እናቱ ንግሥት



ነዋ መስቀለ ሰላም

እሌኒን ወደ ኢየሩሳሌም ልኮ በጎልጎታ የተቀበረውን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል ፈልጋ እንድታስወጣ ነበር ይኸውም አልቀረም በንግሥቲቱ እሌኒ ፍለጋ በክርስቶስ እርዳታ ቅዱስ መስቀል መጋቢት ፲ ቀን ከተቀበረበት መቃብር ወጥቶ ታምራቱን መለኮታዊ ኃይሉን የገለጸበት ዕለት ሆነ የቅዱስ መስቀሉንም መገኘት አብሮ ተቀብሮ የነበረውን የክርስቲያኖች ተስፋ ይዞት ተነስቷል ስለዚህ እስከ መጨረሻው ጊዜ ምእመናን መስቀል ሀይላችን ነው መስቀል መዳ ኀኒታችን እያሉ ሲያመሰግኑት ኃይለ ረድኤትን



www.ethiopianorthodox.org

የሚገልጽበት ዕለት ሁናእል ዘና ቆስጠንጢናስ ምዕራፍ ሰባት ስምንትና ዘጠኝ እስከ መጨረሻው ያለውን እንመልከት ። ሁለተኛው ክፍል የመስቀልን ምርኮ በተመለከተ ይሆናል በ፮፻፲፯ ዓ/ም እንድርያኖስ የተባለ የፋርስ ንጉሥ ወደ ምድረ እሥራኤል ወጥቶ ኢየሩሳሌምን ከቦ አስጨነቃት እሥራኤልም ጠባቂ እንደሌለው መንጋ በየተራራው ተበተኑ ንጉሡም ከህዝቡ የገደለውን ገድሎ የማረከውን ማርኮ ሲመለስ መስቀሉን ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ አውጥቶ ከምርኮኞች ጋር ወደ ፋርስ ይዞት ወረደ ። ለሚቀበለውም ሕዝብ የክርስቲያኖች መመኪያ የነበረውን መስቀል እምጥቼላችኋለሁ እንደፈቀዳችሁ አድርጉት አላቸው ይህንም ማለቱ ያዋረድኩት መስሎት ነው ከዚህ በኋላ ንጉሡ እንድርያኖስ ከልዑላኑ ከመሳፍንቱ ጋር መክሮ መስቀሉን በቤተ መንግሥቱ በታች ከሚገኘው ስውር እዘቅት ቀበረው እሳተ መለኮትን ተሸክሞ የነበረውም ቅዱስ መስቀልም በታምራት ከሰማይ እሳት አውርዶ የፋርስን ከተማ ከላይ እስከ ታች አቃጠለው አነደደው በሕዝቡም ዘንድ ታላቅ ሽብር ሆነ ምድር ተንቀጠቀጠች ልዑላኑ መሳፍንቱ ደነገጡ እግዚአብሔር ተቆጥቶባቸዋልና ሕዝቡም ታወኩ ከገጸ መዓቱ ከቁጣው የተነሳ እሳት ነደደ ጢሱም እስከ ሰማይ ደረሰ ሰማያትን ኦዘነበለ መዓት ወረደባቸው ልበ አምላክ ዳዊት የተናገረው ትንቢት ከነምሳሌው በፋርስ ከተማ ላይ ተፈጸመ መዝሙር ፲፰ ከቁጥር ፯-፲፱ ወዲያው ልኡላኑ መሳፍንቱ ሕዝብ ተሰብስበው ንጉሳቸው እንድርያኖስን ይህ መዓት የወረደብን እሳት ከሰማይ የነደደብን መስቀል ወደ ፋርስ በመግባቱ ነውና አሁንም መዓቱ ይመለስልን እሳቱም ይጠፋልን ዘንድ ይህንን ያመጣኸውን መስቀል መልሰህ ውሰድልን አሉት ንጉሡም ደንግጦ በጨለማ የቀበረውን መስቀል በጸሐይ አውጥቶ ብዙ ወርቅና ብር ገጸ በረከት ጨምር በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መልሶታል ። እምነው የተከተሉትም ምእመናን ብዙ ነበሩ መስቀል ለሁለተኛ ጊዜ ከሁለተኛው መቃብር የወጣበት ዕለት እንደ ቀድሞ መጋቢት ፲ ቀን ነው ። ለእግዚአብሔር አምላክ ክብር ምስጋና ይግባውና በዕውነትም ቅዱስ መስቀል የክርስቲያኖች መመኪያ መሆኑን ለጠላቶቹ ለፋርስ ሰዎች አረጋገጠላቸው መቸውንም ቢሆን ማለ ግብዞች ሰነፎች በልባቸው እግዚአብሔር የለም ማለትን እንደቁም ነገር አድርገው ይዘውታልና መናሩን አሳውቃቸው ። እንግዲህ ይህንን ታሪክ በጽሁፍ ለማቅረብ ያነሣሣን ሃይማኖታቸው የቀና ፫፻፲፰ ሊቃውንት በፍትሐ ነገሥት በአንቀጸ በዓላት በጌታ ስምንት በፍትሐ በወሰኗቸው ከዘጠኙ በዓላት አንዱ መስቀሉ የተገኘበት መጋቢት ፲ ቀን መሆኑን ለምእመናን ለማሳሰብ ነው ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ቀን በየዓመቱ በጸሎት ፣ በትምህርተ ወንጌል ፣ በማህሌት ፣ በቅዳሴ አክብራትውላለች እግዚአብሔር አምላክም የሚያከብሩትን ያከብራቸዋል የሚንቁትን የሚያቃልሉትን ግን በመለኮታዊ ባሕርይው ፈርዶ ይቀጣቸዋል ይልቁንም ለመስቀሉ የሚገባውን ክብር የማይሰጡትን በረከት ይነሳቸዋል ከመስቀሉ በረከት አሁንም እኛ ለመቀበል እንድንችል ከመምራን ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት በታዘዝነው መሠረት በዓለ መስቀሉን አክብረን በፍጹም ልቦናችን ወደ እሱ እንቅረብ ።

አለቃ ኤልያስ ነቢየ ልዑል

# ልትድን ትወዳለህን ?

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በነሳው ሥጋ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በምድር ላይ ይመላለስ በነበረ ጊዜ ልብሱን ዳሰው ቃሉን ሰምተው የተፈወሱት ብዙዎች ናቸው ። በኢየሩሳሌም በበጎች በር አጠገብ በእብራይስጥ ቤተ ሳይዳ የምትባል አንዲት መጠመቂያ ነበረች ለዚህች መጠመቂያ ሥፍራ አምስት መመላለሻ (እርከን) ነበራት ነህምያ ፫ ፩-፫ «እስመ ልአከ እግዚአብሔር በጊዜ ይወርድ ውስተ ምጥማቃት ይትሐወክ ማይ ወዘይወርድ ቀዲሙ ትምድህረ ሁከተ ማይ ዘይትሐጸብ የሐዮ እምኩሉ ደዌ ዘቦ»

በዚያች መጠመቂያም የእግዚአብሔር መልአክ በዓመት አንድ ጊዜ እየወረደ ውሃውን ሲእናውጸው ቀድሞ የገባ በሽተኛ ከአለበት ከማናቸውም ደዌ ይፈወስ ነበር ። መልአከ እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ ለቅድሶተ ማይና መስዋዕት ለማሳረግ ይወረድ ነበረና ነው ። በዚያች መጠመቂያ ቦታ የነበረው ውሃም መልአከ እግዚአብሔር እንደወረደ ለማጠየቅ ይናወጥ ነበር ።

«ወሀየ ይሰክቡ ብዙኃን ድውያን» በዚያች መጠመቂያ ሥፍራም በውሃው መናወጽ በየሳምንቱ አንድ ጊዜ የሚገኘውን ፈውስ ቀድሞ ከውሃው በመግባት ለማግኘት በመጠመቂያ ቦታ አጠገብ በእልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ የተያዙ ህሙማን ይኖሩ ነበር ከእነዚህም ሕሙማን መካከል ሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ ደዌ የጸናበት በሽተኛ ነበር ።

ወሐሎ እሐዱ ብእሲ ዘሠላሳ ወስምንቱ ክረምቱ እምዘ ደወየ ከታመመ ሠላሳ ስምንት ዓመት የሆነው በሽተኛ በዚያች መጠመቂያ ሥፍራ ይኖር ነበር በዚያችም መጠመቂያ ቦታ አጠገብ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያልፍ ያ ሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ ደዌ የጸናበት በሽተኛ በስምንት አንድ ጊዜ የሚደ[illegible] ገውን [illegible] ቦታ በአገኘው ጌታችን በሽተኛውን ባየ ጊዜ «ትፈቅድኑ ትህየው» ልትድን ትወዳለህን? አለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልትድን ትወዳለህን? ያለው በሽተኛው ለመዳን እደሚወድ ሳያውቅ ቀርቶ አይደለም እስፈቅዶ ለማድረግ ነው ።

አንድም አላዋቂ ሥጋን እንደተዋሀደ ለማጠየቅ ነው «እኮ ኢያእሚሮ ኀቡዓተ አላ ከመ የሐበነ መካነ ለጥንተ ትስብእቱ ዘኢየአምር» እንዲል በባሕርይ አምላክነቱ አወቅትኑ ብሎ ሥራውን አይተውምና እስ ፈቃድ ለማዶረግ ነው ።

ወአውሥአ ውእቱ ድውይ ወይቤሎ እዎ እግዚእ አላ ሰብእ አልብየ ከመ ሶበ ይትሐወክ ማይ ያውረዳኒ ውስተ ቀላይ» ድውዩም መለሰ ጌታ ሆይ ውሃው በተናወጠ ጊዜ በመጠመቂያይቱ ውስጥ የሚእኖረኝ ወገን የለኝም ነገር ግን እኔ ስመጣ ሳለሁ ሌላው ይወርዳል አለ ። ጌታችንም ሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ በደዌ ዳኛበአልጋ ቁራኛተ ይዞ የነበረውን ያን በሽተኛ ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለው በሽተኛውም ወዲያው ዳነ አልጋውንም ተሸክሞ ሄደ ዮሐ ፭ ፩-፱ ።

«ተነሥተህ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ» የሚለውን የኢትዮጵያ ሊቃውንት በትርጓሜያቸው ምሥጢር ሲአትቱ ምንት ይቀላል እምብሂለተ ሐድገ ለከ ሐጢአትከ ወእምብሂለ ተንሥእ ወንሣእ አራተከ ወሑር አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ከማለትና ሐጢአትህ ተሰርዮልሃል ከማለት የትኛው ይቀላል አላቸው ከመ ታእምሩ ከመብውህ ሎቱ ለወልደ እጓለ መሀያው ይህድግ ሐጢአተ በዲበ ምድር ለሰው ልጅ ለክርስቶስ በዚህ ዓለም ሐጢአት ማስተሥረይ እንዲቻለው ታውቁ ዘንድ ነው አላቸው ምነው ኃጢአት ከማስተሠረይ ድውይ መፈወስን ማበላለጡ ነው ሁሉስ የጌትነት ሥራ አይደለም ቢሉ ሐጢአት ሲሠረይ አይታይም ድውይ ሲፈወስ ይታያልና ሰውም ከአላየው በሚያየው ማድነቅ ልማድ ነውና ሰው በሚያደንቀው ተናገረ አንድም ኃጢአትህ ተሠረየችልህ ከማለትና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ከማለት ማን ይቀላል? ድውይ ሲፈውስ አይታችሁ ኃጢአት ያሥተሰርያል አትሉም አላቸው ሞተ ሥጋ ለሞተ ነፍስ ምልክት እንደሆነ ድህነተ ሥጋም ለድህነተ ነፍስ ምልክት ነውና በማለት ከዮሐ ፭ ፩-፱ ያለውንና ከማቴ ፱-፱ ያለውን በሐተታ በማገናዘብ እያመሰጠሩ ይተረጉሙታል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ የአልጋ ቁራኛ የደዌ እስረኛ የነበረውን በሽተኛ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ በማለት የምህረት ድምጽ በአሰማው ጊዜ በደዌ ብዛት የተጎሳቆለው ሰውነቱ የሚአገግምበት የሚጽናበት) ጊዜ እላስፈለገውም ወዲያውኑ አልጋውን ተሸክሞ ሄደ ተረፈ ደዌ አልተገኘበትምና የዚህ ዓለም በዐለ መድኃኒቶች የበሽተኛውን አካል መርምረው ያበጠውን እፍርጠው የተሰበረውን ጠግነው በጥበባቸው የሚፈውሱትን በሽተኛ ከተረፈ ደዌው የሚአገግምበት (የሚጠናከርበት) ረጅም የዕረፍት ጊዜ እንዲ ያሳልፍ ይመክሩታል እንጂ ደዌው በተሻለው ማግሥት ጠንካራ ሸክም እንዲሸከምና ብርቱ ሥራ እንዲሠራ አይፈቅዱለትም ።

የሕይወት ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሕይወት ምንጭ በሆነ ቃሉ ድነሃል አልጋህን ተሸክመህ ሂድ በማለት ለሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ ይማቅቅበት ከነበረው ደዌ የፈወሰው በሽተኛ በዚያችው በዳነባት ደቂቃ ለሁለት ጤናማ ሰዎች ሸክም የሚአስቸግረውን የብረት አልጋ ተሸክሞ ተጉዟል ። ምንዜጊም ቢሆን በዓለም ላይ የሚኖር ሰው ችግር እንደሚኖርበት የታወቀ ነው በሀብትም ይሁን በጤንነት ማጣት በሰዎች ዘንድ ችግር ይኖራል ከችግሩ ለመዳን እምነትና ትእግሥት ያስፈልጋል የሕይወት ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስንም ደጅ መጽናት ያስፈልጋል ልትድን ትወዳለህን የሚለው ጥያቄ ሁላችንን የሚመለከት ስለሆነ መልሳችን እዎ ልድን እወዳለሁ የሚል ከሆነ ለማዳን ሥልጣን ያለውን የክብር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በትምህርቱእንከተለው በግብሩም እንምሰለው ሕሙማነ ሥጋን በተአምራት ሕሙማነ ነፍስን በትምህርት ለፈወሰ የምህረትና የቸርነት ጌታ ለሆነው ለጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጋና ለእርሱ ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን ።

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ

# ጾመ ሕርቃል

ጾም ማለት በታወቀው ዕለትና በታወቀው ሰዓት ሰው ከምግብ የሚከለከልበት ወቅት ነው ። በታወቀው ዕለት ማለት በሰባቱ አጽዋም ሲሆን በታወቀው ሰዓት ማለት ደግሞ ዓርብና ረቡዕ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ፤ በጾመ ሕርቃል እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ፣ በዓቢይ ጾም ከቅድስት ሰኞ ጀምሮ እስከ ኒቆዲሞስ ዓርብ አሥራ አንድ ሰዓት ፣ ስሙነ ሕማማትን እስከ አሥራ ሦስት ሰዓት ከሌሊቱ አንድ ሰዓት ጨምሮ መጾም ነው ሲሉ ሊቃውንት በፍትሐ ነገሥት ገልጸውታል ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በአንድ ዓመት ውስጥ እንዲጾሙ ወስና ለምእመናን የምታስተምራቸው አጽዋማት ሰባት ናቸው ፣ እነሱም ጾመ ነቢያት ፣ ጾመ ነነዌ ፣ ዓቢይ ጾም ፣ ጾመ ረቡዕና ዓርብ ፣ ጾመ ሐዋርያት ፣ ጾመ ፍልሰታ ፣ ናቸው ፣ እነዚህን በዝርዝር የተገለጹትን አጽዋማት ስመ ክርስትና ሀብተ ውልድና ያለው ሰው ሁሉ መጾም



www.ethiopianorthodox.org

እንደሚገባው በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፲፭ ታገዛ ዛል ።

እንዲጸሙ ከታዘዙት አጽዋማት በተጨማሪ ሌሎች መናራቸው የታወቀ ነው ፤ "ወአጽዋምሰ ካልዓን እለ ተወሰኩ ላዕለ ዝንቱ ወተሠርዑ በቤተ ክርስቲያን ቅብጣዊት" ከእነዚህ ከተገለጹት አጽዋማት ተጨምረው በግብፅ ጉባኤ የተሠሩ ሌሎች አጽዋማት አሉ ። "ወእምኔሆሙ ዘይከውን በአምሳለ ጾም ዓቢይ በተጠናቅቆ" ከእኒህም እንደ ዓቢይ ጾም ጠንቅቀው ጠብቀው የሚጾሙት ጾም አለ" ወይዕቲ ሰ ሙነ ሕርቃል ዘትከውን እምቅድመ ጾም ዓቢይ" ይህችውም ከዓቢይ ጾም አስቀድማ የምትሆን ጾመ ሕርቃል ናት ይላል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ሰኞ ጀምሮ እስከ ዓርብ ኒቆዲሞስ ድረስ ከቆመ ሳያርፍ ከዘረጋ ሳያጥፍ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት ጹሟል ፤ ሐዋርያት እሁድ እሑድን አውጥተው ቢቆጥሩት ከ፶ ቀን ጉደለባቸው ፤ ለስብከተ ወንጌል ይፋጠኑ ነበርና ሳይዘጋጁት ኖልቁ ሐሳበ ብለው ሐደዋል ። የሚል ታሪክ ተጽፋል ። በሌላ ሀኩል ደግሞ በኢየሩሳሌም ፎቃ ፤ በሮም ሕርቃል ነግሠው ሳለ ፎቃ የተባለው ንጉሥ በኢየሩሳሌም በሚኖሩ ክርስቲያኖች ላይ መከራና ሥቃይ አጸናባቸው አንድ አካል ሁለት ባሕርይ በማለት ብንለ ያይም ወረደ ተወለደ በማለት አንድ ነንና እባክህ መጥተህ የሚያሰቃዩንን ጠላታችንን አጥፋልን እኛ ለአንተ እንገዛልሃለን ብለው ወደሮሙ ንጉሥ ሕርቃል ላኩበት ፤ እርሱም ከአይሁድ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ስለነበረው ነገሩን ቸል ብሎት ብዙ ጊዜ ቆዩ ፤ ከብዙ ጊዜ በኋላ ግን "ግዙራን ይነሥዕዋ ለመንግሥትከ" የተገዘሩ ወገኖች መንግሥትህን ይነጥቁሃል የሚል ራዕይ አየ ፤ ግዙራን የተባሉ ሌሎች እሉን ፤ አይሁድ አይደሉምን ፤ ብሎ ያንን የላካችሁብኝን ነገር አልረሳሁትም ፤ ነገር ግን ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው ነፍስ የገደለ ሰው እስከ ዕድሜ ልኩ ይጹም ብለው ሥርዓት ሠርተዋልና ጾሙን ስለፈራሁ ነው እንጂ ሲል ላከባቸው ።

በኢየሩሳሌም የነበሩ ምእመናንም የአንድ ሰው ዕድሜ ቢበዛ ሰባ ሰማንያ ነው ፤ ጠላታችንን አጥፋለን እንጂ ጾሙንስ እኛ ተካፍለን እንጾምልሃለን አሉት ፤ ሕርቃልም ከሀገሩ ሮም ገሥግሶ ወደ ኢየሩሳሌም ሂዶ ፎቃን አጠፋላቸው ፤ እነርሱም አምስት አምስት ቀን ተካፍለው ጹመውለታል ፤ ያላወቁት አንድ ጊዜ ጹመው ትተውታል ያወቁት ግን ቀድሞም ሐዋርያት ጹመውታል ብለው ሥርዓት አድርገው በዓመት በዓመት በዓቢይ ጾም መጀመሪያ ላይ የሚጾሙት ሁነዋል ።

ይህንን መሠረት በማድረግ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከጌታችን ከመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጾም የመጀመሪያውን ሳምንት ጾመ ሕርቃል በሚል ሥያሜ ሠይማ እንዲጾም አድርጋዋለች "ዘሰ አፈድፈደ ጾመ ይፈደፍድ ሎቱ እሤቱ' ከተወሰኑት ሰባቱ አጽዋማት አብዝቶ የጾመ ሰው ዋጋው ይበዛለታል ተብሎ እንደተጻፈው ማንኛውም ክርስቲያን ከተቻለው ከተወሰኑት አጽዋማት አብልጦ በመጾም ለበለጠ ትሩፋትና ክብር መሸቀዳደም ይኖርበታል ።

ከመነሻውም ላይ እንደተገለጸው እኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዎች የመጀመሪያውን ሳምንት ሰሙነ ሕርቃል በማለት ስንጾመው ፤ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ግን የመለማመጃ ሳምንት በማለት ዓይብ ፤ ዕንቁላል በመመገብ እንደሚያሳልፉት ታውቋል ፤ የእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን ጾምን ከጾም የሚያበላልጥ ሕግ የላትም ጾም ከሆነ ከማንኛውም የጥሉላት ምግብ መከልከል እንደሚገባ ታምናለች ፤ እምናም ለተከታዎቿ ምእመናን ታስተምራለች ።

በጾም የሚገኘው መንፈሳዊ ኃይል ከሁሉ የበለጠና እጅግ በጣም ከፍ ያለ ነው ፤ ሙሴ ፵ መዓልትና ፵ ሌሊት ጾሞ አሠርቱ ቃላትን ከእግዚአብሔር ተቀብሏል ፤ ነቢዩ ኤልያስም ፵ ቀን ከጾመ በኋላ በእሳት ሠረገላ ወደሰማይ አርጓል ፤ ዳንኤል ከአንበሳ አፍ ፤ ሶስና ከረበናት እጅ የዳነችው ዮዲት የወገኖቿን ጠላት የሆለሆርኒስን ቸብቸቦ ቆርጣ ወገኖቿን - - - - ከጥፋት ያዳነችው በጾም ኃይል ነው ።

ነገር ግን ከጾም ጋር አብረው ሊፈጸሙ የሚገባቸው ብዙ መንፈሳውያን ነገሮች አሉ ፤ ከእነርሱም ጥቂቶቹ ጸሎት ስግደት ፍቅር ሰላም አንድነት ትዕግሥት ምጽዋት ቸርነት ትሕትናና የመሳሰሉትም ናቸው ።

ጠላታችንን ድል ነሥተን የምንፈልገውን ለማግኘት የምንችለው በጾም በምናገኘው ኃይለ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ በሃይማኖታችን ጸንተን በፍቅርና በሰላም ሆነን መጾም ይገባናል ፤ ነቢዩ ኢዩኤል ስለ ጾም ዝግጅት ሲገልጽ "በጽዮን መለከትን ንፉ ፆምንም ቀድሱ ጉባኤውንም አውጁ" ብሏል ትንቢ ኢዩ ፤ ፪ ፤ ፲፭ ።

ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ዓይን ከፉ ነገርን ከማየት ይጹም ፤ አንደበት ከፉ ነገርን ከመናገር ፤ ጆሮም ክፉ ነገርን ከመስማት ይከልከል በማለት መጾም የሚገባው ከእህልና ከውኃ ብቻ አለመሆኑን ተናግሯል ፤ ይህ አብሮ አደግ ጋኔን ካልጾሙ ካልጸለዩ አይወጣም ብሎ ጌታችን እንዳስተማረን የከፋትንና የተንኮልን ተግባር ከሰውነታችን አስወጥተን ለማባረር በንጽሕና ሆነን መጾም ይገባናል ።

# ዐድዋና ቅዱስ ጊዮርጊስ

«ከረሀብ ጦር ይሻላል» የሚባል አነጋገር አለ ከድጥ ወደማጥ እንደማለት ያለ ነው ፤ ከችግር የሚብስ ችግር መኖሩን ለመግለጽ የሚነገር የጭንቀት ቋንቋ ነው በረሀብና በጦርነት መካከል አንዱ ከሌላው ይሻላል የሚያሰኝ በጎ ገጽታ የለም አለ ከተባለም ጦርነት በእሳቱ በስለቱ እልቂቱን ስለሚያፋጥንና ጊዜ ሳይፈጅ ከችግር መገላገሉ ይሆናል ። ረሐብ የሚፈጀው እያሰለሰለና እያመነመነ በሚፈነግለው ሰመመን ነው ። የረሀብ ክስተት በሰዎች መካከል ውሎ ካደረ ከተለመደው የምግብ ዓይነት አልፎ መሰል ፍጡርን እስከመመኘት ያደርሳል ።

ጦርነት ከአቤል እስከ ዛሬ በታለፈው ረጅም የታሪክ ሂደት ውስጥ በነደደው እሳት አያሌ የሰው ዘር ፈጅቷል ።

-ብዙ ስመ ጥር የነበሩ ሀገሮችን አውድሟል ። ከተሞቻቸውን አፍርሶአል ፤ ስፍር ቁጥር የሌለውና በአንዝ ተተምኖ ሊገለጽ የማይችል ሀብት ንብረት አውድሟል ፤ የብዙ አህጉርን የሥልጣኔ ጉዞ በጅምር አስቀርቷል ፤ ሥልጣኔአቸው በማበብ ፤ ጥበባቸው በማፍራት ላይ የነበሩትንም እንዳልነበሩ በማድረግ ታሪካቸውንና የታሪክ ቅርሳቸውን አፈር አልብሶአል ። ዛሬ በብዙ የዓለም ክፍሎች በአሸዋና በስሚንቶ ፤ በብረትና በድንጋይ ተቀጣጥለው የተሠሩ ሕንጻዎች የሚታዩባቸው ከተሞች ብዙዎች በጥንቱ ባህልና ሥልጣኔ መቃብር ላይ የተሠሩ ናቸው።

ጦርነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋና እየከፋ በመምጣቱ በአስቃቂ ጥፋቱ እልፍ አዕላፍ ሕጻናትን እናትና አባት አልባ አድርጎ ዘመዶታተን ዓለማትንን የድኅነት ፤ የሰምና አዳሪነትና ሰብአዊ ክብረ ኀሊና የረከሰባት የሐፍረት ገበያ አድርጓታል

ከእልቂት የተረፈውን ብዙ ቤተሰብና ኀብረተሰብ ለድህነት ፤ ለስደትና ለባይተወር ኑሮ እየዳረገ በሁለንተናዊ ገጽታው ፤ የሰው ዘር የጥፋት ምንጭ ሆኖ ቆይቷል ።

በሃይማኖት ትምህርትና በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አገላለጽ የመጀመሪያው ጦርነት በዓለመ መላእክት በቅዱሳን መላእክትና በሳጥናኤል (ዲያብሎስ) ሠራዊት መካከል የተካሄደው ጦርነት ነው ይህ ረቂቅ ጦርነት በዓይነቱ ምን ያህል ከባድና ፈታኝ እንደነበረ በኅሊና ሚዛን መገመት ያስቸግራል ። የጦር አበጋዞች በአንድ በኩል የመላእክት አለቃ ቅ/ሚካኤል ሲሆን በሌላው ግምባር ሰባት ራሶች ፤ አሥር ቀንዶች ያሉትና በጅራቱ ሲሦውን እጅ የሰማይ ከዋክብት ጠርጎ ሊያወርድ እንደሚችል የተጻፈለት ግዙፍ አውሬ ዲያብሎስ ነበር ፤ በዚህ ጦርነት የእግዚአብሔር ልጆችና የከፉ መን... ተከታዮች በእምነትና በክህደት ጉራ ተለይ...




የጀግናች አባቶቻችን የዐድዋው የድል መሪ ፍጡነ ረድኤት ቅዱስ ጊዮርጊስ

ተው የታወቁበት ሲሆን በመላእክት አሸናፊነት የተመታው አውሬ በእሳት ሰንሰለት ተይዞ ወደ ጥልቅ ጉድጓድ ተጥሏል ። (ራእ ፳ ፩-፫ ፤ ፯-፲) ።

በዓለመ መላእክት በእሳትና በነፋስ ክንፍ በሚበሩ ረቂቃንና መንፈሳውያን ኃይላትና በሠራዊተ ዲያብሎስ መካከል ከተፈጸመው ደረቅ ጦርነት ቀጥሎ የተከሠተው ኀጢአት በምኞት መስኮት ወደ ሰው ዘር በገባበት ጊዜ አብሮ የገባው ጦርነት ነው ። ይኸውም ጦርነት በራሱ ስልትና ጥበብ በሥጋክይሲ ተሰውሮ በቀረበው ሰይጣንና ለጦርነቱ ተመቻችቶ በተገኘው የሰው ልጅ አልጠግብ ባይ ኅሊና መካከል የተካሄደ ጦርነት ነው ።

ዛሬም የዓለምን ሕዝብ በመዋጋትና በማዋጋት የሚፈታተነው ይኸው ዓይነት ጦርነት ነው ። «በዘርህና በዘሯ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ» የተባለው መርገም በኃይለኛው ዘመን ከሴቲቱ ዘር በተገኘ መድኀን የተደመሰሰና የተወገደ ቢሆንም ዓለም ወደ በሚያመጣው ፈተና የምኞትና የኀጢአት ሥር እያቆጠቆጠ ጥላቻና በቀል ፤ ጦርነትና ደም መፋሰስ ከገጸ ምድር ሊወገድ አለመቻሉ ዘወትር በአሳዛኝ ሁኔታ የሚታይ ነው ።

በዚህ መልኩ ወደ ዓለም የገባው ጦርነት ቀስበቀስ መልኩን እየለወጠ ከአንድ አባት አብራክ የተገኙና ከአንዲት እናት ማኅጸን የተወለዱ መንትያ ወንድማማች ዓቢልና ቃየልን በማጋደል የደም ግፋስስን የጥፋት መሠረት አስቀምጦአል ። ወንድም ስለወንድሙ ሕይወትና ደህንነት ሲጠየቅ «እኔ የመሰል ወንድሙን ደም የሚሸፍን ሁሉ የወንድሜ ጠባቂ አይደለሁም» የሚል እፍራሽ

፲፩

www.ethiopianorthodox.org

መልስ ማቅረቡን እየተያያዘው መጣ ፡ ግላጋይና
ምስክር በሌለበት ሜዳ ታፍኖ የተገደለው የዓቤል
የደሙ ድምፅ በሕይወት ባለቤት ዘንድ ባሰማው
ክስና አቤቱታ ስለወንድሙ ደም የተጠየቀው ቃየ
ል» የወንድሜ ጠባቂ አይደለሁም» በማለት የመ
ለሰው የክህደት መልስ ለግፍ አድራጎት ዓምድና
ትምህርት ዛሬም በዓለም ላይ በስፋት ሲሠራበት
ይታያል ከዚህ የባሰ ጦርነት ሊኖር አይችልም
ዘፍ ፬ ፰-፱ ።

ከዚያ ወዲህ በቅዱስ መጽሐፍ በተከታታይ
ከተመዘገቡት አስከፊ ጦርነቶች አንዱ ኢየሩሳሌም
አካባቢ በታላቁ የዮርዳኖስ ወንዝ ትይዩ በደቡብ
ከሙት ባሕር እስከ አርሞንኤም ተራራ ፣ በሰሜን
እስከ ባሕረ ገሊላ ማዶ አሞራውያን በአሰቃቂ ሁኔታ
የተመቱበትና በአምስቱ ነገሥተ ሰዶምና በአራቱ
ነገሥተ ኮሎዶጎመር መካከል ሸለቆ የተደረገው
ጦርነት ነው ። የብዙ ሰው ሕይወት አልቆበታል ፣
ስፍር ቁጥር የሌለው ሀብትና ንብረት ወድሞበታል ፣
አዘኔታ የሌለበት ምርኮና ብዝበዛ ተካሄዶበታል
(ዘዳ ፪ ፳፮-፴፭) ።

ጦርና የጦርነት ሁኔታ በዚህ መልኩ እየቀ
ጠለ የጦር መሣሪያም ከተራ ድንጋይና ዱላ ዛሬ
ዓለም ወደሚጫወትባት የእሳት አሎሎ (ኑክሊየርና
ቦንምብ) ደረጃ ላይ ደርሶአል ። ፫ሺ ዓመት ከክርስ
ቶስ ልደት በፊት በጥንቱ ባቢሎን በኤፍራጥስ ወንዝ
አካባቢ ለም መሬት ላይ የነበሩ ሳምራውያን የተለ
ያየ ቅርጽና መጠን ያላቸው ሳንጃዎች ፣ ከርቀት ተስ
ፈንጥረው ነድፈው የሚገድሉ ፣ ቀስቶች ፣ ስለታም
መጥረቢያዎች ጦር ፣ ጋሻና ጎራዴ የመሳሰሉትን
የጦር መሣሪያዎች ሠርተው ትምህርቱ (ዕውቀቱ)
ወደ አካባቢ አገሮች ግብጽ ፣ ኑብያና ኢትዮጵያ
ድረስ እየተዛመተ ሲሠራና ሲሠራበት መቆየቱይወ
ሳል ።

በጥንቱ ዘመን የታሪክ ምዕራፎች የጦርነት
ነገር ሲወሳ በውነተኛው አምላክ እምነት በነበራ
ቸውና በሌሎች አማልክት ተከታዮች መካከል ይካ
ሄድ የነበረው ጦርነት ለሃይማኖት ሰዎች የተላለፈ
ትምህርት አለው ። ሕዝበ እግዚአብሔር የተባሉ
ቤተ እሥራኤል የእግዚአብሔርን ሕግ ጠብቀው
በሥርዓቱና በሕጉ በሚመሩበት ጊዜ በአመጽ የሚ
ነሳባቸው ጠላት አይኖርም ቢነሳም በተወሰነ ጥቂት
የሰው ቁጥር ብዙውን ይመቱታል ያሳድዱታል ።
ከፈጣሪያቸው ሕግና ትእዛዝ እየወጡ በራሳቸው
መንገድ በሚጓዙበት ጊዜ ኃይለ ረድኤት ስለሚነ
ሳቸው ለሽንፈት ይጋለጡ ነበር ። ስለሆነም
በእምነት አንጻር የቀድሞ ሰዎች በብዙ የጦርነት ታሪ
ኮች ውስጥ እንደሚነበበው በጠላት በሚወረሩ
ጊዜ ወይምወደጠላት ግምባር በሚዘምቱበት ጊዜ
አምላካቸውን በጸሎት ጠይቀው ብጽዓትና ስእለት
አድርገው በእምነት ተማጽነው ይዘምታሉ ። የእግ
ዚአብሔርም መንፈስ ስለሚያድርባቸውና ኃይል
ስለሚሰጣቸው ያስጥርጥር ድልን ይቀዳጃሉ ። «ጦር
ነት የኛ ኃይል የእግዚአብሔር» የሚል የእምነት
መፈክር የነበራቸው ሁሉ በዘመቱበት ጦር ግንባር
አፍረው አይመለሱም ፣ አሸንፈው እንጂ ተሸንፈው
አይገቡም ወደጠላት ጎራ አሻግረው ሲመለከቱና
በእግዚአብሔር ተማምነው ሲዘምቱ በልባቸው የሚ
ቀርጹት «ከሰናክሬም ጋር ያለው ሥጋዊ ኃይል ነው
ከኛ ጋር ያለው የሚረዳንና የሚዋጋልን እግዚአብ
ሔር ነው ። የሚለውን የፍጹም እምነት ቃል ነበር
(፪ ዜ መዋ ፴፪ ፰) ።

ብዙዎች የድል መፈክር ብቻ ሳይሆን የጦር
መሣሪያ አድርገው የተጠቀሙበት የእግዚአብሔ
ርን ኃይል ነው ። በተፋላሚዎቹ ተከቦ የተያዘውና
በብዙ እጥፍ የጠፍር መጫኛ የታሰረው ሶምሶን
ማሰሪያውን እሳት ውስጥ እንደገባ ፈትል እየበ
ጠሰ የጠላቶቹን ጭን በክፉ አመታት እየመታ
ጉልበታቸውን የሰበረው በአንድ የአህያ መንጋጋ
(አጥንት) አንድ ሺህ ሰው ያጠፋው በእግዚአብሔር
ኃይል ነበር (መሳ ፲፭ ፳፱-፴፫ ።

ብላቴናው ዳዊት በሱ አቅምና ጉልበት ይወ
ድቃል ተብሎ ያልተገመተውን ግዙፍ የጉልበተ
ሰው (ጎልያድን) በወንጭፍ ድንጋይ መትቶ የጣ
ለው « ከአንበሳና ከድብ አፍ ያዳነኝ እግዚአብሔር
ከዚህ ፍልስጥኤማዊ እጅ ያድነኛል» በሚል እም
ነት ተነሣስቶ እንደነበር ተጽፎአል ። (፩ ሳሙ ፲፯
፴፬-፶፬) ከዚህም ሁሉ ጋር ኃያላን ወደጦሩ ግንባር
ሲዘምቱ ትልቅ የኋላ ደጀን ይሆናቸው የነበረው
የካህናቱና የደካሞቱ ጸሎት ነበር ።

«ንጉሡ ሕዝቅያስና የአሞጽ ልጅ ነቢዩ ኢሳ
ይያስ ጸለዩ ፣ ወደሰማይም ጮሁ ፣ እግዚአብሔርም
ኃያላኑን ጠላቶቻቸውን የሚያጠፋ መልአክ ሰደደ
(፪ ዜ መ ፴፪ ፳-፳፪) ።

በሕዝቅያስና በሰናክሬም መካከል በተደረገው
ጦርነት ይህኑ የመሰለ የድል ሥራ ተሰርቶአል ።
« በዚያችም ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ ወጣ
ከአሞራውያን ሰፈር ፩፻፹፭ሺህ ገደለ ማለዳም በተ
ነሱ ጊዜ እነሆ ሁሉ በድኖች ነበሩ» (፪ ነገ ፲፱ ፴፭)

አስፈላጊም በሆነ ጊዜ የእግዚአብሔር የቃል
ኪዳን ታቦት ከጦር ኃያላኑ ጋር ይዘምታል ። የታ
ቦትም ዘመቻ ቅጥር ይንዳል አምባ (ምሽግ) ያፈ
ርሳል ፣ የጠላትን ግንባር ያሳፍራል (ኢያ ፯ ፱-፳፭)
በኢትዮጵያ ሀገራችንም በዐድዋ በተደረገው ዓይ
ነት የጦር አውድማዎች ታቦታት ዘምተዋልና ፣
የካህናትና የደካሞች ጸሎት ረድቷል ። እነ ቅ/ጊዮ
ርጊስን የመሰሉ የቅዱሳን ረድኤትም በጦሩ ሜዳ
ሥራ ሲሰሩ ታይቶ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔ
ርና ማኅደረ ቅዱሳን መሆኗ ተመስክሮአል ።

በኢትዮጵያ ምድር ዐድዋ ላይ ተሰንዝሮ የነ
በረው የኢጣሊያ ወረራ ቀደም ሲል በተለያየ ጊዜና



ዘኖጣሚ እየተሞከረ ሳይሳካ የቀረ አሰያም በኃያላኑ
ኢትዮጵያውያን አልበገሬነት የኀፍረት ሸማ እየተ
ከናነበ የተመለሰውን የምዕራባውያን ጦር ሽንፈት
ብድር ለመመለስ እንደሆነ የታሪክ ምስክሮች ይገ
ልጻሉ ።

የሀገራችን የመልክዓ ምድር አቀማመጥና የተ
ፈጥሮ ውበት እያስጐመዣቸው ፣ ከየጋራዎቿና ተራ
ሮቿ የሚነፍሰውን የሕይወት አየር እየተነፈሱ ፣
ከወንዞችና ዥረቶቿ የሚፈሰውን ቀዝቃዛ ውሀ እየ
ተጎነጩ ለመኖር አሻግረው የሚመለከቱት ብዙ
የቅርብና የሩቅ አገሮች ኢትዮጵያን በጦር ኃይል
አስገብሮ ለመያዝ የማይከጇል እየሆነባቸው ዐባይ
እንደጠማቸው ቀርቶአል ። ደፍረውና ገፍተው የመ
ጡም እንደተርብ በሚናደፉት የኢትዮጵያ ጀግኖች
ያላስተዋሉትና ያልገመቱት አደጋ እየደረባቸው
የእሳት ራት ፣ ሆነዋል ። በወታደርና የጦር ኃይል
ተሸንፎ መገበር ፣ መሸነፍና መልሶ ማሸነፍ የተለ
መደ የዓለም ኅብረተሰብ ጠባይ ቢሆንም በሐበሻ
ምድር ትልቁ ኀፍረት ለጠላት ተሸንፎ ማደር የበ
ታችነትን መቀበል ነው ። ይህ ለኢትዮጵያውያን
የማይዋጥ መራራ ነገር ነው ። ኢትዮጵያውያን ከሀ
ገራቸው ምድር ስንዝር የማይለቁ የሌለውንም የማ
ይሹ ናቸው ። እንኳን መሬቷን ቆርሰው ሊለቁ አፈ
ርና ትቢያ ከድንበራቸው ወጥቶ እንዳይሄድ የባዕ
ዳንን ጫማ እያራገፉ የሚሸኙ ናቸው ።

በአድዋው ጦርነት ወደ ኢትዮጵያ የመጣው
የወታደር ኃይልና የጦር መሣሪያ በዓይነት ፣ በብ
ዛትም ሆነ በጥራት ኢትዮጵያውያን ከነበራቸው
ጋር ፈጽሞ የማይመጣጠን ፣ በኃይል ሚዛንም ፈጽሞ
የማይቀራረብ ከመሆኑ ጋር ይህ የጦር ዝግጅት በሚ
ሊዮን የሚቆጠር የኢጣሊያ ሕዝብ በአንድ ልብ ፣
በአንድ ፈቃድ ሆኖ የመከረበትና የተስማማበት ፣
ጉዞው በዘመናዊ የጦር መሣሪያ ትጥቅና ስንቅ የተ
ደራጀ ኃይል የተንቀሳቀሰበት ፈጣንና በቀላሉ ይመ
ለሳል ተብሎ የማይገመት ነበር ።

ዳሩ ግን የኢትዮጵያውያን ኃይልና ጉልበት«አይ
ዞአችሁ አትደንግጡ ፣ ከነሱም አትፍሩ ፣ በፊታችሁ
የሚሄድ አምላካችሁ እግዚአብሔር ስለናንተ ይዋ
ጋል» (ዘዳ ፩ ፳፱) የሚለው እምነት ስለነበር በመ
ድፍና በመትረየስ ፣ በቦንብና በአውሮፕላን ተደራ
ጅቶ የመጣውን ኃይል ቀልጣፋው ኢትዮጵያዊ
ጀግና በሰይፍና በጉራዴ እያወራረደ መልሶታል ።

ወጣቱ ዳዊት በወገኖቹ እሥራኤል ላይ የት
ዕቢት ቃል ይናገርና ይገዳደር የነበረው ጉልያድን
በእግዚአብሔር ኃይል ሊያሳፍረው በተነሣ ጊዜ
ንጉሡ ሳኦል የራሱን የጦር ልብስ አልብሶ ከነ
ሐስ የተሰራ የራስ ቁር (ቦርበርቴ) ደፍቶለት ፣
ሰይፍም በወገቡ አስታ ጥቆት ነበር ።

ብላቴናው ዳዊት ግን ያለመደውን የጦር ልብስ
አውልቆ በበግ ጥበቃው ጊዜ አራዊትን ይመታበት
በነበረው መሣሪያው በመጠቀም በወንጭፍ ድንጋይ
ጎልያድን እንደጣለው፣በግዙፉ ሰው ወገብ የነበረው
ንም ሰይፍ ከሰገባው አውጥቶ ራሱን በመቁረጥ
ግዳይ እንደጣለ ሁሉ ፍጥነታቸው እንደነፋስ አነዳደ
ፋቸው እንደንብና ተርብ ቅልጥፍናቸው እንደጭ
ልፊት የሆነው ኢትዮጵያዊውያን በባሕርና በየብስ
ተጭኖ የመጣውን ዘመናዊ መሣሪያና የጦር ኃይል
ከምንም ሳይቆጥሩ የጦር እሳት ከነደደበት መስከ
በድፍረት በመግባት በጦርና በጎራዴ አጣድፈው
ታል፤ቆሞ መተመኮስን እንደውርደት የሚቆጥሩት
ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ከጠላት በቀሙት
መድፍ የጠላትን መድፍ በአፉ እያነጣጠሩ በመበ
ታተን አድዋ ላይ የፈጸሙት አኩሪ ተግባር
በቅኝ ግዛት ጨለማ ውስጥ ለነበረው የአፍ
ሪካ ክፍለ ዓለም የነጻነት ውጋጋን ሆኖአል ። ኢት
ዮጵያውያንም በዚህ ድል ኃይል የእግዚአብሔር
እንጂ የሰው አለመሆን በጦር መሣሪያና በሠራዊት
ብዛት የማይዳን መሆኑን አረጋግጠውበታል የኢት
ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በዕ
ለተ ቅ/ጊዮርጊስ ተጀምሮ በዕለተ ቅ/ጊዮርጊስ የተ
ፈጸመውን በውጊያውም ከኢትዮጵያውያን ወገን
የታላቁ ሰማዕት የቅ/ጊዮርጊስ ኃይል እንደነበረበት
የተመሰከረለትን የአድዋን የድል ቀን መታሰቢያ
በፍጹም የሃይማኖት ስሜት ስታዘክረው ትኖራለች

መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መም
ሪያ ኃላፊ

# ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አገራቸው ግብፅ
ልዩ ቦታቸው ንሂሳ ይባላል ። አባታቸው ስምዖን ፣
እናታቸው አቅሌስያ ናቸው ። አባትና እናታቸው የተ
ገኙት ከደጋጎች ምእመናን ነው ። ወላጆቻቸው እንደ
አያቶቻቸው በእግዚአብሔር ፊት ደጋጎች ነበሩ ።

የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እናት አቅሌስያ መካን
ሆና ልጅ ስለአጣች እያለቀሰች ሠላሳ ዓመት ኖረች
ንጽሕናን የሚወድ ልጅ ስጠኝ እያለች በሥዕለ
ሥላሴ ተማጸነች ።እግዚአብሔርም ክብሩ ከፍ ያለ
ልጅ እንቺ አላት ።
ከዚህ በኋላ አቅሌስያ በመጋቢት ፳፱ ቀን ጸነ
ሰች በታኅሣሥ ፳፱ ቀን ደም ግባቱ ያማረ ልጅ ወለ
ደች ። መልአኩ ቅ/ገብርኤልም በሰው አምሳል
መጥቶ የዚህ የልጅሽ ስሙ ገብረ መንፈስ ቅዱስ
ይሁን አላት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መልአክ እንደ አወጣ
ላቸው ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተብለው ተጠሩ ።
በዚያም ቀን ሕጻኑ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተነ



www.ethiopianorthodox.org



ለ፩፻፳፱ ዓመታት እህል ውሃ ያልቀመሱት ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

ሥተው ከእናታቸው ጭን ወርደው ለእግዚአብሔር ሦስት ጊዜ ሰገዱ ምስጋናም አቀረቡ ።

ከአምስት ዓመት በኋላ እግዚአብሔር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ሕጻኑን ከጉናቱ ከነጎድ ተቀበል ብዙ ገዳማውያን ወደ አሉበት ገዳም ውሰድና ከበራቸው አስቀምጠው አበምኔቱን (የገዳሙ አለቃ) ሕጻኑን ከበር አንስተህ ከአንተ ዘንድ አኑረው ስለ ልብሱ ስለ ምግቡ አታስብ ሕጻኑ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነውና ምግቡም መንፈሳዊ ነው ብለህ ንገረው ብሎ አዘዘው ። መልአኩም ሕጻኑን ወደ እግዚአብሔር አቅርቦ ከእግዚአብሔር ቡራኬ እንዲያገኙ አደረጋቸው ።

ከዚያም መልአኩ ከእግዚአብሔር እንደ ታዘዘው አባ ዘመደ ብርሃን ወደ ሚባል መምህር ዘንድ ወስዶ አስቀመጣቸውና ከዘመደ ብርሃን መዝሙረ ዳዊትንና ሌሎችን የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን እየተማሩ አደጉ ። ትምህርታቸውንም ከጨረሱ በኋላ አባ አብርሃም ከሚባሉ ጳጳስ ዲቁና ተሾሙ ። ከዚያም አመነኩሱዋቸውና የቅስና ሥልጣነ ክህነት ተቀበሉ በጾም በጸሎት በብዙ አገልግሎት ተወስነው በገዳም ብቻቸውን ኖሩ እንደ ሐዋርያት የተአምራትና የፈውስ ሀብት ተሰጣቸው ። ስለዚህም አጋንንትን ሲያወጡ ድውያንን ሲፈውሱ ለምጻሞችን ሲያነጹ መኖራቸው ተጽፎዋል ። በእግዚአብሔር ትእዛዝ በበረሀ ሲኖሩ ስድስት አንበሶችና ስድሳ ነምሮች አብረዋቸው ይኖሩ ነበር ።

አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዕድሜያቸው ፫፻ ዓመት ሲሆን ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ከተቀበሉ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሂድ በዚያ ከዓይን የምታወጣቸው ነፍሳት አሉ አላቸው ።

ከዚያም በኋላ ወደ ኢትዮጵያ መጡ ። በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል እየተመሩ ምድረ ከብድ ደረሱ ። ዳግመኛም ወደ ዝቋላ ሔዱ ወደ ባሕርም ተወርውረው ተዘቅዝቀው ቆመው አርባ ቀን በጸሎት ቆዩ «ስምህን የጠራውን መታሰቢያህን ያደረገውን እምርልሃለሁ የሚል ቃል ወደ አባታችን ወደ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ መጣ ። መላ ኢትዮጵያን ካልማርክልኝ ከዚህ ባሕር አልወጣም ብለው ለመልአኩ ነገሩት መልአኩም ከርሳቸው ዘንድ ሄዶ በኋላ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ በዚያ ባሕር ውስጥ ፲ ዓመት ኖሩ ። ከዚህ በኋላ ጌታችን ወደርሳቸው መጥቶ ከባሕር ዳር ቆመና» ተነሥ ውጣ መላ ኢትዮጵያን ምሬልሃለሁ» አላቸውና ወደ ምድረ ከብድ ላካቸው ። በዚያም ሰባት ዓመት ቆመውና ወደ ሰማይ አንጋጠው ሲጸልዩ ሰይጣን በቁራ ተመስሎ መጥቶ ዓይናቸውን አወጣውና አሳወራቸው ። ቅዱስ ሚካኤልና ቅ/ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልከው መጥተው በሁለቱም ዓይናቸው ላይ እፍ አሉባቸውና ዓይኖቻቸው እንደ ቀድሞው አዩ መላእክቱም ወደ ዝቋላ ሔደህ ጠላቶችህ አጋንንትን ተበቀል አሉዋቸውና ወደ ሰማይ ዐረጉ ። እርሳቸውም ወደ ዝቋላ ሲመለሱ እግዚአብሔር ለአብርሃም በመምሬ አጸድ በአንድነቱ ፣ በሦስትነቱ እንደተገለጠለት ለርሳቸውም ተገተጠላቸው (ዘፍ ፲፰ ፩—፭) በራእይም እስከ ሦስተኛው ሰማይ አወጣቸው ገነትንም አስጎበኛቸው ። በዝቋላም ሰባቱ ሊቃነ መላእክት እየረዱዋቸው ጠላቶቻቸው ሰይጣናትን በመበረቅ አጠፏቸው እንደገናም ወደ ምድረ ከብድ ተመልሰው በአራዊት መካከል ሆነው ሲጸልዩ መንፈስ ቅዱስ የጠራቸው ሦስት ቅዱሳን ወደርሳቸው መጡ ። እነዚህም የዋልድባው አባ ሳሙኤል ፣ የአዘሎው አባ አንበሳ ፣ ከላዕላይ ግብፅ የመጣው አባ ብንያም ናቸው ። በአንበሶቻቸው ተጭነው ወደ ምድረ ከብድ መጡ ። ለጊዜው አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ስለተሠወሩዋቸው ሰባት ቀን በሱባኤ ጸለዩ ከዚያም ተገናኝተው ሰላምታ ተለዋወጡ ። ከእነዚያም እንግዶች ጋር ከተሰነባበቱ በኋላ መንፈስ አነሳስቶአቸው ክርስቶስን የካዱ ሰዎች ወደ አሉበት ወደ ምዕራብ ሀገር ሔዱ ከዚያም ጣዖት አምላኪው ንጉሥ በተአምራት አጋንንት ያደሩባቸውን ጣዖታት ስለ ሰበሩበትና አጋንንቱም ስለጠፉ እንደ ሠለስቱ ደቂቅ በነደደ እሳት ውስጥ እንዲጣሉ አደረጋቸው እሳቱም ውሀ ሆነላቸው እንደገና ከሐዲው ንጉሥ አባታችንን አንገታቸውን በሰይፍ ሊቆርጣቸው ሲቃጣ መብረቅ ከሰማይ ወርዶ ንጉሡን ከነሠራዊቱ አጠፋቸው ። አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ከዚያ ሔደው እግራቸውን በገመድ አሥረው በገደል ላይ ቁልቁል ተሰቀሉ ሰይጣን መጥቶ ያችን ገመድ ቆረጣት አባታችንም ወደ ታች ወደቁ ። ቅዱስ ሚካኤል ያዛቸውና በራሳቸው ቆመው ስለእነዚያ ከሐዲዎች ነፍሳት መጸለይ ቀጠሉ በጥርሳቸው ድንጋይ ነክሰው እስከ ሠላሳ ዓመት ኖሩ ። ብዙ ገድልን ተጋደሉ ።

ከሠላሳ ዓመት በኋላ ጌታችን ሰባቱን ሊቃነ መላእክት አስከትሎ እናቱን ቅድስት ድንግል ማርያምን ጨምሮ መጣና ጠራቸው ። አቤት ጌታዬ አሉት እሱም እነዚያን ከሐዲዎች ምሬልሃለሁ በአላቸው ጊዜ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የነከሱትን ድንጋይ ጣሉ ጥርሳቸው ግን ተነቅሎ በድንጋይ ላይ እንደ ተተከለ ቀረ ። በኋላ ግን ተመልሶላቸዋል ከዚያ ወደ ዓረብ ሀገር ሔደው ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ሥልጣን በከሐዲዎቹ ዐጽም ላይ ጸልየው ሙታኑን አስነሱዋቸው ሃይማኖትንም አስተማሩዋቸው እነሱም አምነው ተጠምቀው ክርስቲያን ሆኑ ።

አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ከአባ ፍሬ ቅዱስና ከአባ ብንያም ጋር ከኢትዮጵያ ወደ ዐረብ ፣ ከዐረብ ወደ ኢትዮጵያ እየተመላለሱ በምድረ ከብድና በሌሎችም ገዳማት እየተዘዋወሩ ኢትዮጵያን በአራቱም ማዕዘን እየባረኩና እግዚአብሔርን እያመሰገኑ በጸሎታቸው ተአምራት እያደረጉ ለኢትዮጵያ በረከት እያደሉ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር እያስታረቁ ቆዩ ።

አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ምድራዊ ህብስትንና ምድራዊ መጠጥን ሳይቀምሱ ሴት የፈተለችውን ሳይለብሱ አስቀድመው ሰማያዊ ኅብስት መላእክት እያመጡላቸው ሲመገቡ ከኖሩ በኋላ ከገነት የሚላክላቸውን ሰባት ሰባት የእንጨት ፍሬ ይመገቡ ነበር ። ልብሳቸውም የአንበሳ ጋማ የመሰለ ከራሳቸው እስከ ጥፍራቸው የሚሸፍናቸው ፀጉር እንደነበር በሥእላቸው ይታያል ። ለመኖሪያቸውም ዋሻ ወይም ቤት አልነበራቸውም ከገዳም ወደ ገዳም ከአድባራት ወደ አድባራት ማለት ዱር ለዱር ጫካ ለጫካ በመዘዋወር ከአራዊት ጋር ኖሩ እንጂ ።

አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በገድላቸው እንደተጻፈው የኢትዮጵያ ብርሃን የኢትዮጵያ ፀሐይ የኢትዮጵያ የአጥቢያ ኮከብ የሚል በኢትዮጵያ ላይ ያደረጉትን ምግባረ ሠናይና ትምህርተ እግዚአብሔር የሚያንፀባርቅ ስም አላቸው ።

ጻድቁ አባታችን በዓመት ሦስት ጊዜ ማለት ለልደት ለጥምቀት ለስቅለትና ትንሣኤ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄዱ በጌታችን መቃብር በጎልጎታ እየሰገዱና እየጸለዩ ይመለሱ ነበር በጎልጎታ በሚያደርጉት ጸሎት ለኢትዮጵያ ሰዎች ሥርየተ ኃጢአትንና ምህረትን በመለመን አጥብቀው ይማጸኑ እንደነበር ተጽፎአል ።

አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በሚቀድሱበት ጊዜ ፍሬ ቅዱሳን ተራዳኢ ካህን ፣ ዘርዐ ቡሩክን ዲያቆን ፣ አድርገው በሦስት ይቀድሱ እንደነበር በገድላቸው ተጽፎ ይነበባል ።

ብፁዕ አባታችን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የዕረፍታቸው ጊዜ ሲደርስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾ «የለመንኸኝን ሁሉ አደርግልሀለሁ ፣ ከእናትህ ማኅጸን ጀምሮ የመረጥሁህ እኔ ነኝ ቃል ኪዳኔንም ከአንተ ጋር አቆማለሁ እስከ አሁን ለምነኸኝ የከለከልኩህ ነገር የለም ሁሉንም ፈጽሜልሃለሁ አሁንም የምትጠይቀኝን ሁሉ አደርግልሃለሁ ይህን ያህል ዘመን ድካምን ችግርንና ፈተናን ታግሰህ በእኔ ስም ገድልህን ፈጽመሃልና አላቸው ። ጻድቁም እስከ አሁን የለመኑትን ሁሉ እንደፈጸመላቸው ጠቅሰው ምስጋና በማቅረብ ከዚህ ዓለም ሥጋ በሞት ከተለየሁ በኋላ ስሜ ተደብቆ እንዳይቀር አድርግልኝ በዓለሙ ሁሉ ሥራዬን ገድሌ ይታወቅ አንተ ሥራዬን ከአልገለጥህልኝ ግን መታሰቢያዬን ያድርግልኛል ? የሰጠኸኝ ቃል ኪዳን ሁሉ የታወቀ ይሁንልኝ በስሜ ለድሆች ለጦም አዳሪዎች ለሙት ልጆች ጠዋሪ ለሌላቸው ሽማግሌዎች ምጽዋት በመስጠት ለጦም አዳሪዎች በማብላት በማጠጣት መታሰቢያዬን ያጸፉትን ሁሉ ማርልኝ ሥርየተ ኃጢአትን ስጥልኝ አሉት ጌታም በራሱ በመማል ስምህን የጠራውን ያስጠራውን ፣ መታሰቢያህን ያደረገውን በጸሎትህ በአማላጅነትህ የታመመውን እምርልሃለሁ ገድልህን ያጻፈውን ሳይጠራጠር በፍጹም ልብ አምኖ ሲነበብ የሰማውን እኔ ስሙን በመጽሐፈ ሕይወት እጽፍለታለሁ መታሰቢያህ በሚደረግበት ቀን ለቤተ ክርስቲያን ስንዴና ወይን ለመሥዋዕት ፣ ቅብአ ዘይት ፣ ጡዋፍ ሻማ ለመብራት ፣ ዕጣን ለማዕጠንት መባዕ አድርጎ የሰጠውን ኃጢአቱን እደመስስለታለሁ ፹ ዓመት እስከሚፈጸም ድረስ በምስሐ ደብረ ጽዮን አስቀምጠዋለሁ (ራዕ ፳ ፩-፯) ለድሆችና ለጦም አዳሪዎች የሚራራውን የተራበውን የሚያበላውን የተጠማውን የሚያጠጣውን በምስሐ ደብረ ጽዮን ከአንተ ጋር ሺ ዓመት አስቀምጠዋለሁ ከአንተም ጋር በመንግሥተ ሰማያት የሕይወት እንጀራ ይበላል ። በስምህ የተራቆተውን ያለበሰውን ለተቸገረው የራራለትን ፣ ያዘነውን ያረጋጋውን የተጨነቀውን ያስደሰተ በመታሰቢያህ ቀን ይህን የመሰለውን መልካም ሥራ ያደረገውን ሁሉ የቀደመውን ኃጢአቱን አላስብበትም የዕዳውን ደብዳቤ እፍቅለታለሁ እንደ አልበደለም ንጹሀ አደርገዋለሁ ሲል ቃል ኪዳኑን ከአጸናላቸው በኋላ ተሰወረ ።

አባታችንም ይህን ቃል ኪዳን በገዳመ ዝቋላ ከተቀበሉ በኋላ ወደ ምድረ ከብድ ሔዱ ምድረ ከብድ ላሉ መነኩሳት ሁሉ ጊዜ ሞታቸው እንደቀረበ ነገሩአቸው ። መጋቢት ፫ ቀኔ ዓርብ ታመሙ በዚህም ጊዜ ፍሬ ቅዱስና ዘርዐ ብሩክ ያዕቆብና ብንያም ዮሴፍና ሌሎችም ብዙ ባሕታውያን ወደርሳቸው ቀረቡ ቀዳሚት በማግሥቱ ድካም እየተሰማቸው ወዛቸው ላባቸው እየበዛ ዋሉ ። ሲመሽ መናገር እየተሳናቸው ሔደ ገብረ እንድርያስ የተባለው ለሞታቸው ምስክር እንዲሆን ለጊዜው አልነበረምና ሔደው ከአለበት ጠርተው አመጡት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚት ማታ ለእሑድ አጥቢያ መጋቢት ፭ ቀን ከሌሊቱ ፯ ሰዓት ሲሆን ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተለየች ። በዚህም ጊዜ እንደ ነጎድጓድ ያለ ድምፅ ከሰማይ ተሰማ ጌታችንም ወደ አባታችን ወረደ ዳግመኛም ለአቀባበሉ እንደ በረዶ ነጭ የሆነ ሻማ ከሰማይ ወደ ምድርም እንደ ወንጭፍ ድንጊያ ወረወረ እንደ ፀሐይ በራ ምድር ተንቀጠቀጠች ባሕታውያኑ ሁሉ ስለፈሩ ሥጋቸውን ለመገነዝ ችላ አሉ ነገሩ የገባቸው ግን ይህ ሁሉ የሆነ ስለ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ክብር መሆኑን ተገንዝበው አደነቁ ።

ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወዳጄ ሰላም ለአንተ ይሁን አላቸው በሕይወት ሳሉ የሰጣ



www.ethiopianorthodox.org

ቸውንም ቃል ኪዳን አጸናላቸው ነፍስህ ከሥጋህ ከተለየችበት ከመጋቢት ፭ ቀን ጀምሮ መታሰቢያህን ያድርጉ አሁንም ወደ ሰማይ ከፀሐይ ሰባት እጅ ወደ ሚያበራ ወደ ብርሃን ቤት ውጣ እነሆ አሥራ፤ሁሉት አክሊላት ሰጥቼሃለሁ አላቸው ። ።

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ሚካኤል ሦስት አክሊል
ቅዱስ ገብኤል ሦስት አክሊል
ሱራፌልም ሦስት አክሊል
ኪሩቤልም ሦስት አክሊል ሰጡዋቸው ።

ዳግመኛም እነሆ መብራት ሰጥቼሃለሁ ። አንድ መቶ ሺ በቀኝህ ፤ መቶ ሺ በግራህ ፤ መቶ ሺህ በፊትህ መቶ ሺ በኋላህ ይብራ አላቸው እያንዳንዱ ብርሃን ከፀሐይ ዕጥፍ የ ሚያበራ ነው ።

ከዚህ ሌላ የብርሃን ድባብ ሰጥቼሃለሁ መቶ ሺ በቀኝህ ፤ መቶ ሺ በግራህ ፤ መቶ ሺ በፊትህ ፤ መቶ ሺ በኋላህ ፤ ይሁኑልህ አላቸው የየአንዳንዱም የድባብ ብርሃን ከፀሐይ ብርሃን ዕጥፍ የሚያበራ ነው ። አምስት መቶ ስልሳ ሁለት ዓመትም ያለ ልብስ ራቁትህን ስለኖርህ የብርሃንን ልብስ እነሆ ሰጥቼሃለሁ አላቸው

አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ጌታችንን አቤቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድ ሳታስቀር በሙሉ ማራቸው አሉት ። ጌታችንም ለአባታችን እነሆ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ አሥራት እንዲሆኑህ ሰጥቼሃለሁ እንደ ወደድህ ለአንተ ይሁኑህ መታሰቢያህን ያድርጉ በጸሎትህ በአማላጅነትህ ይታመኑ ደስ ብሎዋቸው ለዘለዓለም ይኑሩ አላቸው ።

በጻድቁ ሰው ጸሎት ሀገር ትጸናለች እንጂ አትጠፋም ። ሐዋርያው ያዕቆብ እንደ ተናገረ የጻድቅ ጸሎቱ ግዳጅ ትፈጽማለችና ። (ያዕ ፭ ፲፮)

ያን ጊዜ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዳ ስ ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተለየች ጌታችንም ተቀብሎ ሰማት ደስ ታንም መላት ።

ለምስክርነት የቆሙና ያዩ ቅዱሳን ገዳማያን በዚያች ሌሊት ድንቅ ነገር አዩ ሰማያት ሲከፈቱ መላእክት ከሠራዊታቸው ጋር የቅዱሱ ሥጋ ወደ አለበት እየተጨናነቁና እየተጋፉ ሲወርዱ አዩ ዳግመኛም አባታችን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ሰባቱ ሊቃነ መላእክት ውረዱ ለቅሶ ኀዘን ወደ ለሌባቸው ወደ ብርሃን ቤቶች ታስገቡት ዘንድ የሚል ቃል ሰሙ ።

ከዚህም ሌላ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን በድን አንስታችሁ ወደ ኢየሩሳሌም ውሰዱ መቃብሩም ከመሠዊያው በስተቀኝ በኩል ይሁን የሚል ቃል ሰሙ ። ሌሎች የመላእክት አለቆችም የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በድን በአለበት በስተቀኝ ቆሙ በንጸሕት ነፍሳቸው ፊት ዕልልታና ምስጋና እያደረጉ እንደ ውሀ ፏፏቴ መቋረጥ በሌለበት ልዩ ልዩ ምስጋና አመሰገኑ ሥርዓቱ ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ በድናቸውን መላእክት ሊቀብሩት እግዚአብሔር ወደ አዘዘበት ቦታ ወሰዱት ።

እግዚአብሔር ያዘዘው ሁሉ በተፈጸመ ጊዜ እነዚያ መላእክት በምስጋና በክብር በዕልልታ ነፍሳቸውን ወደ ብርሃን አዳራሽ አስገቡዋት በመላእክት ማኅበርም ውስጥ በሰማይ ፍጹም ደስታ ሆነ ።

ሰውን ለወደደ ለእግዚአብሔርም እስከ ዘለዓለሙ ድረስ ምስጋና ይሁን እያሉ አመሰገኑ ።

### አንባብያን

የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በዓል በየ ዓመቱ ፫ ጊዜ የሚከበረውና መታሰቢያ የሚደረግላቸው ይህን ታሪክ በተከተለ ሁኔታ ነው ።

፫ ጊዜ የተባለው ታኅሣሥ ፳፱ ወይም ጥር ፭ ቀን ልደታቸው መጋቢት ፭ ቀን ዕረፍታቸው ፤ ጥቅምት ፭ ቀን ቃለ ኪዳን የተቀበሉበት ወይም የመጋቢት ፭ ቀን ለውጥ ነው ። ለውጥነቱም መጋቢት ፭ ቀን በወርኀ ጾም ስለሚውልና ይባቤ ስለማይደረግ ለውጡን ጥቅምት ፭ ቀን በይባቤና በደስታ ለማክበር መሆኑን ገድላቸው ይናገራል ።

ከተሰጣቸው ቃለ ኪዳን እንደተረዳነው በጻድቁ በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ስም ለቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳትን አልባሳትን መጻሕፍትን ገዝተን ብንሰጥ ዕጣን ለማዕጠንት ፤ ስንዴ ፤ ወይን (ዘቢብ) ለሙሥዋዕት ፤ ጡዋፍ ሻማ ዘይት ለመብራት ስናገባ ለነዳያንና ለጦም አዳሪዎች መርጃ የሚሆን ድርጅት በየቤተ ክርስቲያኑ ብናቋቁምና ብንረዳ በጻድቁ አማላጅነት በእግዚአብሔር ቸርነት ምሕረት ፤ ሥርየተ ኃጢአት እናገኛለን ።

ከጻድቁ ረድኤትና በረከት ይከፈለን አሜን ።

ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ
የሰዋሰወ ብርሃን ቅ/ጳውሎስ ከ/መ/ት/ቤት ም/ ዲን

# ከነነዌ የምንማረው

ከመልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁን

- ዮናስ ማለት ርግብ የዋህ ማለት ነው ። ይህ ስም በማንም ላይ ጉዳት የማድረስ ጠባይ የሌላቸውና (የማይገባቸው) ፤

- በሰዎች ኃጢአትና በደል ፤

የሚያዝኑና የሚያለቅሱ የእግዚአብሔር ወዳጆችና እንደርግብ የዋህ የሆኑ ነቢያት ሁሉ የሚጠሩበት ስም ነው "ዮናስ" የሚለው ስም ፍችውና ትርጉ ም የገባቸው ሰዎች ልጆቻቸውን በዚህ ስም ለመጥራት "ዮናስ" ብለው ይሰይማሉ ።

- የዮናስ መጽሐፍ ቊጥሩ ከነቢያት ይሁን እንጂ ታሪካዊ ነው ከዓርባ ቀን በኋላ ነነዌ ትገለበጣለች ከሚለው በስተቀር ሌላው የሀገሪቱን ጥፋት የሕዝቡን በደል የእግዚአብሔርን ትዕግሥትና ቁጣ የነቢዩን ተልእኮና የትንቢታዊ ዘመቻውን ውጤት የሚገልጽ ትረካ ነው ።

- ዮናስ በእግዚአብሔር መንፈስ የተቃኘ የዛብሎን ነገድ የምትሆን በምድረ እሥራኤል ሜፍ በምትገኝ አንዲት የገሊላ ክፍል የተወለደ በኢዮር ብዓም ዘመን ለነነዌ ሕዝብ ምህረት የተጠራ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው ። ይህ ታሪክ አስደናቂ የሆኑ የሰውን ልጆች የደካማነት ጠባዮች ለተከታታይ ትውልድ ትምህርት እንዲሆኑ በምሳሌነት ዘግቦአል ። በንስሐ የሚመለሱ ኃጢአተኞች ከእግዚአብሔር የሚያገኙትን ይቅርታ ይገልጻል ። ነነዌ ምስክር ናት ።

- ነነዌ የአሞራውያን መንግሥት መዲና ነበረች (ዘፍ ፤ ፲ ፤ ፲፩) በወቅቱ በሕዝብ ብዛት በሥልጣን በአካባቢ የበላይነት ታላቅ ነበረች በአንድ ወቅት የዚችን መሬት (የመላውን ዓለም) ነገሥታት ገዝታለች የተባለበትም ጊዜ ነበር ። አዎ ታላላቅ አገሮች እንዲሁም ታላላቅ ሰዎች ከእግዚአብሔር ሥልጣን (ቊጥጥር) ውጭ ባለመሆናቸው ታላቅነቷ የትም አላደረሳትም ። እውነተኛው አምላክና አምልኮቱ የማይታወቅባት ሀገረ አሕዛብ ነበረች ። ከአምልኮተ እግዚአብሔር ተራቁታ አመጽና በደል የተመላባት ፤

- ዮናስ የተባለው በእግዚአብሔር ፊት የደረሰውንና በነነዌ የተጠራቀመ የኃጢአት ክምር ለመናድ ፤ ሕዝቡ ወደ ንስሐ እንዲመለስ ለመምህና በንስሐ ባይመለሱ የሚደርሰውን ጥፋት ለመንገር ለማስጠንቀቅ ነው ። የዋሁ ዮናስ የእግዚአብሔርን መልእክት ወደ ታዘዘበት አገር በቀጥታ በማድረስ ፈንታ ከእግዚአብሔር ፊት ለማምለጥ ምንም የባህር ወደብ ግንኙነት ወደሌላት ምናልባትም የእግዚአብሔር ሥልጣን (ሀይን) ሊደርስባት አይችልም ብሎ ወዳሰበባት ተርሴስ ወደምትባል አገር ኮበለለ በምድረ እሥራኤል ታዋቂ ወደሆነች "ጃፓ ወደ ምትባል የባህር ወደብ ሸሸ ።

- ዮናስን ለመመለስና ተልእኮውን እንዲያስታውስ አስፈሪ ማዕበል ከኋላ ተላከ ወደ ጥፋት ዓለም ሰፊ መንገድ ይዘን ማዕበልና ጐርፍ የመላበት ጉዞ ስንጓዝ አቅጣጫ መሳታችንን ገልጾ የሚመልስ ጥሪ ምንኛ መታደል ነው ።

መርከበኞቹ ምንም እንኳ በሥራ ጠባያቸው የዚህ ዓይነቱ ችግር እየገጠማቸው የለመዱት ቢሆንም የዚያ ዕለት ቁጣ በልዩ ሁኔታ አስፈርቶ አቸውተጨንቀዋል ። ዮናስ ምንነቱን ፤ ማንነቱን ረስቷል ። ሁሉ ወደ የአምላኩ እንዲጮህ ታዞ ጮኸ ጸሎት የሚለመደው በጭንቅ ጊዜ ነው ችግር ካልደረሰ ብዙዎች ጸሎት የሚያስፈልግ አይመስላቸውም ፤ ስንቸገር ህልዎተ እግዚአብሔር ይታወቃል ስንጨነቅ አዳኝ እንሻለን ፤ ድህነታችን ይሰማናል። ችግራችን እንዲወገድ በምንጠይቅበትም ጊዜ አፋጣኝ መልስ ካላገኘን ተስፋ ከመቁረጥ እንደርሳለን በፈጣሪ ህልውና ውስጥ ገብተን በማንጎራጎርና እግዚአብሔርን በማሳዘን ሕይወታችንን ወደ ባሰ ጨለማ ውስጥ እንጥላለን (ግብ ፤ ሐ ፤ ፳፯-፲፰-፲፱፤ ፴፱) ።

ክብደት ለመቀነስ ብዙ ዕቃ እያወጡ ወደ ባሕር ጣሉ ፤ ዮናስ ከመርከቡ እንቅስቃሰ የሚሰማው ሁከትና ጩኸት ወይም በራሱ ሕሊና ወ ስጥ የሚደውለው የአመጽ ድምፅ አልተሰማውም ፤ ከእግዚአብሔር ለመኰብለል ያነሳሳው የበደል ስሜት አላነቃውም በጥልቅ እንቅልፍ ላይ ነበር መርከቢቱ ታውካለች በሰው በደል መልሀቋ ተጨንቋል፤ በኃጢአት ማዕበል ውስጥ ተኝቶ ወደ ጥፋት ዓለም የሚሄድ ሰውም እንዲዚሁ ነው ።

- በመርከቡ ውስጥ የነበሩት ሁሉ እንደየ አምልኮታቸው ወደ የአምላካቸው ሲጮሁ እሱ ብቻ ተለይቶ በእንቅልፍ ውስጥ በመሆኑ የመርከቡ መሪ ለጸሎት እንዲነቃ ቀሰቀሰው « - - አንዲት ሰዓት እንኳ ከኔ ጋር ልትተጉ አልቻላችሁም? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ጸልዩ" የሚለውን ኃይለ ቃል አስታወሰው ። ዮናስን የቀሰቀሰው በሕይወት ለመትረፍ ብቻ ሳይሆን በመርከቡ ላይ የደረሰው ሁከትና መናወጥ ከባድ ነበርና ሞትንም ነቅቶ እንዲጠብቅ ነበር ።

- ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ከነበረበት ዓሣ በእግዚአብሔር ሥልጣን ወጥቶ ወደተላከበት አገር መድረሱን አውቆ ወደነነዌ ከተማ የአንድ ቀን ጉዞ ዘልቆ በመግባት የታዘዘውን ፈጸመ ። ከእግዚአብሔር እንደተነገረው ነነዌ ከበደሏ ባትመለስ በኃጢአቷም ተጸጽታ በነቢዩ ቃል ንስሐ ባትገባ በሦስት ቀን ውስጥ ትጠፋለች በማለት አወጀ በታላቅ ድምፅ አሰምቶ ተናገረ ቃሉ ሰሚ አገኘ ሕዝቡም ከመሪዎች እስከ ተራው ሰው የነቢዩን ዐዋጅ ተቀብለው ጊዜ ሳይሰጡ ለንስሐ ተዘጋጁ የጾም ፤ የጸሎትና የንስሐ ጊዜ ወሰኑ ፤ ከሰው እስከ እንስሳ፤ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ያለው የከተማው ተንቀሳቃሽ ፍጥረት ሁሉ ከመብል ከመጠጥ ተከለከለ እግዚአብሔርም የሕዝቡን ታዛዥነት ንስሐና ኀዘን ተመለከተ ቁጣውንም በምህረቱ መለሰ ይህ ግን ዮናስን አላስደሰተውም ። ይልቁንም ተቆጣ እስከ ሞትም ድረስ አዘነ በዮናስና በእግዚአብሔር መካከል የቀጠለው ይህ የፈተና ጊዜ ሰው ለመሆር ሰው ያለውን የተፈጥሮ አመለካከት ና እግዚአብሔር በአርአያውና በምሳሌው ለፈጠረው ሰው ያለውን ርኅራሔ የሚያስገነዝብ የጥናት ውጤት ነበር ። ዮናስ ከእግዚአብሔር ይሸሻል እግዚአብሔር ግን ዮናስን እየተከተለ ያስተምራል ። ከእግዚአብሔር የሚገኘውን ትምህርት በትዕግሥትና በማስተዋል የሚቀበል ሁሉ የማያልፈው ፈተና አይኖርም ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስ ለበደል ሥራ የተባበረውንና በእግዚአብሔር ላይ ያመጸውን ሕዝብ ለሙቀጣት ዝናም እንዳይዘንም ለማድረግ የተሰጠውን



www.ethiopianorthodox.org

ሥልጣን ተጠቅሞ የሰማይን ፣ መስኮት ዘግቶ እሱ
በተደበቀበት ዋሻ ከእግዚአብሔር የታዘዘለትን
ምግብ እየተመገበና የኮራትን ወንዝ ውሀ እየጠጣ
በፍጥረት ላይ የደረሰውን ችግር ረሀብና ጥምን
በራሱ እንዲፈትነው በማድረግ አስተማረው ረሀብ
ምንድነው ? ያለ ንጉሥ ሰሎሞንንም የረሀብን ምን
ነት ያስተማረው ረሀብን እንዲቀምሰው በማድረግ
ነበር ዮናስም ላልተከላት ላላበቀላትና ውሀ ላላጠ
ጣት የተክል (ቅጠል) እንዲራራ በማድረግ ለነነዌ
ሕዝብ የነበረውን የጥፋት ውሳኔ እንደገና
እንዲመረምርና ለመጨረሻ ጊዜ ተምሮ የአመለ
ካከት አትጣጫውን እንዲለውጥ አድርጎታል ።
የነነዌ ሕዝብ በዮናስ ስብከትና ንስሓውን ጾሙንና
ጸሎቱን ምክንያት አድርጎ እግዚአብሔር ከጥፋት
አድኖታል ።

ነቢዩ ዮናስም ሰውን ከጥፋት አዘቅት ለማው
ጣት ከሞት ወደ ሕይወት ለማሻጋገር ሦስት መዓ
ልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ለተነሳው
ለወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ አንፃራዊ
ምሳሌ ሆኖ ስሙና ታሪኩ በሐዲስ ኪዳን ተሳልፎ
ሲነገርለት ይኖራል ምሳሌው አድርጎ ያስተማረ
ውም ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ማቴ
፲፪ ፣ ፴፱-፵) ዮናስ አንድ ሆኖ ብዙ ሰዎች ፣ ከፍተኛ
ሀብትና ንብረት የነበረበትን መርከብ አስጨንቆ
ከእግዚአብሔር አምልኮት ከእውነት መንገድና ከፍ
ትሕ ሚዛን ሸሽተው የሚኖሩ ብዙ ዮናሶች የተሳፈ
ሩባት መርከብ (ይህች ዓለም) የቱን ያህል ጭን
ቀት ይኖርባት ይሆን ? ከጭንቀት በላይ ነው ።
የዮናስ ዕጣ ቢወድቅስ ወደ ባሕር የሚጣለው ስንት
ሰው ይሆን ? ይሁንና ከታሪኩ የምንማረው ሰው
በደለኛ እግዚአብሔር መሐሪ መሆኑን ነው ።
የቤተ ክርስቲያንን ድምፅ መስማት የንስሓን ጥሪ
መቀበል ፣ በጾም በጸሎትና በዕንባ ወደ እግዚአብ
ሔር መመለስ ከታዘዘ መቅሠፍት ያድናል ፣ ቀደ
ምት አበው የነነዌ ሰዎች የጻኑበት ጾም ጸሎት
ኀዘንና ንስሐ የሚጠቅም ትምህርት ስለሆነ እኛም
እንድንጾመው ወስነዋል ። ጾሙን እንድንጠቀም
በት ምሳሌውን አስተላልፈዋልና ።

# ገዳማዊ ሕይወት

## «በግዐ ቅድስት ማርያም ገዳም»

ከሊቀ ትጉሃን ገብረ ክርስቶስ ኃ/ማርያም

ይህ ገዳም በትግራይ ክልል በተምቤን ወረዳ
ከዓቢይ ዐዲ ከተማ ፲ ኩሎ ሜትር ያህል ርቆ የሚገኝ
ነው ። ይህ ገዳሙ ከተተከለ ፩ሺ፪፻ ዓመት እንደሚሆ
ነውከታሪኩ መረዳት ይቻላል ፡ የበግዓ ቅድስት ማር
ያምን ገዳም የተከሉት ጌታዬ ተወልደ መድኅን የሚ
ባሉ አባትናቸው ። ጌታዬ ተወልደ መድኅን ደብረ ዓሣ
እየተባለ በሚጠራው ቅልቅ አምባ በምናኔ ዓለም
የሚኖሩ አባት ነበሩ ። እኚህ አበው ከዕለታት ባንዱ
ከተራራው ላይ ባለው በዓታቸው ሆነው ሲጸልዩ
ሰው አለበት ተብሎ በማይገመት ደንና ጫካ ቀጭን
ጢስ ወደ ሰማይ ቀጥ ብሎ ሲወጣ አዩ፤በዚህ ሁኔታም
ለብዙ ጊዜ በቀኪታታይ ሲመለከቱ ቆዩ በዚሁ ጊዜ
ጌታዬ ተወልደ መድኅን ካሉበት ጢሱ እስከ ታየበት
ቦታ በኢጋምና በቀንጣፉ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ከመሆኑም
በላይ ታላላቅ አውሬዎች በብዛት የረቡበት ስለነበር
ጢስ ቅሬታው ኪታየበት ቦታ ሰተት ብሎ ለመሔድ
አስነጋሪ ነበር «ይሁን እንጂ ለእግዚአብሔር ያደረ
አገልጋይ የሆነ ሁሉ ሥጋችሁን እንጂ ነፍሳችሁን
ሊያጠፉት አይችሉም» የሚል ቃለ ወንጌል ስለሚ
ያበረታቸው ጢስ ቅታሬው ኪታየበት ቦታ ለመድረስ
መጥረቢያዎችን አዘጋጅተው ለእርሳቸው ብቻ መሔ
ጃ የምትሆን መንገድ በጫካው ውስጥ ለውስጥ መመ
ንጠር ጀመሩ ፣ በዚህ ዓይነት ጉዞ ከአንድ ዓመት ባል
በለጠ ጊዜ ውስጥ ከቦታው ደረሱ ። እዚያ እንደደረ
ሱም አንድ ነጭ በግ ፊቱን ወደ ምሥራቅ አቅንቶ
ተኝቶአል ወደ ሰሚን አቅጣጫም የተኛ አንበሳ ይታ
ያል ፣ ወደ ደቡብም ለመብረር የተዘጋጀች የምትመ
ስል ዘብድወ ጠሊ (ሚዳቋ) አለች ወደ ምዕራብም
ደግሞ አትኩሮ የሚያይ ሽንጣም ነብር ተጋድሞአል
ከአራቱ እንስሳትና አራዊት መካከል ደግሞ ሥራው
እጅግ የሚያስደንቅ ታቦተ ማርያም ከነጽላቱ ፣ በታ
ቦቱ ላይ የወርቅ ጻሕል ፣ በግርጌው የወርቅ ዕርፈ
መስቀል ያለበት የወርቅ ጽዋ ተቀምጦአል ፣ በሰው
እጅ ያልተሠራ ሥራው እጹብ ድንቅ የሆነ ጽንሐሕ
ፍሕምና ዕጣን ያለበት ሲጤስ ከዐውዱ ጎን ደግሞ
ትልቅ ለመቀደሻ የሚሆን የእጅ መስቀል ተመ
ለከቱ ፣ እን ሰሳቱና አራዊቱጌታዬ ተወልደ መድኅንን
ባዩ ጊዜ ወደ የአቅጣጫው እየበረሩ ሔዱ ።

ጌታዬ ተወልደመድኅ ንም እንጨት ቆርጠው
ሣር አጭደው ትንሽ መቃኞ ሠርተው ንዋያተ ቅድሳ
ቱንም አስገብተው በየመልኩ አስቀምጠው ወደበዓ
ታቸው ተመለሱ ። ከዚያም የበዓለ ማርያም ዕለት
በወር አንድ ጊዜ አምስት ልኡካን እየያዙ በመሔድ
ቀድሰው ይመለሳሉ ። ከብዙጊዜ በኋላም በአካቢባው
ሰዎች እየመጡ ጫካውንም እየመነጠሩ እያቀኑ መን
ደር ፣ አገር አደረጉት ፣ እነሆም ሕዝቡ በዚያ ጫካ
ይህ ቤተ ክርስቲያን በማግኘቱ ታላቅ ደስታ ተሰማው
ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎትም
በተሟላ መልኩ በሥነ ሥርዓት ይካሔድ ጀመር ።
ከብዙ ዘመናት በኋላም ቦታው ለገዳም አመቺነቱ
በሁሉም ዘንድ ስለተደገፈ ሀሳቡ በዘመኑ ለነበሩ
ለአጼ አድያም ሰገድ ኢያሱ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮ
ጵያ ቀርቦ በሕዝቡ ጥያቄ መሠረት ርስተ ጉልቱ
ተሟልቶ ገዳም ሆነ በመረሠቱ ታሪኩም ስሙም
«በግዐ ቅድስት ማርያም » ተብሎ እንዲጠራ መወሰ
ኑንም ከገዳሙ የሚገኘው ታሪክ በሰፊው ያስረዳል ።

ከዚያም በገዳሙ ብዙ የበቁ በረከታቸውና
ረድኤታቸውም ለሀገርና ለወገን የሚጠቅሙ አበው
ወጥተውበታል ። አልፈውበታልም ። ዛሬም
ቢሆን ይህ ገዳም ከታሪኩና ከዝናው አንጻር
«በግዐ ቅድስት ማርያም ዐቢይ»እየተባለ ሲጠራ
ይሰማል ። ከሥላሳ ያላነሱ መንደሮችም በሁዚ ገዳም
ስም «ትንሹ በግዐ» እየተባሉ ሲጠሩ ይኖራሉ ።

ይህ ገዳም በድሮ ዘመን የተትረፈረፈ ሀብት
ስለነበረው ብዙ መምህራንና መዘምራን የቅኔ ፣
የዜማ ፣ የመጻሕፍትና የሌዩ ልዩ ጥበባተ እድ ሊቃ
ውንት ነበሩበት በወርቅ ሙካሽና በሐር የተጌጡ ፣
አልባሳት ፣ ሕብሩ የማይታወቅ የተለያየ ንዋያተ
ቅድሳት ፣ የታሪክና የወግ ዕቃዎች አሉት «የወርቅ ፣
የብርና የናስ የብረትና የአልምኒየም መስቀሎች በብ
ዛት ይገኙበታል» ታላላቅ የብራና መጻሕፍት ረዥም
ዕድሜ ያላቸው አርጋኖን ፣ ግዕዝ በግዕዝ የሚተረጉም
ወንጌል ነገረ ማርያም ጊዮርጊስ ወልደ አሚድና
የመሳሰሉት የከበሩ ቅዱሳት መጻሕፍት አሉት ።

እንግዲህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ
ክርስቲያን ገዳማት ሀገራችን ኢትዮጵያን የሚያኮሩ
አት ጥንታዊነትዋንና ታሪካዊነትዋን የሚመሰክሩላት
መዘክሮች ናቸው እነዚህንና የመሳሰሉትን ብርቅና
ድንቅ የሆኑ ቅርሶች የያዙ ገዳማት ለሕዝቡና ለሀገ
ሪቱም ጌጥና ፈርጥ ናቸው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ
ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንም ገዳማትን
የሚወዱ በዚህና በመሳሰለው ታሪካዊ ገጻቸው (ይዞ
ታቸው) ነው ። እንዲሁም ገዳማትን የቆረቆሩ አባ
ቶች በመንፈሳዊ አገልግሎታቸውና በተጋድሎአቸው
በትሩፋታቸውና በግብረ ገብነታቸው ያገኙት ጸጋ
ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ቃል ኪዳን መሠረት
በእምነት ለሚመስሉአቸው በቃል ኪዳናቸው ለሚ
ታመኑ ልጆቻቸው በረከታቸውን እንደሚያስተላል
ፉላቸው በማመን ነው ፣ ስለሆነም ምእመናን ገዳማ
ቱን የቀረበውን በእግራቸው ፣ የራቀውን በትራንስ
ፖርት እየኼዱ የሚሳለሙ ይህንኑ የአባቶች በረከት
እንደሚያገኙ ተስፋ በማድረግና በማመን ነው ።

የቅዱሳንን በረከት ለማትረፍ ፣ ቅዱሳን ካሉበት
ወይም ካረፉበት ደጅ መሳለም ከጥንት ተያይዞ
የመጣ እንጂ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደውኃ ፈሳሽ
የተገኘ አይደለም ። ምእመናን ከቅዱሳን በረከት
ለማግኘት የጌታን መካነ መቃብር ተሳልመው ረድ
ኤት ለመቀበል በየብስ ይጓዙ ነበር በግብጽ በእስከን
ድርያ ያሉት ታላላቅ ገዳማትም እንደዚሁ ትብንተ
ውና ተሳልመው ይመለሱ እንደነበሩ ከታሪክ ማኅደር
ለመረዳት እንችላለን ።

በተለይም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክር
ስቶስ «ዘተወከፈ ኪያክሙ ተወከፈ ኪያየ ወዘተወ
ከፈ ኪያየ ተወክፎ ለዘፈነወኒ ዘተወከፈ ነቢየ በስመ
ነቢይ አስበ ነቢይ ይነሥእ፣ ወዘተወከፈ ጻድቀ በስመ
ጻድቅ አስበ ጻድቅ ይነሥእ» ማለት እናንተን የተቀ
በለ እኔን ይቀበላል እኔን የሚቀበል የላከኝን ይቀበ
ላል በነቢይ ስም የተቀበለ የነቢይን ዋጋ ያገኛል »
በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል ።
ባለው መሠረት ምእመናን ከነቢያት ከሐዋርያትና
ከሰማዕታት አባቶቻቸው ጸጋና በረከት ለመቀበል
ለማግኘት ወደገዳማት መሔድና መሳለም ያዘወት
ራሉ ይህም አስፈላጊና ተገቢ መሆኑን በገድለ ቅዱ
ሳን ተጽፎአል ።

ከሐዋርያት አባቶች አንዱና ዋነኛ የሆነው ቅዱስ
ጴጥሮስም በሁለተኛው መልእክቱ «በቅዱሳን ነቢ
ያትም ቀድሞ የተባለውን ቃል በሐዋርያቶቻችሁም
ያገኛችኋትን የጌታችንና የመድኃኒታችን ትእዛዝ
እንድታስቡ በሁለቱ እያሳሰብኋችሁ ቅን ልቦናችሁን
አነቃቃለሁ» ፩ ጴጥ ፫፣ ፩—፪ ብሎ በጻፈው
ማሳሰቢያ ቃል ገድለ አበውን ድካመ አበውን በማዘ
ከር ቅዱሳን ካረፉበት ወይም ከጸለዩበት ሐዶ
በረከታቸውን መቀበል አለብኝ ብሎ አስቦ ገዳማትን
የሚጎበኝና የሚሳለም ሰው ንኡድ ክቡር መሆኑንና
የጽድቅ መንገድ የሆኑትን ቅዱሳት መጻሕፍትን
ማንበብ እንደሚጠቅም የሚያምን ሁሉ ዋጋው ትልቅ
መሆኑን አያጠራጥርም ።

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ካለፈው የቀጠለ

## የቤተ ክርስቲያን አመሠራረት

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ጊዜው በደረሰ
ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ» (ገላ ፬ ፬) እንዳለው
ከአዳም እስከ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክር
ስቶስ ልደት የነበሩት እናት አባቶቻችን በአካለ ነፍስ
በሲኦል ሆነው ስለመድኃኒታችን እና ስለ መዳናቸው
ወደ ፈጣሪያቸው ይጸልዩ ነበርና ልዑል እግዚአብ
ሔር ጸሎታቸውን ሰምቶ ነቢያትን አስነሣላቸው
ነቢያትም በኋለኛው ዘመን የእግዚአብሔር ልጅ ሰው
ሆኖ ራሳቸውንና አባቶቻቸውን እንደሚያድን ተገል
ጾላቸው ትንቢት ተናገሩ ለአባታችን ለአዳም በተሰ
ጠው ተስፋ መሠረት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ የሰውን ልጅ ለማዳን ከእመቤታችን ከቅድ
ስት ድንግል ማርያም ተወለደ ። ፍጹም አምላክ ፍጹም
ሰውም መሆኑን ለማረጋገጥ እምላክ ነኝና አለቱን
ልደግ ሳይል ለእናቱና ለዘመዶቹ እየታዘዘ በየጥቂቱ
አደገ ። (ሉቃ ፪. ፶፩) በሠላሳ ዓመቱ በፈለገ ዮርዳኖስ
በዕደ ዮሐንስ ተጠመቀ ። አርብዓ መዓልትና አርብዓ
ሌሊት በገዳመ ቆሮንቶስ ከጾመ በኋላ በዲያብሎስ

www.ethiopianorthodox.org

ሎች አውራጃዎች እየተዘዋወረ ማስተማር ጀመረ ። (ማቴ ፬ ፳ ፣ ፲፺) ።

የእግዚአብሔር ቃል ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰበክ ሐዋርያትን መረጠ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትም ትምህርቱን እየተማሩ ፣ ታምራቱን እያዩ ሦስት ዓመት ከሶስት ወር ከርሱ ጋር ኖሩ ። የሐዋርያቱም ስም ቅዱስ ጴጥሮስ ፣ ቅዱስ እንድርያስ ፣ ቅዱስ ያዕቆብ ፣ ቅዱስ ዮሐንስ ፣ ቅዱስ ፊልጶስ ፣ ቅዱስ በርተሎሜዎስ ፣ ቅዱስ ቶማስ ፣ ቅዱስ ማቴዎስ ፣ ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ፣ ቅዱስ ታዴዎስ የተባለው ልብድዮስ ቅዱስ ስምኦን ቀነናዊ በኋላ ናትናኤል የተባለው ይሁዳ አስቆሮታዊ ሲሆን ጌታ ከአረገ በኋላ በይሁዳ አስቆሮታዊ ምትክ ማትያስ ተመርጦ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ጋር ተቆጥሯል ። ትውልዳቸውም ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ነው ። ጴጥሮስ ፣ ወንድሙ እንድርያስ አባታቸው ከነገደ ሮቤል ሲሆን እናታቸው ደግሞ ከነገደ ስምኦን ናት ። ያዕቆብና ወንድሙ ዮሐንስ በአባታቸው ከነገደ ይሁዳ ሲሆን በእናታቸው ደግሞ ከነገደ ሌዊ ነው ። ፊልጶስ ከነገደ ዛብሎን ፣ በርቶሎሜዎስ ከነገደ ንፍታሌም ፣ ቶማስ ከነገደ አሴር ፣ ማቴዎስ ከነገደ ይሳኮር ። ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ከነገደ ጋድ ። ስምኦን ቀነናዊ በኋላ ናትናኤል የተባለው ከነገደ ብንያም ። ታዴዎስ የተባለው ልብድዮስ ከነገደ ዮሴፍ ። በይሁዳ ምትክ የገባው ማትያስ ከነገደ ዳን ነው ።

የሐዋርያት ትውልዳቸው ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ይሁን እንጂ የተመረጡት ዝቅተኛ ኑሮ ከሚኖሩ ቤተሰቦች ነበር ። «እግዚአብሔር የዚህን ዓለም ጠቢባን ያሳፍር ዘንድ ሰነፎችን ፣ ኃያላንንም ያሳፍር ዘንድ ደካሞችን መረጠ ። የዘመድ ታላቅነት ያላቸውን ያሳፍር ዘንድ የተናቁትን መረጠ» ሲል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የጻፈውን መመልከት ያስፈልጋል ። (፩ኛ ቆሮ ፩ ፳፯-፳፱) ። ያዕ ፪ ፭ ።

አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትም በጌታ ከተመረጡ በኋላ በምድረ እስራኤል እየዞሩ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ» እያሉ እንዲያስተምሩ ታዘዙ የታዘዙበትንም የወንጌል ሥራ ለመፈጸም ሲዘዋወሩ ለእጃቸው በትር ፣ ለስንቃቸው ምግብ ፣ ለእግራቸው ጫማ እንዳይዙ መመሪያ ሰጣቸው ከዚህም ጋር ድውያኑን እንዲፈውሱ ሙት እንዲያስነሱ አጋንንትን እንዲያስወጡ ፣ ለምጽ እንዲያነጹ ሥልጣን ስለተሰጣቸው በየደረሱበት ተቀባይነት አግኝተው ስለነበር የዕለት ምግብና ልብስ አልተቸገሩም ። (ማቴ ፲ ፳-፲፭ ሲያስተምሩም መከራንና ሞትን እንዳይፈሩ በሚያስተምሩበትም ጊዜ እንዳያስቡና እንዳይጨነቁ የሚያበረታታና የሚያጽናና ቃል ተነገራቸው ። ማቴ ፲ ፲፱ ፣

ጌታ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ከአስተማረ በኋላ የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ከሊቃነ ካህናት በተላኩ ወታደሮች ተይዞ ፣ በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ ። በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ። ከተነሣ በኋላ አርባ ቀኖች ቆየ ። በእነዚህ ቀኖች ውስጥ ለሐዋርያት በገሊላና በኢየሩሳሌም እየተገለጸ፣ ለሐዋርያት ምሥጢራትን እየፈጸመ የሐዋርያነት ሥራቸውን እንዴት እንደሚሠሩ ሲያስረዳቸውና ሲያስተምራቸው ከሰነበተ በኋላ ዐረገ ።

ከሙታን በተነሣ በዐርባኛው ቀን በዐረገ በአሥረኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን በሐዋርያት ላይ አሳደረ ። የመጀመሪያይቱን ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ። (የሐ ሥ ፪ ፬) ጌታ በሚያርግበት ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እስክትለብሱ ከኢየሩሳሌም ከተማ አትውጡ ብሎ ደቀመዛሙርቱን አዞአቸው ነበርና በጸንጠቆስጤ በዓል ሁሉም በየሥፍራቸው በአንድነት ሳሉ እንደ አውሎ ነፋስ ያለ ድምጽ በድንገት ከሰማይ መጥቶ የነበሩበትን ቤት ሞላው ። የተከፋፈለም የእሳት ላንቃ (ልሳን) ታያቸውና በየአንዳንዱ ላይ አደረባቸው ። ወዲያውም በልዩ ልዩ ቋንቋ ይናገሩ ጀመር በየአገሩ ከተበተኑ አይሁድ ወገን ለበዓለ ፋሲካ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ነበሩና በሁኔታው እጅግ ተደነቁ ።

ለበዓለ ፋሲካ በኢየሩሳሌም የተሰበሰቡበትም ምክንያት እስራኤል በምድረ ግብጽ በባርነት እየተገዙ ሲኖሩ ልዑል እግዚአብሔር በቸርነቱ ከባርነት አውጥቶ ወደ ምድረ ርስት ስለአገባቸው ከባርነት የወጡበትን ቀን በዓለ ፋሲካ እያሉ በየዓመቱ እንዲያከብሩ ታዘው ነበር ። (ዘፀ ፲፪ ፲፰-፳) በዓለ ፋሲካንም ከአከበሩ በኋላ አምሳ ቀን ቆጥረው በዓለ ሰዊትን የሚባለውን በዓል አክብረው ወደ የመጡበት አገር ይመለሱ ነበር ።

በዓለ ሰዊትም ማለት እህል የሚታጨድበት የመከር ወራት ነው ። መከርም በደረሰ ጊዜ መጀመሪያ ከሚወቁት እህል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ታዘው ነበር ። ከበዓለ ፋሲካ ጀምሮ ሰባት ሳምንቶች እስኪጨርሱ እያንዳንዱ በየቀኑ አንዳንድ ነዶ እህል ይሰጥ ነበር።ነዶ ማለት ትንሽ መስፈሪያ ነው ። ሰባት ሳምቶች አርባ ዘጠኝ ቀናት ናቸው ። በሃምሳኛውም ቀን ሊቀ ካህናቱ ከእህሉ በእንቅብ አቅርቦ ከጸለየበት በኋላ የበጉን መሥዋዕት ለእግዚአብሕሔር ያቀርባል ይህም ቀን ታላቅ በዓል ሆኖ ይውል ነበር ። ይህ ቀን በጽርዕ ቋንቋ ጰንጠቆስጤ ተብሎአል ። ሰባት ሳምንቶች ማለት ነው ።(ዘሌዋ ፳፫ ፲-፲፩) በሀገራችን በተለይም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የዘመን መለወጫ ዕለት ሁለት ወይም ሦስት መስፈሪያ ስንዴ በእንቅብ ይቀርብና ከምሑራኑ አንዱ ባሕረ ኃሳቡን ተናግሮ የበዓላቱን ቅደም ተከተል ዘርዝሮ ሲጨርስ ካህኑ ስንዴውን ይባርካል ። ይህም ሥርዓት ከበዓለ ሰዊት የመጣ ደገኛው የአይሁድ ልማድ መሆኑን ያስረዳል ።

መንፈስ ቅዱስ በዚሁ በጰንጠቆስጤ በዓል በዕለተ እሁድ ከነግሁ በሦስት ሰዓት በሐዋርያት ላይ በወረደ ጊዜ ሁሉም በያገሩ ቋንቋ ይናገሩ ጀመር ። ከዚያም ታምራት እያደረጉ ፣ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወንጌልን እየሰበኩ ስለኖሩ በሕዝቡ ዘንድ መወደድን አተረፉ እግዚአብሔርም በየቀኑ የአመኑትን ለቤተ ክርስቲያን ይጨምር ነበር ። (የሐ ሥራ ፪ ፩-፵፯

ይቀጥላል ።

ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ/አማኑኤል

# የጸሎት ኃይል

ነፍስ ያለው ፍጡር ሁሉ በሕይወት ለመኖር መተንፈስ አስፈላጊው መሆኑን ልጅም ሆነ አዋቂ ያውቃል እስትንፋሱም በሚከለከልበት ቅጽበት ወዲያው ታፍኖ መሞቱ የግድ ነው እንዲሁም የትንፋሽ ችግር የሚባል በሽታ ሲኖርበት ሰውነቱ ደካማና ለሥራ አቅም የሌለው ይሆናል ልክ እንደዚሁ የክርስቲያን እስትንፋስ ተብሎ የሚጠራው ጸሎት ቢቋረጥበት ውጤቱ መንፈሳዊ ሞት ነው እንጂ በክርስቲያንነቱ ጸንቶ ሊኖር አይችልም ምናልባት እስከዚህ ድረስ ባይደርስም ጸሎት ማድረጉን የሚያጓድል ክርስቲያን ለክርስቲያናዊ ተግባር የማይበቃ መንፈሳዊ ደካማ ሆኖ መገኘቱ የማይቀር ነው ። ሰው ከፈጣሪው ጋር የሚነጋገረው በጸሎት ነው ይህ ግንኙነት ተጠብቆ እንዲኖር የጸሎት መንገድ ተሰጥቶናል ። ስለዚህም ከእግዚአብሔር ጋር የምንነጋገረው በጸሎት ነው ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት የምድርን አሕዛብ ሁሉ የእርሱ ተከታዮች እንዲያደርጉ ለሥራ በላካቸው ጊዜ ያስታጠቃቸው መሳሪያ ጸሎት ነበር ። ከዕርገቱም በኋላ ሲልካቸው በሰጣቸው ትእዛዝ አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ ደቀመዛሙርቴ አድርጉአቸው የሚል ነበር ።

ሥራውንም የጀመሩት ከኢየሩሳሌም ነበር ከተማይቱ ጌታችን ካረገበት ደብረ ዘይት ከተባለው ሥፍራ ምንም ያህል የራቀች አልነበረችም ከቆሙባት ቦታ ሆነው ሊያይዋት ይችሉ ነበር ። ከተማይቱ በጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ንጹሕ ደም እጃቸውን ሊታጠቡ በሚጓጉ የናዝሬቱ ኢየሱስ ስም በገሃድ ያነሣውን ሁሉ ለማጥፋት ታጥቀው በተነሱ አማጽያን ተሞልታ ነበር ምንም እንኳን አሥራ አንዱ ሐዋርያት ከአደጋው ለማምለጥ ዕድል ቢያጋጥማቸው እንዲሰብኩ የታዘዙት ምን ነበር ? ለአይሁድ እንቅፋት ለግሪኮች ሞኝነት የሆነውን የተሰቀለውን ክርስቶስን ነበር ።

ደብረ ዘይት ላይ ሆነው በምዕራብ አቅጣጫ የሜድትራንያንን ባሕር አሻግረው ሲመለከቱ ሃሳባቸው የሚያርፈው የዚያን ጊዜ የዓለም ዕንብርት በነበረችው ሮም ላይ ነበር ። የዚችንም ከተማ ነገር ሲያስቡ የወደፊቱ ዕድላቸው የተቃና ሆኖ አልታያቸውም ። እዚያ የሚጠብቃቸው በጽናቱና በታላቅነቱ ወደር የማይገኝለት መንግሥት በጥንታዊነቱ ተመሳሳይ የሌለው ሥልጣኔና ጥበብ ነበር ። በሥልጣኔና በጥበብ የደረጀውን በዚያን ዘመን የታወቀውን ዓለም ወደ ክርስቶስ እንዲመልሱ ከልዩ ልዩ ተግባር ላይ ተመርጠው የተጠሩ የገሊላ ሰዎች ሐዋርያት አድርጎ መላክ እንደቧልት የሚቆጠር ነገር ነበር ። ይህንን ከተግባራት ሁሉ በላይ የሆነውን ተግባር እንዲያከናውኑ የላካቸው ክርስቶስ የሚያደርገውን ነገር የሚያውቅ የባሕርይ አምላክ በመሆኑ የተሰጣቸውን ተግባር በሚገባ እንዲያከናውኑ የጸሎትን ጥቅምና መሳሪያነት እንዲያውቁ አድርጓቸው ነበር።የላካቸው አንድ የጸሎት ሌሊት ካሳለፈ በኋላ ነው(ሉቃ ፮ ፲፪) የጸሎትንም ታላቅነትና መሳሪያነት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምን ግምት ላይ እንዳዋለው ለመረዳት ከተናገራቸው ቃላት ጥቂቶቹን ብቻ መጥቀስ ይበቃል ።

ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው አባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል ማቴ ፲፰ ፲፱

እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉ ያልፋል ። የሚሳናችሁ ነገር የለም(ማቴ ፲፯ ፳ እድሚያቸውን ሙሉ በሥራና በትግል በማሳለፍ በዚህ መሣሪያከተጠቀ ሙት ቅዱሳን አንዱ እንዲህ ይላል ።

በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ (ፊልጵ ፬-፮)

ጌታችን ለዚህ ታላቅ ተግባር እንዲውሉ ሲልካቸው የሰጣቸው መሣሪያ የማይበገሩ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ያውቃልና የሰጣቸው ተስፋ የሚሳናችሁ የለም የሚል ነበር ። ጸሎት ያለ አንዳች ግዙፍ ማስተላለፊያ ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላው ሊሸጋገር የሚችለው የጠቢባን ፍልስፍና ሊደርስበት ከሚችለው በላይ ነው ። ይህም መሣሪያ ለእግዚአብሔር ወዳጆች ከፍ ያለ አገልግሎት የሚሰጠው ተቃዋሚዎቹ ሊጠቀሙበት የማይችሉ በመሆናቸው ነው እርግጥ ነው በዚህም የእግዚአብሔርን ስጦታና ጥበብ እንረዳለን ማንኛውም ሰው ይህን መሣሪያ ለበቀልና ለጥፋት ሊያውለው ቢችል ኖሮ የዚህ መሣሪያ አገልግሎት እንዴት አስፈሪ በሆነ ነበር የክርስቶስ ወዳጆች እንኳን ከእርሱ ፈቃድና ሐሳብ ውጭ በኃይሉ ሊጠቀሙበት አይችሉም ። ይህን ለማድረግ በሚሞክሩበት ጊዜ የመገናኛው መስመር በገዛ እጁ ይቋረጣል ። እግዚአብሔር ጸሎታችንን የሚሰማው ከፈቃዱ ውጭ ያልሆኑትን ነገሮችን በምንለምንበት ጊዜ ብቻ ነው ።

እንዲህ ከሆነ ልናስታውሰውና ከልብ ልንዘጋጅበት የሚገባ ጉዳይ ቢኖር ከፊታችን የምንደርስበት ዓመታዊውና ታላቁ የጾምና የጸሎት ጊዜ ነው ይህ ጊዜ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን በመገኘት ቁመን የምናስቀድስበት ጸሎት የምንጸልይበት ቅዱስ ቁርባን የምንቀበልበት መንፈሳዊ የሥራ ጊዜያችን ነው ።

በአንድ መንፈስ ሁነን በማኅበር ጸሎት ወደ እግዚአብሔር የምናቀርበው ልመና ተሰሚነቱ ፈጣን ነው ይህም እንዲሆን ሁላችን በማህበር ጸሎት ሁሉ ንጹሕ አስተሳሰብ እንዲኖረን ያስፈልጋል በንጹህ አስተሳሰብ ተሳስሮ የሚቀርብ ምልጃ ከእግዚአብሔር ጋር ያገናኛል ። በኃጢአት ብዛት መቅሰፍት



www.ethiopianorthodox.org

እንዲ ቢታዘዝ በማኅበር ጸሎት ከልብ የቀረበ ምልጃ መቅሰፍትን ሁሉ ይከላከላል ። የነነዌ መጥፋት በነቢዩ ዮናስ ተነገረ ። የነነዌ ሰዎች በእግዚአብሔር አምነው አዋጅ ነገሩ ሰዎችና እንሰሶች ከምግብ ተከልክለው ወደ እግዚአብሔር በብርቱ ጮኹ ሰዎችም ከክፉ መንገዳቸውና በእጃቸው ካለው ግፍ እንዲመለሱ ተነገረ ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ እግዚአብሔር ባየጊዜ ይወርድባቸው የነበረውን ጥፋት መለሰላቸው ። (ዮናስ ፫ ፩-፲) ቁም ነገሩ የጌታን ተግሳጽ ሰምቶ በጸጸት መመለስ ነው በዓለም ፍቅር ሲኖር የሚችለው የፍቅር አምላክ ዓለምን በምህረቱ ሲመለከት ነው።ችግሮች ተወግደው ሰላማዊ ኑሮ ለመኖር የሚቻለው ሰዎች ከክፉ ሥራ ርቀው አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ሲያደርጉ ነው ።

ከላይ እንደተመለከትነው ሐዋርያት በጸሎት ትጥቅ ከእግዚአብሔር ጋር በመሆናቸው ኃያላንን ሁሉ አሳፍረውና አሸንፈው ምድርን በወንጌል ኃይል ገለባብጠው አለፉ ። የድል አክሊል ተቀባዮች ሆኑ ። የእነዚህ ታላላቅ አባቶች ልጆች የሆን እኛም በዚህ ሐዘንና ደስታ ማጣትና ማግኘት መውደቅና መነሳት በሚፈራረቅበት ዓለም ላይ እንመላለሳለንና የጸሎትን ኃይል ታጥቀን ጸሎትም ሥራ መሆኑን አምነን ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው (ማቴ ፳፮-፵፩) እንዳለው ደካማ ሥጋችን እንዳያሸንፈን አጥብቀን መጸለይ ይገባናል ። ጸሎትም ኃይል ነውና

ሊቀ ዲያቆናት በላይ ጸጋዬ
ሰባኬ ወንጌል

## ሰማያዊ አባታችሁ ቸር እንደሆነ እናንተም ቸር ሁኑ

ሰዎች መልኩን አይተው ድምጹን ሰምተው አካሉን ዳሰው እንዲረዱት በቸርነቱ ሰው ሆኖ ለሰው ተገለጠ ወደ ሠርግ ቤት ሄዶ ውኃውን ወይን ጠጅ አድርጎ የሰዎችን ችግር አቃለለ በሁለት ዓሣ በአምስት እንጀራ አምስት ሺ ሕዝብ መግቦ አሥራ ሁለት መሶብ እንዲነሳ አደረገ በአንድ ዓሣ በሰባት እንጀራ አራት ሺ ሕዝብ መግቦ ሰባት መሶብ መነሳቱም ተጽፎል ዕውራን በማብራት አንካሶችን በማርታት ለምጻሙን በማንጻት አጋንንት ያደረባቸውን በማስወጣት በሽተኞችን በማዳን (በመፈወስ) ቸርነት ሠርቷል የዕለት ሬሣን ወልደ መበለትን ወለተ ኢያኤሮስን የአራት ቀን ሬሣ አልዓዛርን በማስነሳት የሰዎች ሐዘናቸውንና መከራቸውን በማስወገድ ቸርነት ሠርቷል ።

ተርቤ አበላችሁኝ ፣ ተጠምቼ አጠጣችሁኝ እንግዳ ሆኜ ተቀበላችሁኝ አለ እሱ የማያልቅበት ሀብታም ፣ የማያበድሩት ባለ ጸጋ ሲሆን ለሰዎች የተደረገ ለሱ እንደተደረገ በመቁጠር ተርቤ ተጠምቼ አለ እሱ በቦታ የማይወሰን ሲሆን እንግዳ ሆኜ አለ ታርዤ አለበሳችሁኝ ታምሜ ጠይቃችሁኛል እሱ በሽተኞችን የሚያድንና የሚፈውስ ሲሆን ለሰዎች የተደረገ ለሱ እንደተደረገ በመቁጠር ታምሜ ጠይቃችሁኛል አለ ታስሬ ጎብኝታችሁኛል እሱ ምን ወንጀል ሠርቶ ታሰረና ነው እንዲህ ያለው ቸር ሰው ወዳጅ ስለሆነ ለሰው ያደረጋችሁት ለኔ ያደረጋችሁት ነው ሲል በማይታበል ቃሉ አስረድቷል ።

-ቸርነት በስድስት ይከፈላል ።
- በገንዘብ ለተራበ ማብላት ለተጠማ ማጠጣት ለታረዘ ማልበስ ይህ በገንዘብ መርዳት ሲሆን
- በጉልበት ደግሞ በአርግና በደዌ በአቅም ደካማ ለሆነው የሚፈልገውን ነገር ገዝቶ በመስጠት በጉልበት የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በመርዳት የሚደረግ ቸርነት በጉልበት የሚረዳ ቸርነት ይባላል
- በአእምሮ ይቅርታ የማድረግ ቸርነት ማቴ ፮-፲፬ ።
- የተጣላን በማስታረቅ የሚደረግ ቸርነት ማቴ ፭-፱ ብፁዓን ገባርያነ ሰላም እስመ እሙንቱ ውሉደ እግዚአብሔር ይሰመዩ እርቅን የሚመሠርቱ ቅራኔን የሚፈቱ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ ተብሏል ።
- እራስን አሳልፎ በመስጠት የሚደረግ ቸርነት ዮሐ ፲፭-፲፫ አልቦ ዘየዐቢ እምዝፍቅር ከመዘይሚጡ ነፍሶ ህየንተ ቤዛቢጹ ስለ ባልንጀራ እራስን አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ ፍቅር የለም ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኛ ታስሮአል ስለኛም ተደብድቦአል ስለኛ ሥጋው አልቆ አጥንቱ እንከሚታይ ድረስ ተገርፎል በመልዕለተ መስቀል ተሰቅሎ ደሙን አፍስሷል መከራችንን ተቀብሎ ሞታችንን ሞቶ አድኖናል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመከተል ብዙ ክርስቲያኖች ራሳቸውን አሳልፈው በመስጠት የመጨረሻውን ቸርነት ፈጽመዋል ። እንጢላርዮስ የተባለ ፍጹም ሰው ገንዘቡን ሰጥቶ ከጨረሰ በኋላ ነዳያን ወደ እሱ መጥተው ገንዘብ ስጠን አሉት ፍጹሙ ሰው ገንዘቤን ጨርሻለሁ ምንም ገንዘብ ከኪሴ የለም የለበስኩት ልብሴ እና አካሌ እንጂ ምንም ገንዘብ የለኝም ጨርሼ ሰጥቻለሁ ሳልጨርስ ብትመጡ ኖሮ እንደሌላው አካፍላችሁ ነበር አላቸው ነዳያኑም የመጣነው ከሩቅ ሀገር ነው እንደምንም ብለህ ፈልግልን አሉት እንግዲያውስ እኔን ሸጣችሁ ገንዘቡን ተከፋፈሉ አላቸው እነሱም ፍጹሙን ሰው ሸጠው ገንዘቡን ተካፈሉ እንዲሁም አስቄጥስ በሚባል ገዳም አንድ ፍጹም ባህታዊ ነበረ በዚህም ገዳም አበምኔት ሲቀድስ የሚለብሳት ልብስ ነበረች ያችን ልብስ ሰይጣን እነሣሥቶት አንድ ሰው ከሰረቃት በኋላ ደወል ተደወለ ሌባው የደወሉን ድምጽ በሰማ ጊዜ ደነገጠ ፍጹሙ ባህታዊ ሲደነግጥ አይቶ ወንድሜ ምነው ደነገጥክ አለው ሌባው ሰይጣን አነሣሥቶኝ አበምኔቱ ሲቀድስ የሚለብሳትን ልብስ እንስቻለሁኝ የሚደወለው በዚህ ምክንያት በመሆኑ የሚደርስብኝን ችግር ስላወኩኝ ነው አለው ፍጹሙ ባህታዊ ልብሱን ጣለውና ሂድ አለው ጥሎት ሄደ ባህታዊው ልብሷን ዞር ቢያደርግ አትገኝም ነበር ደወሉ ተሰብስቡ የሚል ስለነበረ ሌባው ከስብሰባው ተገኝ በስብሰባውም የልብሰዋ መጥፋት ተነገረ ጉባኤው የገዳሙን ነዋሪዎች ቤት በሙሉ እየዞሩ የሚፈትሹ ሰዎችን መደበ ፈታሾቹም ሥራቸውን ቀጠሉ ፍጹሙ ባህታዊ ስለ ማይጠረጠር ፍተሻውን በፍጹሙ ባህታዊ ቤት አልጀመሩም ቢፈትሹ ቢፈትሹ ልብሷን ለማግኘት አልቻሉም ፈታሾቹ በመጨረሻ የማን ቤት ቀረን ቤቱን ሁሉ ዞረን አይተነዋል አሉና የቀረን ቤት የለም ከባህታዊ ቤት በቀር አሉ ታድያ ባህታዊ ሊሰርቀን ነው ? አሉና እንደ ገና ባህታዊ በዚህ ባይጠረጠርም የሁሉ ቤት ይፈተሽ ተብሏልና ባህታዊም ከሁሉ ውስጥ በመሆኑ የባህታዊ ቤት መፈተሽ አለበት በሚለው ተስማሙ ከበሩ ሲደርሱ አባታችን አንተን ጠርጥረን ሳይሆን የሁሉ ቤት ይፈተሽ ስለተባለ ነው ወደ አንተ ቤት የመጣን አሉት የሚሆነውን ምን አውቃችሁ ግቡ አላቸው ቢገቡም ከወለሉ ላይ አገኙዋት አንተ ላዩ ባህታዊ ውስጡ አታላይ አጭበርባሪ ሐሰተኛ ባህታዊ እያሉ ደበደቡት አንገላቱት ከደበደቡት በኋላ ከቦታችን ውጣ አሉት ደብድባችሁኛል ንስሐዬን ተቀብዬ ከቦታው ልኑር አላቸው እኛስ ከሌባ ጋር አንኖርም ብለው አስወጡት ልብሷን እናነሳለን ሲሉ የማትነሳ ሆነች በዚህ ጊዜ ሌባው ልብሷን የሰረኩኝ እኔ ነኝ ባህታዊው የተደበደበው በእኔ ምክንያት ነው ብሎ ተናገረ ስለ ባልንጀራ ራስን አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ ፍቅር የለም ያለው ዮሐ ፲፭-፲፫ በመጥቀስ የገዳሙ ነዋሪዎች ፍጹሙን ባህታዊ አድንቀውታል ። እርሱም ከበዓቱ ተቀምጧል እስመ ውእቱ መጠወ በእንቲአነ ወንሕነኒ ይደልዎነ ንመጡ ነፍሰነ በእንተ ቢጽነ እሱ ራሱን ስለኛ አሳልፎ ሰጥተዋልና እኛም ስለ ባልንጀሮቻችን ራሳችንን አሳልፈን መስጠት ይገባናል እንዳለው ሁሉ የቸርነት መጨረሻው የፍቅር መደምደሚያው ራስን አሳልፎ መስጠት ነውና በገንዘባችን በጉልበታችን በይቅርታ የተጣሉትን በማስታረቅ እንዲሁም ራስን አሳልፎ እስከ መስጠት ድረስ ቸርነት መሥራት ይገባናል ሰማያዊ አባታችሁ ቸር እንደሆነ እናንተም ርኅሩኅ ሁኑ ብሏልና ።

ከመምህር ገብረ ማርያም ጥላዬ

## ሰንበትን አክብር

ሰንበት ማለት ዕረፍት ወይም ሰባተኛ ቀን ማለት ነው ሰንበትን ማክበር የጀመረው ፍጡር ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር አምላክ ነው ። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ስድስት ቀን ሲፈጥር ሰንብቶ በሰባተኛው ቀን ከመፍጠር አረፈ ብሏልና እግዚአብሔር ከመፍጠር አረፈ ሲባል የሚፈጥረው አጥቶና በባሕርዩ ድካም ኑሮበት ወይም እርሱ ከሌላ ክብርን የሚሻ ሆኖ ሳይሆን ሰንበትን ማክበር ለሰው ጠቃሚ መሆኑን ለመግለጽ ነው ከአሥርቱም ቃላት አንደኛው ሰንበትን አክብር የሚለው ነው ።

አሥርቱ ቃላትን እግዚአብሔር በጣቱ ጽፎ ለሙሴ ከሰጠው በኋላ እንዲህ ብሎ አዘዘው የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ እስከ ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ ሰባተኛውን ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው አንተ ወንድ ልጅህም ሴት ልጅህም ሌሎህም ገረድህም ከብትህም በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ እግዚአብሔር በስድስተኛው ቀን ሰማይንና ምድርን ባሕርንም በውስጣቸው ያለውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፎአልና ዘጸ ፳ ቁ ፰-፲፪ ።

ኢሳይያስም የሰው ልጅ እንዳያረክሰው ሰንበትን የሚጠብቅ እጁንም ክፉት ከማድረግ የሚከለክል ብፁዕ ነው ብሏል ። «እግዚአብሔር ሰንበቱን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላል በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ለዘለዓለም የማይጠፋም ስም እሰጣቸዋለሁ ካለ በኋላ ወደ እግዚአብሔር የሚጠጉትንም መጻተኞች እንዳያረክሱት ሰንበትን የሚጠብቁትን ቃል ኪዳኔንም የሚይዙትን ሁሉ ወደ ተቀደሰ ተራራዬ አመጣቸዋለሁ ብሏል እያይዞም በጸሎቴም ቤት ደስ አሰኛቸዋለሁ ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የሚሆን የጸሎት ቤት ይባላልና ኢሳ ፶፮ ፩-፯ በሌላም በኩል ፈቃድህን ለተቀደሰው ቀን ከማድረግ እግርህን ከሰንበት ብትመልስ ሰንበትንም ደስታ ብትለው እግዚአብሔርም የቀደሰውን ክቡር ብትለው የገዛ መንገድህንም ከማድረግ ከንቱ ነገርንም ከመናገር ተከልክለህ ብታከብረው በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ደስ ይልሃል በምድርም ከፍታዎች ላይ አወጣሃለሁ ፣ የአባትህንም የያዕቆብን ርስት እሰጥሃለሁ የእግዚአብሔር አፍ ተናግሮአልና ኢሳ ፶፰ ፲፫-፲፬ በማለት ስለ ሰንበት ክብር ያስረዳል ።

ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን በርኲታል ቀድሷታልም ዘፀ ም ፳ ቁ-፲፪ ከሙሴም በኋላ የተነሱ ነቢያት ዕለተ ሰንበት እንዳይሻር ይጠብቁና ያስጠብቁ ይመክሩና ያስተምሩ ነበር ።

በፍትሐ ነገሥትም በአንቀጽ ፲፱ እሁድንና ቀዳሚትን ማክበር እንዲገባ ይናገራል ። ሐዋርያትም



www.ethiopianorthodox.org

በሁለተኛው ቀሌምንጦስ በስድሳ ሰባተኛው አንቀጽ
ሠራተኞች ወይም ሎሌና ገረድ አምስቱን ቀን ይሥሩ
አንድነቱንና ሦስትነቱን ይማሩ ዘንድ እሁድና ቅዳሜ
ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሂዱ ብሏል አይሁድ ቀዳሚት
ሰንበትን ሲያከብሩ ዐርብ ጀምረው የዘረጉትን አያ
ጥፉም ያጠፉትንም አይዘረጉም የታመመ አይጠይ
ቁም የሞተ አይቀብሩም ፡፡

ክርስቲያኖች ግን የታመመ ይጠይቃሉ የተጣላ
ያስታርቃሉ የሞተ ይቀብራሉ ፡፡ ስለዚህ የአይሁድና
የክርስቲያን አከባበር ልዩ ነው ጌታትን መድኃኒታ
ችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ወንጌል በሚያስ
ተምርበት ጊዜ በዕለተ ሰንበት ድውይ ሲፈውስ ዕውር
ሲያበራ ለምጽ ሲያነጻ ምውት ሲያነሣ ጸሐፍት ፈሪ
ሳውያን አይተው ሰንበትን ይሽራል እያሉ ይቃወ
ሙት ነበር ፡፡

ሐዋርያትንም በሰንበት ቀን እሸት ቀጥፈው በሉ
ብለው ከሰዋቸው ነበር ጌታ ግን ከመሥዋዕት ይልቅ
ምሀረትን እወዳለሁ ሲል ተገቢውን መልስ ሰጥቷ
ቸዋል በምሳሌም እንዲህ ሲል አስተምራል ከናንተ
በጉ ቢወድቅበት በሰንበት የማያነሳው ማነው ?
ከበግማ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረው ሰው
አይበልጥምን? እያለ የማዳን ሥራውን ሁሉ የሚ
ሠራው በሰንበት ነበር ፡፡

ይህ ሁሉ ለእኛ አብነት ለመሆን ነው ሰንበት
የሚለውንም ለቅዳሜ ብቻ አይደለም እሁድም ሰን
በተ ክርስቲያን ትባላለች እርሷንም የምናከብርበት
ምክንያት ፩ኛ/ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የጌታን
ጽንስ ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያበ
ሰረበት ዕለት በመሆኑ ፣ ፪ኛ/ መድኃኒታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ ዓርብ ዕለት በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ
ሞቶ ዓለምን አድኖ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለ
ይቶ የተነሣበትንና ተስፋ ትንሣኤውን የመሠረተበት
ቀን በመሆኑ ፣ ፫ኛ/ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት በጽ
ርሐ ጽዮን የወረደበት ዕለት ስለሆነ ከሰንበተ አይሁድ
ሰንበ ክርስቲያን ትበልጣለች ምክንያቱም ዓለም
የዳነው በዚሁ ዕለት ነውና በዚሁም አብነት አባ ባው
ማ የሚባል ደግ ሰው ነበር ግብሩ እየተዘዋወረ ገዳማ
ትን መጎብኘት ነው ከዕለታት በአንድ ቀን ገዳማትን
ሲጎበኝ ከአባ ኪሮስ ገዳም ደረሰናከአባ ኪሮስ ጋር
ነገራተ እግዚአብሔርን ሲነጋገሩእስከ ሰማይ የሚ
ደርስ ታላቅ ጩኸት ሰማ ከጩኸቱም የተነሣ ተራራ
ዎችና ኮረብታዎች ተነዋወጹ እርሱም አባ ኪሮስን
አባቴ ሆይ ይህ የምሰማው ጩኸት ምንድነው ብሎ
ጠየቃቸው አባ ኪሮስም ከጌታችን ኢየሱስ ክርስ
ቶስ አስቀድመው ምሥጢሩን አውቀውት ስለ ነበር
ይህ የምትሰማው ጩኸት በሲኦል ያሉ የኃጥአን
ጩኸት ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ስለከበረች ትንሣኤው ቅዳሜ ከ፱ ሰዓት ጀምሮ
እስከ እሁድ ማታ ፀሀይ እስኪገባ ድረስ ያሳርፏቸዋ
ልና ስለዚህ ሲያመሰግኑት ነው የሰማኸው አሉት
እኔም ይህንን ሰምቼ የሰንበትን ጌታ ኢየሱስ ክርስ
ቶስን አመሰገንሁት ብሏል ፡፡ (ስንክሳር ሐምሌ ፳) ፡፡

ሊቃውንትም ስለ ክብረ ሰንበት ሲናገሩ ቅዳ
ሜን ብቻ የሚያከብር እንደሆነ ኤርብ በ፱ ይወጣል
ቅዳሜ በተሲያት ይወርዳል ሁለቱንም የሚያከብር
ከሆነ ግን አርብ በተሲያት ይወጣል እሁድ በውርክ
ይወርያል እንዲህ እያለ ሲመላለስ ሲኖር ጌታ የሚ
መጣ እሁድ ቀን ነው ያን ጊዜ እንደወጣ ይቀራል ፡፡
ይላሉ ዛሬ ግን ካህናት ከአለማስተማራቸው የተነሣ
ሰንበትን ማክበር እየተዘነጋ የአከባበር መልኩም
እየተለወጠ በመሄድ ላይ ስለሆነ ከእግዚአብሔር
ክብር ለማግኘት የሚፈልግ ሁሉ ሰንበትን ያክብር ፡፡

መሪጌታ ይባቤ መልአክ

# የደወሌው ታቦተ ቅዱስ ሚካኤል ዕውር አበራ

በደወሌ ቅ/ሚካኤል የተፈጸመውን ገቢረ ተአ
ምር ከመግለጻችን አስቀድሞ ስለ ደወሌው ቅ/ሚ
ካኤል ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት በመጠኑ እና
ያለን ፣ ደወሌ ከድሬደዋ ምሥራቃዊ ክፍል በኢት
ዮጵያና ጂቡቲ ወሰን አቅራቢያ የሚገኝ በረሃማ
አነስተኛ ከተማ ነው ፡፡

የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በዚሁ
ከተማ ላይ በምድር ባቡር ፣ በጉምሩክ ፣ በፋናን
ስና በይለፍ ክፍል የሥራ ባልደረቦች እንዲሁም
በከተማው በሚኖሩ ምእመናን በጎ ፈቃድና ኅብ
ረት በ፲፱፻፸፩ ዓ/ም ገደማ ተመሠረተ ፡፡ የቤተ ክር
ስቲያኑ ሥራ በአካባቢው ሕዝብ ተሠርቶ እንዳ
በቃ ጊዜውን ጠብቆ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሲሆን
ሐምሌ ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም በበቆምስ ብርሃነ
ሥላሴ ተ/ሃይማኖት በአሁኑ ብፁዕ አቡነ ዜና ማር
ቆስ ተባርኮ ታቦተ ሕጉ የገባ መሆኑን በጊዜው
የድሬደዋ ሀ/ስብከት ሥራ አስኪያጅ የነበሩት
መጋቤ ትፍሥሕት አንዳርጌ ዘውዴ ገልጸዋል ፡፡

በሪፖርቱ እንደተገለጸው በደወሌ በረሃማ
ሥፍራ ላይ በተመሠረተው የቅዱስ ሚካኤል ቤተ
ክርስቲያን ልዩ ልዩ ተአምራት ታይቷል ከነዚህም
አንድ ዐይነ ሥውር ከመብራቱም በላይ ሁለተኛው
ሊቀ መላእክት ቅ/ሚካኤል የተወሰደበትን ቆርቆሮ
በተአምር ወደ ቤተ መቅደሱ መመለሱ ነው ዐይ
ናቸው የበራው ግለሰብ አቶ ጥላሁን ታደሰ የሚ
ባሉ የድሬደዋ ከተማ ነዋሪ ለዓይናቸው መታወር
መነሻው በውሃና ፍሳሽ አገልግሎት የቦኖ ውሃ አስ
ቀጂ ሁነው በሚሠሩበት ወቅት ቢርካውን ሲከ
ፍቱ እንደ ደም ያለ ነገር ይታያቸዋል ፡፡ ኮዚህም
ጋር የጋዜጣ ንባብ ሱስ ስለነበረባቸው አዘውት
ረው ጋዜጣ ያነቡ ነበር በነዚህ ፪ ምክንያቶች በየ
ትኛው ዐይናቸው እንደጠፋ በትክክል ባይታወ



መልአከ ምህረት ቅዱስ ሚካኤል

ቅም ዐይናቸው ደም ካየበት ጊዜ ጀምሮ እየደከመ
መምጣቱን አቶ ጥላሁን በዝርዝር ገልጸው የታወሩ
በት ዘመን በ፲፱፻፸፯ ዓ/ም እንደሆነ በሪፖርቱ
ሰፋ ተደርጎ ተገልጾአል ፡፡

አቶ ጥላሁን ታደሰ እንደገለጹት ከልጅነት
ዕድሜየ ጀምሮ ቅዱስ ሚካኤልን እወደዋለሁ አከ
ብረዋለሁ እዘክረዋለሁ ግን ዐይኔ በመታወሩ ምክ
ንያት ከሥራ ተወገድኩ ፣ ለመኖር ስል አንድ መሪ
ልጅ ይዤ ከድሬደዋ ደወሌ በመመላለስ የጫት
ንግድ ጀመርኩ በዚሁም ምክንያት በሔድኩ ቁጥር
በረኸኛው ቅ/ሚካኤል በድርሳንህ እንደሚነገረው
ብዙ ተአምር ሠርተሃል በእኔም ላይ ተአምርህን
አሳይ እለው ነበር በንግዴ የዕለት ጉርሴንና የዓ
መት ልብሴን በሚገባ እያገኘሁ የደወሌውን ቅ/ሚ
ካኤል አጥብቄ እማፀነው ነበር ፡፡ ዕለቱ ማክሰኞ
ወርሁ ሐሌም ፲፪ የሚካኤል ወርሐዊ በዓል ነበር
በዚሁ ዕለት የደወሌው ቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስቲ
ያን ተባርኮ ታቦቱ እንደሚገባ ባለቤቴ ነገረችኝ
እኔ ግን እጄም እግሬም በመተሳሰሩ ምክንያት አንች
ሂደሽ አክብረሽ ተመለሺ አልኳት አከበረች እኔ ግን
በዚሁ የሚካኤል ዕለት ልጄን ይዤ ዳቦዬን አቅ
ርቤ ከዘከርኩ በኋላ ከጎረቤቶቼ ጋር ጠበል ጠዲ
ቁን ቀመስን ቅዱስ ሚካኤልን አመሰግነን ጉረቤቶቼ
ሲወጡ እኔ ጋደም አልኩ እንቅልፍም ያዘኝ ፡፡ በእ
ንቅልፍ ላይ ሳለሁ አንተ አንተ የሚል የጥሪ ድምፅ
ሰማሁ ድምጹም ተደጋገሞ መጣ በኋላ ግን ብድግ
አልኩ ልጄን ብጠራው የለም ነገሩ ግራ አጋባኝ
በቤቱ ወለል ላይ በመተከዝ እንዳለሁ አንተ አንተ
አለና አታየኝም እንዴ ? አለኝ እኔም መልሼ እኔ
እኮ ዓይን የሌለኝ በመሆኔ ላይህ አልችልም አልኩ
መልሶም እኔ የደወሌው የመቶ አለቃ ኃይለ ሚካ
ኤል ነኝ እንዴት አታውቀኝም አለኝ እኔም በደ
ወሌ የማውቀው መቶ አለቃ ገበየሁን ነው አልኩት፣

ዕለቱ ቅ/ሚካኤል በመሆኑ ከልጅነት የምማፀ
ነው ቅ/ሚካኤል ይሆናል ብዬ አሰብ ነበር ፣ ሆኖም
የደወሌው መቶ አለቃ ኃይለ ሚካኤል ነኝ ቢለኝ
ልቤ በደስታ እየተመላ መጣ እሱም አሳቡን በመ
ቀጠል የለበስኩት ምንድነው ? የእኔስ መልክ ምን
ይመስላል ሲል ጠየቀኝ እኔም የለበሰው ልብስ በኮ
ከብ የተጥለቀለቀ መሆኑንና መልኩም ቀይ እን
ደሆነ ነገርኩት ፡፡ ከዚህም በኋላ ለ፲ ዓመታት ብር
ሃንን አጥቶ የኖረው ዐይኔ ለማየት በመታደሉ በደ
ስታ ተሞላሁ ከዚህም ቀጥሎ መልኩ እንደ ብርሃን
የሚያበራው ይኸ ሰው በቀጥታ እያየሁት የወርቅ
ኃብል በአንገቴ ላይ አጠለቀልኝ ፡፡ የዓይኔን መብ
ራት አረጋግጦ የድሮውን የወታደሮች ካኪ ልብስ
አለበሰኝ ፣ ወርቁንም ሆነ ልብሱን ለማንም እንዳ
ትሰጥ በማለት አስጠንቅቆኝ ከእኔ ተሰወረ ፡፡

ከተሰወረ በኋላ ለእኔም ሆነ ለጉረቤቴ ነገሩ
እውነት አልመሰለም በመሆኑም ባለ ፶ ባለ ፳፭
እና ባለ ፲ ሳንቲም ገንዘብ በግሬ ሥር እየጣሉ
ይኸ ምንድነው ? እያሉ ፈተኑኝ ፡፡ ሁሉንም ነገር
ኳቸው ፡፡ ይኸን ሲያረጋግጡ ደስታው ልዩ ሆነ ፡፡
እግዚአብሔር ይመስገን የቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢ
ነት አማላጅነት በሁሉም ሰዎች ዘንድ ለዘለዓለም
ይኑር አልኩ ብለዋል ፡፡

በመጨረሻም አቶ ጥላሁን ቃላቸውን ያጠ
ቃለሉት ይኸን አስደናቂ ተአምር በየቤተ ክርስቲ
ያኑ እየዞርክ መናገር አለብህ በሁላችንም ዘንድ
አስደናቂ ተአምር ነውና ሲሉ ጉረቤቶቼ ያላቸውን
ሃሳብ አካፈሉኝ ፡፡ እኔም ለ፲ ዓመታት በዓይኔ ሳላ
ያቸው የቆዩ በቤቴ ውስጥ ያሉ ሥዕሎችን እልል
እያልኩና እየሰገድኩ ሳምኳቸው ፡፡ ብለዋል ፡፡

ከዚህም ሌላ የደወሌ ቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስ
ቲያን ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በልዩ ልዩ
ምክንያት ሥራው ሳይጠናቀቅ ቆይቶ በመቃረቢ
ያው ቤተ ክርስቲያን ጣራ ላይ ተሠርቶ የነበረውን
ቆርቆሮ ነፋስ ወስዶት ስለነበር የወሰዱት ግለሰ
ቦች ቆርቆሮውን እንዲመልሱ ተጠይቀው ፈቃ
ደኞች ባለመሆናቸው በእነሱ ላይ ቅዱስ ሚካ
ኤል ተአምሩን ገልጾአል ፡፡

ታቦተ ቅ/ካኤል ሐምሌ ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም
ተባርኮ ከገባ
አዲስ በተሠራበት ቤተ ክርስቲያን ተባርኮ ከገባ
በኋላ በ፱ኛውና ፲፪ኛው ቀን ማለትም ሐምሌ ፳ ና ፳፪
፲፱፻፹፯ ዓ/ም ከባድ ነፋስ የቀላቀለ ኃይለኛ ዝናብ
ጥሎ በከተማው ውስጥ የሚገኙ ታላላቅ ሕንፃዎች
ተሰነጣጠቁ በላያቸው ላይ የነበረው የጣራ ቆርቆር
በነፋሱ ኃይል ተገንጣጥሎ ሲወሰድ ቀደም ሲል
ከቤተ መቅደሱ ላይ ተወስዶ የነበረውና ግለሰቦች
በራስ ወዳድነት ይጠቀሙበት የነበረው ቆርቆሮ
በዚሁ ከባድ ነፋስ ተጭኖ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ
በመምጣት በቅጽረ ግቢው ውስጥ ተቀመጠ ፡፡ ስለ
ሆነም ይህ በጣም አስደናቂ ተአምር ተባለ ፡፡ በከ



www.ethiopianorthodox.org

ተማው ከነበሩ ቤቶች ላይ የተነሳው ቀርቀሮ ግን በአየር ላይ በና በመሄዱ ሕዝቡን አስደንቋል ።

ከዚህም ጋር ለቅዱስ ሚካኤል በዓል አገልግሎት የተሰራች የቀርቀሮ ቤትና የቤተ ክርስቲያኑ ንብረቶች በዚህ ኃይለኛ ነፋስና ዝናብ ሳይጠፉ ድነዋል ። በማለት የሶበካ ጉባኤው ም/ ሊቀ መንበር መምህር ፍስሐ እንግዳ ወርቅ አረጋግጠዋል ።

እኛም ይህ ህስደናቂ ተአምር ለቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን የመንፈስ ጥንካሬ የሚሰጥ በመሆኑ ከድሬድዋ ሀ/ስብከት በተላለፈልን ዘገባ መሠረት በመጽሄቱ እንዲወጣ አድርገናል ።

ስለዚህ እግዚአብሔርን የሚወዱና የሚያከብሩ በቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነትና አማላጅነት የሚያምኑ ሁሉ ከሥጋዊ ቁስል ብቻ ሳይሆን ከቁስለ ነፍስም ሊድኑ እንደሚችሉ በዚህ መረዳት እንችላለን ።

ሊቀ ካህናት በለጠ አበበ

# አስደናቂ ተአምር በወንበር ማርያም


በዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም ከተራራው ዝቀ ብሎ በዳገታማው ሥፍራ ላይ ተተበላ የረጅም ዓመታት ታሪክ ያላት የወንበር ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፲፬ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው የኢተዮጵያ ንጉሥ እንድርያስ (ሕዝበናኝ) በዝቋላ ገዳም ካሠራቸው አምስት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አንዷ መሆኗ ይነገርላታል ። ይህች ከ፭፻ ዓመታት በላይ ያስቆጠረች ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያን ሥሪቷም ሆነ አስተዳደሯ በዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቀዱስ ገዳም ሥር ሆኖ በቀድሞ ጊዜ የነበሩት የገዳሙ አስተዳዳሪዎችም ለማንኛውም አስተዳደራዊ ሥራ ምቹና የአየር ጸባይዋም ወይና ደጋ በመሆኑ የመንፈሳዊ ዳኝነቱን ሥራ በዚችው ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ሁነው ያከናወኑ ስለነበር በዚህ ምክንያት የመምህሩ ማለትም የአስተዳዳሪው ወንበር መቀመጫ እዚያ ነው ለማለት ወበንር የሚለው ስያሜ እንደተሰጣተ ታሪክ ያበረዳናል ።

የወንበር ቀድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተች ወዲህ በጠላት ወረራ ተደጋጋሚ ጥፋት የደረሰባትና በፋሽስት ኢጣሊያን ቦንብ የቀድሞው ቤተ ክርስቲያን የተቃጠለባት ብትሆንም ጥንታዊነቷን የሚያስመስክሩላት በርካታ ጥንታዊ ቀርሳ ቅርሶች የሚገኙባት ታላቅ ገዳም ናት ። ይህች ቤተ ክርስቲያን የምትመራው በዝቋላ ገዳም አስተዳደር ሥር ሲሆን አገልጋዮቿም መናንያን መነኮሳትና የአካባቢው ተወላጆች ካህናት ናቸው ። አገልግሎቱን በተመለከተ ዘወትር ስብሐተ ነግህ (መዝሙር) የማይቋረጥ ሲሆን ቅዳሴና ሰዓታት በዓላትን በመከተል አገልግሎት ይሰጣል ። በዚህች ቤተ ክርስቲያን ስር ሆነው ገዳሙ በድጎማ የሚረዳቸው ፴፫ አቀመ ደካሞችና ከ፵ እስከ ፶ የሚደርሱ ካህናት ይገኛሉ ።

የቤተ ክርስቲያኗን ታሪካዊ አመጣጥና ሥሪት በማስመልከት አጠር ባለ መልኩ ከላይ ለመግለጽ ሞክረናል ። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ከላይ በርእሱ ወዳስቀመጥነው አስደናቂ ተአምር እንገባለን ። ዕለቱ ጥር ፲፩ ቀን ፻፺፯ ዓ/ም የጥምቀት ዕለት ሐሙስ ለአርብ አጥቢያ ሌሊት ነው ። በዚህ ሌሊት በዚህችው በእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ አስደንጋጭ የሆነ ዜና በደወል ተስተጋባ ፣ በዚያን ወቅት ሰዓቱ ፲ ሰዓት ነበር ። የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምና አብሮ በድርብ የነበረ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ፅላቶች መሠረቃቸው ለሕዝቡ ሲገለጽለት እናታቸው እንደሞተችባቸው ሕጻናት ሕዝቡ በእንባ ተራጨ ፣ ወዲያውም በአካባቢው ፍለጋውን ተያያዘው ፣ በዚህ ጊዜ ነበር አንድ አስደናቂ ተአምር የተከሰተው ፣ በፍለጋ ከተሰማሩት ምእመናን ውስጥ አንድ የ፲፰ ዓመት ወጣት ከቤተ ክርስቲያኑ በስተምሥራቅ በኩል በግምት አንድ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ አንድ በመጋረጃ የተጠቀለለ ሣጥን ተጥሎ ያገኛል ፣ ወዲያው ይህ ደግሞ ምንድን ነው ብሎ ከጓደኞቹ ጋር ለማንሣት ጠጋ ብሎ እጁን ሲዘረጋ እጁ ጥምልምል ይላል ፣ ሰውነቱም ዝልፍልፍ ይልበታል ፣ አብረውት የነበሩትም እንደዚሁ ይሆናሉ ። ለካስ የድንግል ማርያም ጽላት ኖሯል ወዲያው ካህን ተጠርቶ ቢታይ ሁለቱም ጽላቶች እንደነበሩ በሣጥኑ ውስጥ ተገኙ ፣ ሌላው ደግሞ የሚያስደንቀው የሌባው ልዩ ዕቃ ዘወትር በእጅ ይዞት ይታይ የነበረው ከጽላቶቹ ጎን አብሮ ወድቆ መገኘቱ የእመቤታችንንና የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን



ገባሬ ኃይል ቅድስት|ድ/ ማርያም



ጥንታዊቷ የወንበር ማርያም ቤተ ክርስቲያን

ተአምር እጅግ በጣም እንድናደንቅና የነበረንን ጠንካራ እምነት ይበልጥ እንድናጎለብተው ረድቶናል ። በዚሁ በተገኘው ዕቃ በመመራት ሌባውን ለመያዝ ብዙም ጊዜ አልፈጀም ሕዝቡን ሰብስበን ይህ ዕቃ የማን እንደሆነ የምታውቁ አጋልጡ ሲባል በሙሉ ሕዝቡ ወዲያውኑ አጋለጠ ። ያም ተጠርጣሪ ሰው ከተጠርጣሪ ግብር አበሮቹ ጋር እመቤታችን እሥር ይዛው ኖሮ ወዲያው ተያዘ ፣ ግብር አበሮቹ ይሆናሉ ከተባሉት ፫ ሰዎች ጋር በድምሩ ፬ ሰዎች በወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ታሥረው በምርመራ ላይ ይገኛሉ ።

የጠፋውም ስንክሳር በአዲስ አበባ ከተማ ሌባው ሊሸጥ በመዋዋል ላይ እንዳለ እጅ ከፍንጅ ተይዞ በም/ ሸዋ ፖሊስ ቁጥጥር ሥር ይገኛል ።

አንባብያን ሆይ !

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በርካታ ጥንታውያን ገዳማትና አድባራት እንዲሁም የሀገርና የወገን አኩሪ ቅርሳ ቅርሶች እንዳሉ ግልጽ ነው ። ይሁን እንጂ እነዚህን ቅርሶች በተለያየ ዘዴ በመጠበቀም ከሀገር ለማስወጣትና ቤተ ክርስቲያናችንን ቅርስ አልባ ለማድረግ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖታችንን ለማዳከም ፀረ ቤተ ክርስቲያን ሠርጎ ገቦች ቤተ ክርስቲያናትንን ለመድፈር ቢቃጡም ፣ ተዋሕዶ እምነታችን ድባቅ እየመታች ለውርደትና ለሀፍረት እያጋለጠቻቸው ይታያል ፣ ለዚህም በወንበር ቅድስት ማርያም የተፈፀመው ተአምር በቂ ምስክር ነው ።

ስለዚህ ማንኛውም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ እምነታችን (ሃይማኖታችን) ከጥንት አባቶቻችን ጀምሮ ልዩ ልዩ ገቢረ ተአምራት እየተፈጸመላት በርካታ አባቶች በዚህችው በተዋሕዶ እምነት ጸንተው ድውያንን በመፈወስ ሙታንን በማስነሳት ፣ ከልዑል እግዚአብሔር ጸጋና በረከትን በማግኘትና በማስገኘት ጠብቀው አሁን ላለነው ትውልድ ሙሉ እምነት ከነቀርሱ ሙሉ በረከት ከነትሩፋቱ ሙሉ ፍቅር ከነአንድነቱ ፣ አስረክበውን አልፈዋል ። እኛ የተዋሕዶ እምነት ተከታይ ልጆቻቸው ደግሞ የነሱን አርአያ ተከትለን ሃይማኖታችንን ቅርሶቻችንን አክብረንና ተንከባክበን መጠበቅ የሁላችን ድርሻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ።

እግዚአብሔር አምላክ ታቦተ ሕጉን በሚዳፈሩ ፀረ ቤተ ክርስቲያን ግለሰቦች ላይ ተአምራቱን የሚፈጽምባቸው (የሚያጋልጣቸው) እነሱ በንስሐ እንዲመለሱ ፣ እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ የተዋሕዶ እምነታችን ይበልጥ እንዲጠነክር በእምነታችን እንድንኩራበት የልዑል እግዚአብሔርን ሕግና ሥርዓት ጠብቀን እንድንኖር ስለሆነ የተዋሕዶ እምነታችን ከነጣቂ ተኩላዎች (ከመጤ ሃይማኖት) ጠብቀን ለእግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት ተገዥዎች ሆነን እንድንኖር ኋላም ከጻድቃን ከወገኖቹ ጋር ይቆጥረን ዘንድ የልዑል እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን አሜን ።

እነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ለርሱ ይሁን አሜን

መምህር ክፍለ ዮሐንስ መርሻ
የደብረ ዝቋላ ገዳም አስተዳዳሪ

# የቦሌ ደብረ ምህረት ቅ/ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎትና የልማት ሥራ እንቅስቃሴ

በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በየካ ኮተቤና ቦሌ አውራጃ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት አንዱ የቦሌ ደብረ ምህረት ቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ነው የዚህ ቤተ ክርስያን በአማረ ጥርብ ደንጊያ ተሰርቶ በመጠናቀቁ ታቦተ ቅዱስ ሚካኤል በአዲሱ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ስለገባ የደብሩ ሊቃውንት ተገቢውን ስብሐተ እግዚአብሔር ያደርሱበታል ።

የዚህን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን በውጭ ሁነን ስንመለከት በምሥራቅ በኩል የቅዱስ ሚካኤል ስእል በትልቁ ተስሎ በሕንጻ ቤተ መቅደሱ አናት ላይ ይገኛል በስተምዕራብ በኩል ደግሞ የቅ/ሚካኤል የቅ/ገብርኤል ስእሎች ያሉ ሲሆን ከሁለቱ ሥዕሎች መካከል የቅ/ድንግል ማርያም ሥዕል በትልቅ ቅርጽ ተሥላ ትገኛለች ።

በዚህ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቸርነት በቅ/ሚካኤል ጸሎትና ረድኤት ብዙ ሕሙማን ከደዌ አቸው ይፈወሳሉ ምእመናንም ብጽዓት ገብተው የለመኑት ይደርስላቸዋል ። በጠቅላላ ልዩ ልዩ አስደናቂ ተአምራት ይፈጸማሉ ።

የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ምህረት ጌታቸው አዳፍሬ ስለደብሩ መንፈሳዊ አገልግሎትና ጠቅላላ የልማት ሥራ በቁጥር ፬ሽ፬፻፶፱፭/፩፻፲፯/፹፯፬/፯/፹፯ ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ እንደገለጹት በዚህ ደብር ያሉ ሊቃውንትና ካህናት ፍጹም በሆነ ክርስቲያናዊ ፍቅር በመግባባት መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን የሚአከና





www.ethiopianorthodox.org

ውኑ ሲሆኑ ምእመናንም ለቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት የሚያደረጉትን አስተዋጽኦ በደስታእንደሚሰጡ እንደሚከተለው አስረድተዋል ።

የካህናት አገልግሎትን በተመለከተ

ለደብሩ መንፈሳዊ አገልግሎት የተመደቡ በቂ የሆኑ የአብነት መምህራንና ካህናት ያሉበት በመሆኑ አገልግሎቱ በአማረ ሁኔታ ይከናወናል የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ምህረት ጌታቸው የአስተዳደሩን ሥራ በፍቅርና በሰላም እየመሩ በአገልግሎቱም በኩል እንደ አንድ ካህን ሁነው ስለሚሠሩ የሁሉም መንፈሳዊ አገልግሎት አፈጻጸም በእጅጉ ያማረ ነው

ስብከተ ወንጌልን በተመለከተ ፣

ከዚህ ቀደም በዚህ ደብር በሳምንት ሁለት ቀን ብቻ የነበረው የወንጌል ትምህርት በአሁኑ ጊዜ ከአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በተመደበው ሰባኬ ወንጌልና በሌሎችም መምህራን በየቀኑ ዘወትር የወንጌል ትምህርት ይሰጣል ። ቀድሞ የወንጌል ትምህርት ይሰጥበት የነበረው ድምጽ ማጉሊያ እየተበላሸ በማስቸገሩ ከአሥራ ዘጠኝ ሺህ ብር በላይ የፈጀ አዲስ ድምጽ ማጉሊያ በአንድ በጎ አድራጊ ተገዝቶ አገልግሎት ላይ በመዋሉ የሚሰጠው የወንጌል ትምህርት በርቀት ለሚአዳምጡ ምእመናን ሁሉ በሚገባ ይሰማል በዚህ ደብር በዕለቱ ለሚሰጠው የወንጌል ትምህርት ከስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ያሉ ሊቃውንት እየተገኙ እንዲያስተምሩ ቢደረግ የሚሰጠው የወንጌል ትምህርት ምእመናን ለንስሐ የሚአዘጋ ይሆናል ።

የሰንበት ት/ ቤትን በተመለከተ

በዚህ ደብር የተጠናከረ የወንጌል ትምህርት የሚሰጥበት ሰንበት ት/ቤት አለ በዚህ ሰንበት ት/ቤት የሚማሩ ልጆች በቤተ ክርስቲያኑ ውስጣዊ ሥራ በልጅነት ጉልበታቸው በመታዘዝ ያገለግላሉ የቤተ ክርስቲያኑ አጥር በተሠራ ጊዜ ብዙ ገንዘብ ያስወጣ የነበረውን የአርማታ መሙላት ሥራ በሰንበት ት/ቤት ተማሮች ጉልበት መሸፈኑ ታውቆአል ለእንነዚህ የመልካም ሥራ ባልደረቦች የሰንበት ት/ቤት ተማሮች ከአንድ በጎ አድራጊ በተገኘና ከደብሩ ጽ/ቤት በተዋጣ ሰባት ሺህ ብር ዩኒፎርም የተገዛላቸው መሆኑን የደብሩ አስተዳዳሪ መልአከ ምህረት ጌታቸው አዳፍሬ ገልጸዋል ።

የልማት ሥራን በተመለከተ ፣

በቦሌ ደብረ ምህረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው የልማት ሥራዎች ተከናውነዋል ከእንዚህም መካከል ጥቂቶቹ ፣

፩/ ከአርባ አምስት ሺህ በላይ የፈጀ ቤተ ልሄም ሥራው ተጠናቆ በአገልግሎት ላይ ይገኛል ።

፪/ ቤተ ክርስቲያኑ ደወል ስለአልነበረው አንድ ትልቅ ደወል በአንድ በጐ አድራጊ ተገዝቶ በአገልግሎት ላይ ይገኛል ።

፫/ ከአሥራ ስምንት ሺህ ብር በላይ በሆነ ወጭ ሙሉ በሙሉ የቤቱ ክርስቲያኑ ጣራ ተስተካክሎ በቤተ ክርስቲያኑ ጣራ እየገባ አስቸግሮ የነበረው ፍሳሽ እንዲወገድ ተደርጓል ።



የቦሌ ደብረ ምህረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን

፬/ ከ፪፻፵ ሜትር በላይ ርዝመት ያለው የቤተ ክርስቲያኑ አጥር በብረትና በድንጋይ በብሎኬት ከ፹ ሺህ ብር በላይ በሆነ ወጭ በአማረ ሁኔታ ታጥሮአል ።

፭/ እያንዳንዳቸው ፱ ሜትር ስፋት ያላቸው በቤተክርስቲያኑ አጥር ዙሪያ መካከል ለሚገኙ ትልልቅ ሦስት በሮች የእያንዳንዳቸው ዋጋ ፲፮ ሺህ ብር የፈጀ ሦስት የብረት መዝጊያዎች በበጎ አድራጊዎች ልግስና ተገዝተው ቀርበዋል ።

፮/ ከአሥር ሺህ ብር በላይ የፈጀ የንዋየ ቅድሳት መሸጫ እንዲሁም የንብረት ማስቀመጫ ዕቃ ቤትና የግብር ቤት ተሠርቶ በአገልግሎት ላይ ውሎአል ።

፯/ አንድ በጎ አድራጊ ግለሰብእ ከ፶ሺህ ብር በላይ ሰጥተው የደብሩ ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤትም ብር ፲፩ሽህ ፭፻ በአደረገው አስተዋጽኦ የቤተ ክርስቲያኑ አውደ ምህረት ዙሪያ በብረትና በኮንክሬት በአማረ ሁኔታ ተሰርቶ ይገኛል ።



መልአከ ምሀረት ጌታቸው አዳፍሬ የደብሩ አስተዳዳሪ

፰/ የቤተ ክርስቲያኑ ውስጣዊ አካሉ በተለያዩ ህብረ ቀለማት በመቀባት የምእመናን ዐይን በሚማርክ መልኩ አምር ይታያል ።

የወደፊቱን ዕቅድ በተመለከተ

ቀሪውን የቤተ ክርስቲያኑን አጥር ዙሪያ ለማሳጠርና እንዲሁም በሙኮድ አጥር ሥር በቀበና ወንዝ ላይ ከወረዳ ፲፱ ቀበሌ ፶፬ እና ከደብረ ይባቤ ቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን የሚአገናኝ ከ፹ሺህ ብር በላይ በሆነ ወጭ ለማሠራትና የስብከተ ወንጌል አዳራሽ በሆነ ክርስቲያናዊ ፍቅር በማስተባበር መልአከ ምህረት ጌታቸው አዳፍሬ የፈጸሙት መልካም ሥራቸው ቅ/ቤተ ክርስቲያን ለጣለችባቸው ከፍተኛ ኃላፊነትና አደራ በቅን ልቡና ለመፈጸም ያላቸውን ብቃት ያስረዳል ።

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ

# የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት የሥራ እንቅስቃሴ ፤

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያሉት የብዙ ምዕት ዓመታት ዕድሜ ያላቸው ጥንታውያን አድባራትና ገዳማት ከሚገኙባቸው ሀገረ ስብከቶች አንዱ የደቡብ ወሎ ሀገረ ስብከት ነው ።

በዚህ ሀገረ ስብከት ከሚገኙት ጥንታውያን አድባራትና ገዳማት ጥቂቶች የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግማደ መስቀል የሚገኝባት ግሼን ደብረ ከርቤ ማርያም ያለችው በዚሁ ሀገረ ስብከት ነው ፣ የሽህ ዓመታት ባለታሪክ የሆኑትም ተድባበ ማርያምና አትሮንስ ማርያም ሌሎችም እያሌ ገዳማትና አድባራት በዚሁ ሀገረ ስብከት ይገኛሉ ።

የዚህ ሀገረ ስብከት የሥራ እንቅስቃሴው ምን እንደሚመስል የሀገረ ስብከቱ ተ/ ሥራ አስኪያጅ በቁጥር ፭፻፴፪/ ፹፯ በ፳፯/፯/፲፱፻፹፯ ዓ/ም ለመንበረ ፓትርያርኩ ጠቅላይ ጽ/ት ከላኩት ደብዳቤ ለመረዳት እንደቻልነው በዚህ ሀገረ ስብከት ተገቢ የሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት በመካሄድ ላይ መሆኑን ይገልጻል ።

ሰበካ ጉባኤን በተመለከተ

የሀገረ ስብከቱ ተ/ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ትጉሃን ይትባረክ ታጠቀ እንደገለጹት የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ የሚሰጡትን አባታዊ መመሪያ በመቀበል የሀገረ ስብከቱ ሠራተኞች ለቅድስት ቤተ ክርስታቲያናትን አገልግሎት በአላቸው ፍቅርና ቅን ታዛዥነት በሀገረ ስብከቱ በሚገኙት ከስድስት መቶ በላይ በሆኑት አብያተ ክርስቲያናት በሁሉም ሰበካ ጉባኤ በሚገባ ተቋቁሞ የቃለ ዓዋዲው ድንጋጌ ተጠብቆ ሥራው በሚገባ በመከናወን ላይ እንደሚገኝ ተገልጾአል ።

በዚህም ከምእመናን በሚገኘው የሰበካ ጉባኤ አስተዋጽኦ በየአድባራቱና በየገዳማቱ ለሚገኙት የአብነት መምህራን ተገቢውን ክፍያ ስለሚአገኙ ነቅተውና ተግተው ጥንታዊውን የቤተ ክርስያንን ትምህርት በማስተማራቸው ብዙ ደቀመዛሙርት በማፍራት ላይ ናቸው ።

ስብከተ ወንጌልን በተመለከተ በሀገረ ስብከቱ ርእሰ ከተማ በደሴ በሚገኙት አድባራትና ገዳማት በሁሉም በየዕለቱ የወንጌል ትምህርት በበሰሉ መምህራን ይሰጣል በእርግጥ በዚህ ሀገረ ስብከት ውስጥ በአሉት አውራጃዎችና ወረዳዎች በሚገኙት አድባራት እስከ ወረዳ ድረስ ተገቢውን የወንጌል ትምህርት ለማዳረስ የወንጌል መምህራን እጥረት እንዳለ ቢታወቅም በተቻለ መጠን የወንጌል ትምህርት በመስጠት ላይ መሆኑን ተጠባባቂው ሥራ አስኪያጁ አልሸሸጉም ሆኖም በደሴ ከተማ ሠርገው የገቡት መናፍቃን በክህደት ትምህርታቸው ምእመናንን እንዳያስቸግሩ በሀገረ ስብከቱ ያሉት የወንጌል መምህራን ከምእመናን ጋር በመተባበር በርእሰ ተከማው ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ዘወትር ጠንክረው ያስተምራሉ

ሰንበት ት/ቤትን በተመለከተ ፣

በደቡብ ወሎ ርእሰ ከተማ በደሴ በሚገኙት አድባራትና ገዳማት የተጠናከረ የሰንበት ት/ቤት ተቋቁሞአል ። ለተማሮችም ተገቢው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ይሰጣል የሀገረ ስብከቱ ጽ ቤትም መጻሕፍት ጋዜጦችና መጽሔቶች በየሰንበት ት/ቤቱ እንዲያዳረሱ ያደርጋል ።

በዚህ ሰንበት ት/ቤት በጥቂት ሀገረ ስብከቶች የተከሰተው ሕጸናትን በክህደት ትምህርት ለመበረዝ ሠርጎ የሚገባው የመናፍቅን ቡድን ሠርጎ እንዳይገባ በሀገረ ስብከቱ የወንጌል መምህራን ብርቱ ክትትል እንደሚደረግ ሥራ አስኪያጁ ገልጸዋል ።

ቅርሳቅርስን በተመለከተ ፣

በአሁኑ ዘመን ይገኖሉ ወይም በቀላሉ ይተካሉ የማይባሉ እያሌ ንዋየ ቅድሳትና የታላቋ ሀገራችን የጥንታዊ ታሪኳ የክብር መዘክር የሆኑት ዕቃዎች ከሚገኙባቸው አድባራትና ገዳማት ከፊሎች ያሉት በዚሁ ሀገረ ስብከት ስለሆነ ንዋያተ ቀድሳቱና የክብር ዕቃዎች በክብር ተመዝግበው የሚጠበቁበትንና ብልሽት በማያገኙቸው ቦታ በጥንቃቄ እንዲቀመጡ ሀገረ ስብከቱ ለአበው መነኮሳትና ካህናት ለደሴ ነዋሪዎች ምእመናን በየቦታው ላሉት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ተገቢ የሆነ ትምህርት በመስጠት ላይ ነው ። ከባሕልና እስፖርት ኩዳይ ሚ/ር ከሚመለከታቸው ባለሙያዎችና ከታላላቅ የከተማው ነዋሪዎች ጋርም በመካከር ለቅርሶች አጠባበቅ አስፈላጊውን መመሪያ እንደሚሰጥ ተ/ ሥራ አስኪያጁ ሊቀ ትጉሃን ይትባረክ ታጠቅ ገልጸዋል ።

የሀገረ ስብከቱ ተ/ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ትጉሃን ይትባረክ ታጠቅ በአጠቃላይ እንደገለጹት በዚህ ሀገረ ስብከት ያሉት ካህናትና ምእመናን አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በማሳነጽ ያረጁትን በመጠገንና





www.ethiopianorthodox.org

በማሳደስ የሚአደረጉት ከፍ ያለና የተቀደሰ የሥራ እንቅስቃሴ በእጅጉ የሚደነቅ መሆኑን በሰፊው ገልጸዋል ።

ተጠባባቂው ሥራ አስኪያጅ በዚህ ሀገረ ስብከት በተ/ሥራ አስኪያጅነት በተሾሙት በአጭር ጊዜ ውስጥ የከተማውን ሕዝብ በማስተባበር የተጣሉትን በማስታረቅ የተራራቁትን በማቀራረብ የተጣመመውን በማቃናት የጎደለውን በማሟላት የሀገረ ስብከቱ የሥራ እንቅስቃሴ በተገቢው መንገድ እንዲቀላጠፍ በማድረጋቸው ሕዝቡንና እርሳቸውን ከልብ እናደንቃለን ።

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ

# ለመምህር ክፍለ ዮሐንስ መርሻ አቀባበል ተደረገላቸው

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መልካም ፈቃድ ከየካቲት ወር ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ጀምሮ መምህር ክፍለ ዮሐንስ መርሻ የታላቁ ደብረ ዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም አስተዳዳሪ ሁነው ተሹመዋል

መምህር ክፍለ ዮሐንስ መርሻ በታላቁ ደብረ ዝቋላ ገዳም አበው መነኮሳትን በመታዘዝ በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ተመድበው ከ፳ ዓመታት በላይ በትህትናና በቅንነት አገልግለዋል በዚህም የተቀደሰ አገልግሎታቸው በደብረ ዝቋላ ገዳም አረጋውያን መነኮሳትና መናንያን ዘንድ ኬልክ ያለፈ ተወዳጅነትና አድናቆትን አትርፈዋል ።

መምህር ክፍለ ዮሐንስ ከ፲፱፻፸፰ ዓ.ም ጀምሮ የደብረ ዝቋላ ገዳም መጋቢ ሁነው በመሾም ለቁጥር የሚያታክቱ ሥራዎችን ያከናወኑ ሲሆኑ በተለይ በደብረ ዝቋላ ገዳምና በወንበር ማርያም እልህ አስጨራሽ የነበረውን ከፍተኛ የውሃ ችግር የጉድጓድ ውሃ በማስቆፈርና ያሉትን የውሃ ምንጮች በማጉልበት የነበረው የውሃ ችግር እንዲቃለል አድርገዋል

በዚህ የተቀደሰ አገልግሎታቸው መምህር ክፍለ ዮሐንስ መርሻ በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ የተቀደሰ ትዕዛዝ የደብረ ዝቋላ ገዳም መምህር ሁነው ተሹመው የካቲት ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም በገዳሙ በገቡበት ዕለት ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ የሰሜን አሞ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ



መምህር ክፍለ ዮሐንስ መርሻ የታላቁ ደብረ ዝቋላ ገዳም አስተዳዳሪ እኒህ ናቸው ።

ያዕቆብ የደቡብ አሞ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ፀባቴ ተክለ ሚካኤል እንዲሁም ሊቃውንትና ካህናት በተገኙበት የገዳሙ አበው መነኮሳትና መናንያን ልባዊ በሆነ ደስታ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

ቅዱስ አምላካችን መልካም የሥራ ዘመን እንዲያደርግላቸው እንጸልያለን ።

መ/ኤፍሬም በየነ

# ለ፪፻፺፪ አብያተ ክርስቲያናት ልብሰ ተክህኖ የረዱ በጎ አድራጊ

አቶ ተገኝ ገ/ ማርያም (ተገኝ ሴንጀር) ይባላሉ

አቶ ተገኝ ከአባታቸው ከአቶ ገብረ ማርያም ደስታና ከእናታቸው ከወ/ሮ ዘሪቱ አየለ በአዲስ አበባ ከተማ በገነተ ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ በ፲፰፻፺፮ ዓ/ም ተወለዱ ። ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚሁ በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት ተምረዋል ።

አቶ ተገኝ ከወጣትነት ዕድሜአቸው ጀምሮ በግል ሥራ ላይ ተሰማርተው እንዳሉ ከወ/ሮ ተዋበች ወሌዬ ጋር የጋብቻ ሥርዓት ፈጽመው በሥጋ ወደሙ ተወስነው ከባለቤታቸው ጋር የኖሩ ታዋቂ የቤተ ክርስቲያናችን አባል ነበሩ ።

አቶ ተገኝ ገ/ማርያም ከልጅነታቸው ጀምረው መንፈሳዊ ሥራ መሥራት ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ልዩ ሀብት በመሆኑ ሠርተው የሚያገኙትን ለራሳቸው ብቻ ሳያውሉ የመንግሥተ ሰማያትን ዋጋ በሚያስጥ ተግባር አውለውታል ። ሀብታቸውን ለነዳያን ከመመጽወት ጋር በመላ ኢትዮጵያ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ለ፰፻፹፪ አብያተ ክርስቲያናት ለአምስትና ለሰባት ልውካን



በጎ አድራጊው አቶ ተገኝ ገ/ማርያም እኒህ ነበሩ (ተገኝ ሴንጀር)

የሚያገለግል ልብሰ ተክህኖ ሰጥተዋል እንደመጾር መስቀል የብር ጻናጽልና መቋሚያ የመሰሉትን ለግሰዋል ።

ከባለቤታቸው ከወ/ሮ ተዋበች ወልዴ ጋር በመሆን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን ታላላቅ ገዳማትና አድባራትን ጎብኝተዋል ። ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም በመሄድ ቅዱሳት መካናትን ተሳልመዋል ። ያላቸውንም ሀብት በፍጹም መንፈሳዊ ደስታ ለቤተ ክርስቲያን ለግሰዋል ።

በጎ አድራጊው አቶ ተገኝ ልጅ ስለሌላቸው ለአብያተ ክርስቲያናት መርዳት ደስ ይላቸው ነበር እኒህ መልካም ሰው መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫዬንም ፈጽሜአለሁ ሃይማኖቴንም ጠብቄአለሁ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል «የሚለውን የሐዋርያውን ቃል ተከትለው የተቀደሰ ዓላማቸውን ፈጽመው በተወለዱ በ፹፱ ዓመታቸው የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ ተለይተዋል ። የበጎ አድራጊው የሙት ዓመት መታሰቢያ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም ዘመድና ወዳጅ በተገኙበት በመካነ መቃብራቸው በአዲስ አበባ ገነተ ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ታስቦአል ።

በየሀገረ ስብከቱ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የሰጡት ልብሰ ተክህኖ ብዛት

፩/ ለሰሜንና ለምሥራቅ ለምዕራብና ለደቡብ ሸዋ ለ፩፪፰ አብያተ ክርስቲያናት ፩ሺ፩፻፩ ልብሰ ተክህኖ ፣

፪/ ለሰሜንና ምዕራብ ጎጃም ለ፩፻፩ አብያተ ክርስቲያናት ፩፻፭ ልብሰ ተክህኖ ፣

፫/ በሰሜንና በደቡብ ጎንደር ለ፴ አብያተ ክርስቲያናት ፵፭ ልብሰ ተክህኖ ፣

፬/ በወሎ ለ፳ አብያተ ክርስቲያናት ፳፭

፭/ በኤርትራ ለ፫ አብያተ ክርስቲያናት ፲፭

፮/ በትግራይ ለ፭ አብያተ ክርስቲያናት ፳፱

፯/ በሐረር ለ፲፫ አብያተ ክርስቲያናት ፹፭

፰/ በአርሲ ለ፩ ቤተ ክርስቲያን ፭

፱/ በባሌ ለ፪ አብያተ ክርስቲያናት ፲

፲/ በከፋ ለ፭ አብያተ ክርስቲያናት ፳፭

፲፩/ በአሰቦት ለ፩ ቤተ ክርስቲየን ፭

፲፪/ በሲዳሞ ለ፩ ቤተ ክርስቲያን ፭

፲፫/ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ለ፵፰ አብያተ ክርስቲያናት ፰፻፺፰

፲፬/ በቅድስተ ሀገር ኢየሩሳሌም ለ፫ አብያተ ክርስቲያናት ፲፭

በአጠቃላይ ለ፪፻፺፪ አብያተ ክርስቲያናት ፪ሺ፫፻፰፰ ልብሰ ተክህኖ ረድተዋል ከዚህም ሌላ ለታቦታት ሕግ መንበርና መቋሚያዎች ለ፲፰ አብያተ ክርስቲያናት ለግሰዋል ። በአደረጉትም እያሌ የልብሰ ተክህኖ ስጦታ ሲንጀር እየተባሉ ይጠሩ ነበር ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለነፍሳቸው በጎ ዕረፍትን እየተመኘች አርአያነታቸውን ምእመናን እንዲከተሉት መልእክቷን ታስተላልፋለች ።

አቅራቢ ዘነበ ብርቅነህ

www.ethiopianorthodox.org

# በቅርጻ ቅርፅ ሙያቸው የታወቁት አባት

በጎጃም ሀገረ ስብከት በባሕር ዳር አውራጃ በይልማና ዴንሳ ወረዳ በሰንቀኛ በዐለ እግዚአብሔር ደብር የተወለዱት አባ ወልደ ተክለ ሃይማኖት ካሣ የመዝገብ ቅዳሴ የቅኔ የባሕረ ሐሳብና የመጽሐፈ መነኮሳት ትርጓሜ ትምህርታቸውን አጠናቀው በታላቁ ገዳም በደብረ ሊባኖስ በምናኔ ፲፪ ዓመት ከኖሩ በኋላ በገዳሙ ሥርዓት ምንኩስና ፈጽመው እስከቁምስና ያለውን መዓርገ ክህነት ተቀብለዋል።

በዚሁ በደብረ ሊባኖስ ገዳም በቈመታቸው ልክ ጉድጓድ ቆፍረው በዚያ ገብተው ሰባት ዓመት ከጸየለዩ በኋላ በዚሁ ገዳም መስቀል መቅረፅ ሥእል መሣል ሌሎችንም ቅርጻ ቅርጾች እስከ ታቦት መቅረጽ ድረስ ተምረው መስቀሎችንና የመስቀል ቅርፅ ያለባቸውን ልዩ ልዩ ንዋየ ቅድሳትን እየቀረጹ ለአያሌ አብያተ ክርስቲያናት ለሊቃነ ጳጳሳትና ለአበው መነኮሳት በነጻ ይሰጡ እንደነበር የሕይወት ታሪካቸው ያስረዳል ።



በቅርጻቅርጽ ሙያቸው የታወቁት አባ ወልደ ተክለ ሃይማኖት እኒህ ነበሩ

አባ ወ/ተክለ ሃይማኖት ካሣ ለቅ/ቤተ ክርስቲያን ከነበራቸው ፍቅር የተነሣ አዳዲስ ለሚሾሙት ኤጲስ ቆጶሳት የክብር መቋሚያዎችን አይካኖችን እየቀረጹ በነጻ ያበረክቱ ነበር ከዚህም ሌላ በውጭው ዓለም በኢየሩሳሌምና በምዕራብ አገሮች ለተቋቋሙት አዳዲስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ሥዕል እየሳሉ መስቀል እየቀረጹና የተለያዩ የቅዱሳት ምሥጢራት መፈጸሚያ ቅርጻቅርጾችን በነጻ ለግሰዋል።በዚህ የሥዕልና የቅርጻ ቅርጽ ሚያቸው በግርማዊት እቴጌ መነን መልካም ፈቃድ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ብዙ የቅርጻ ቅርጽ ሥራዎችን ሠርተው ሥዕሎችን ሥለው ለመዘክርነት በዚያው አበርክተው ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል ። አባ ወ/ተክለ ሃይማኖት ከሠሩአቸው የአያሌ አብያተ ክርስቲያናት መንበረ ታቦት መካከል የአዲስ አበባ ደብረ ገሊላ አማኑኤል የደብረ ኃይል ቁልቢ ቅዱስ ገብርኤል መንበሮች ይገኙባቸዋል ።

በአሁኑ ጊዜ ዓለም አቀፋዊ ዝናን ያገኙትን የአክሱምን ሐውልት የቀሊያንና የዝሆን ቅርጽ የሳሊበላን አብያተ ክርስቲያናት የኢትዮጵያን የካርታ አቀማመጥ በተለየ ሥነ ጥበባቸው ከእንጨት ቀርጸው ለአገር ያስረከቡ ታዋቂው የሥነ ጥበብ ባለሙያ አባ ወ/ተክለ ሃይማኖት ናቸው ።

አባ ወ/ተክለ ሃይማኖት በዚህ የተለየ ችሎታቸው በባሕል ሚ ር በሥነ ጥበብ መምህርነት ተቀጥረው በጡረታ እስከ ተገለሉበት ድረስ ብዙ ዓመታት አገልግለዋል አያሌ ባለሙያዎችንም ተከተዋል በዚሁ ሥራቸው ላይ እንዳሉ ዳካር ላይ በተደረገው የጥቁር ሕዝቦች ፌስቲ በዓል ላይ የእኒሁ አባት የቅርፅ ሥራ ታይቶ(ቀርቦ) አሸናፊነት ስለአገኙ ከሀገሪቱ መሪ ሽልማት አግኝተዋል ።

በዚህም ዝናቸው የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም አባ ወ/ተክለ ሃይማኖት ከኢትዮጵያ ሰአልያን አርቲስቶች አንዱ መሆናቸውን በጋዜጣና በመጽሔት መግለጹ ይታወሳል ።

ታላቁ የጥበብ ሰው አባ ወ/ተክለ ሃይማኖት በአደረባቸው ሕማም ምክንያት ጥቅምት ፲ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ/ም አርፈው ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና አያሌ ሕዝበ ክርስቲያን በተገኙበት በእንጦጦ መንበረ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የቀብራቸው ሥርዓት ተፈጽሞአል ።

www.ethiopianorthodox.org